ጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሣይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋናሥነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የአማርኛ ቋንቋ  መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያ አጠቃቀም ፍተሻ ፡፡

(በምስራቅ ወለጋ ዞኒ፣አርጆ ወረዳ የሚገኙ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተተኳርነት)

በ

ኦላኒ ጉደታ  አያንሣ

ግንቦት 2013 ዓ.ም

ጅማ፣ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሣይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋናሥነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያ

# አጠቃቀም ፍተሻ

(በምስራቅ ወለጋ ዞን፣በአርጆ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

9ኛ እና10ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተተኳርነት)

በ

ኦላኒ ጉደታ

የጥናቱ አማካሪ

ደመላሽ መንግስቱ ተሰማ (ዶ/ር)

ይክበር ይመስገን (ኤም.ኤ)

ግንበ 2013 ዓ.ም

ጅማ፣ኢትዮጵያ

**የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያ**

**አጠቃቀም ፍተሻ**

**(በምስራቅ ወለጋ ዞን፣በአርጆ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ እና10ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተተኳርነት)**

በ

ኦላኒ ጉደታ አያንሳ

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ -------------------------------- ፊርማ ------------------ ቀን ---------

ፈታኝ ---------------------------------- ፊርማ ------------------ ቀን --------

ፈታኝ ---------------------------------- ፊርማ ------------------ ቀን --------

## ማረጋገጫ(Declaration)

በምስራቅ ወለጋ ዞን፣በአርጆ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያ አጠቃቀም ፍተሻ 9ኛ እና10ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተተኳርነት፤በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሣይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉ በመሆኑ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም ኦላኒ ጉደታ አያንሳ

ፊርማ----------------------------

ቀን 03/13/2013 ዓ.ም

# ምሥጋና

በቅድሚያ የሁሉም ፈጣሪ የሆነው እግዚያብሔር ሁሉንም አሳልፎ ለዚህ ስለአበቃኝ ምስጋና ይግባው፤ጠቃሚ አስተያየቶች በመለገስ ለሥራዎቼ ፈጣን ምላሽ በመስጠት ጥናቱ ለዚህ እንዲበቃ ያገዙኝን ዋና አማካሪዬ ደመላሽ  መንግስቱ ተሰማ (ዶ/ር) እና ረዳት አማካሪዬ ይክበር  ይመስገን  (ኤም.ኤ) ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

በመቀጠልም ከጎኔ ሁኖ ሳይሰለቹ በሀሳብም ሆነ በቁሳቁስ ለረዱኝ ቤተሰቦቼ ለባለቤቴ ጣይቱ ገርባ፣ ለልጆቼ ኦልያድ ኦላኒ፣ለናብራቦን ኦላኒና ለወርቃማ ልጀ ሮብሳን ኦላኒ ከፍ ያለ ምስጋና ይደረሳችሁ፡፡በመጨረሻም መረጃዎችን በመስጠትና በማገዝ የረዱኝን ለመ/ር ጌታቸዉ መብራቴ፣ለደመቀ አስረስ እና ለተስፋዬ ዱረሦ   ምስጋናዬ እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡

**አጠቃሎ(Abstruct)**

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በምስራቅ ወለጋ ዞን በአርጆ ወረዳ የሚገኙት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የምያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀም በጠቅላይ ናሙና በመጠቀም መፈተሽ ነው። ዓላማውን ለማሳካትም አይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዜደ ተግባራዊ ሆኗል። የጥናቱ ተሳታፉዎችም በአርጆ ሁለተኛ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ዘጠኝ የአማርኛ ቋኝቋ መምህራን እና አንድ የትምህርት ቤቶቹ ሱፐርቨይዘር ያሳተፈ ነበር። መረጃዎቹ የተሰበሰቡትም በክፍል ዉስጥ ምልከታ ፣በቃለ መጠቅእና በውይይውት መረጃዎችን በመሰብሰብ በገላጩ ምርምር ስልት ተተንትነዋል። የጥናቱ ግኝትም በቂ የሆነ ሥልጠና ባለማግኘታቸው በአጠቃቀም ረገድ ያላቸው ተሳትፎ አናሳ መሆን፣በአብዛኛው ያለ መርጃ መሣርያ ማስተማራቸው፣የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ መሣርያ ጉል ሆኖ አለመገኘት፣ሳብ እንዳልሆነ፣ተሰማም እዳልሆነ፣በመጠኑ የተጠቀሙት እይታዊ ብቻ መሆኑ፣ለተጠቀሙትም ተገቢ ማስቀመጫ ቦታ እንደለላቸው፣ የተገኙትም የትምህርት መርጃ መሳረያዎች በመምህራን አሰተባባርነት በተማሪዎች የተሠሩ መሆን እና ተጠኝዎቹ የትምህርት መርጃ መሳርያ ለማዘጋጀት በቂ ዕውቀት፣ ፍላጎትና ልምድ እንደለላቸው በጥናቱ ምልከታ ወቅት ለማረጋገጥ ተችለዋል። የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎች ከተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውጭ ሌሎች እንደሌሉ ተረጋግጧል። በመሆኑም የመንፈቀ ዓመት ዕቅዳቸው ከመርሓ ትምህርቱ ጋር የየትምህርት ቤቶቹ እቅዶች የቅርፅና የይዘት ልዩነት ታይተዋል። ትንተናውም መረጃዎቹ በሚያነሱት ጉዳይ ተከፋፍሎ በሠንጠረዥ ውስጥ በቁጥርና በመቶኛ ስሌት (%) በማስቀመጥ በምስራቅ ወለጋ ዞን፣በአርጆ ወረዳ ካሉት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያ አጠቃቀም ሁነታ አጥኝው ጠቁመዋል። መመጨረሻም ለእነዚህ እንቅፋቶችም በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ በመምህራን ትምህርት ኮለጅ ደረጃ፣ በትምህርት ቤት ደረጃና የሚመለከተው አካላት ምን ማዲረግ እንደሚገባቸው የመፌትሄ ሀሳቦች ተጠቁመዋል።

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ማረጋገጫ ........ iv

ምሥጋና ........ v

አህጽሮተ ጥናት(Abstruct) ........ vi

ምዕራፍ አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ........ 3

1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ........ 4

1.4 የጥናቱ ዓላማ---------- 5

1.4.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ ........ 5

1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ........ 5

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 6

1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 6

1.7 የቁልፍ ቃላት እና ሐረጋት ፍቺ ........ 7

ምዕራፍ ሁለት ........ 8

ክለሳ ድርሳናት ........ 8

2. መግቢያ ........ 8

2.1 የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ምንነት ........ 8

2.2 መምህራን ለምን የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን ይጠቀማሉ? ........ 9

2.3 የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ........ 11

2.4 የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ........ 15

2.5 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ........ 17

2.5.1 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የአመራረጥ መርሖ ........ 17

2.5.2 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ባሕርያት ........ 20

2.5.3 የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን የማቅረብ (የማሳየት) መርሖ ........ 25

2.5.4 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ሥነልቦናዊ ሁኔታ................26
2.6.1 በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቀቀም ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮች፣.....................................................................................27
2.6.2 የሥልጠና ጉዳይ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ዙሪያ ......30
2.7 የማስተማሪያ መሣሪያዎች በመርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም ያላቸው እገዛ......32
2.7.1 የተማሪ መጽሐፍና የመምህሩ መምሪያ ..........................................32
2.7.2 መርሐ ትምህርት፣ ....................................................................33
2.8 የቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት...................................................34
ምዕራፍ ሦስት፣------------------------------------------------------------- ---38
የጥናቱ ዘዴ እና አካሄድ ...........................................................................38
3.1 መግቢያ .............................................................................................38
3.2 የጥናቱ ስልትና ንድፍ........................................................................39
3.3 የትምህርት ቤቱ ናሙና አመራረጥ ..........................................................39
3.4 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ............................................................40
3.5 የመማርያ ክፍሎች አመራረጥ ዘዴ..........................................................40
3.6 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ዘዴ..........................................................41
3.7 የመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎች.............................................................41
3.8 የመረጃ አተናተን ስልት .......................................................................44
ምዕራፍ አራት ......................................................Error! Bookmark not defined.
የዋናው ጥናት ውጤት ትንተና እና ማብራሪያ ..................................................46
4 መግቢያ ..............................................................................................46
4.1. ከክፍል ዉስጥ ምልከታ የተገኘ ውጤት ....................................................47
4.1.1. የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም አሰመልክተው የተገኙ ውጤቶች.............................................................................47
4.1.2 መምህራን በኅትመት ውጤቶች የመጠቀም ልምድ በተመለከተ፤..........65
4.1.3 መምህራን በተለያዩ ሠሌዳዎች የመጠቀም ልምድ አስመልክተው የተገኘ ውጤት...........................................................................................65
4.1.4 ታላሚ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በተመለከተ ስለአጋጠማቸው ችግር አሰመልክተው የሰጡት ምላሽ፣ ...........................................66

4.1.5 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችና የማስተማሪያ መሣሪያዎች.................66
4.2. ለመምህራን ከቀረበው ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ........................................67
4.3. ለመምህራን ከተሰራጨው ጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ...............................70
4.3.1. የመምህራንን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃት የሚወሰኑት ተላውጦዎች /Variables/ .........................................................................................77
4.3.1.1 ግለሰባዊ ተላውጦዎች......................................................................77
4.3.1.2 የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ፣ .78
የታላሚ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያን በተመለከተ የቅድመ ሥራ ላይ ሥልጠና፣ ..............................................................................................78
4.3.1.3. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀም በተመለከተ የታላሚ መምህራን የሥራ ላይ ሥልጠና፤ ....................................................................79
4.3.1.4. በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም የቋንቋ መምህራኑ ፍላጎትና ተነሳሽነት፤ ..............................................................................80
4.3.2. ተቋማዊ ተላውጦዎች ...............................................................................81
4.3.2.1 ቦታን በተመለከተ ...............................................................................81
4.3.2.2 በጀትን በተመለከተ ..............................................................................81
ምዕራፍ አምስት---------------------------------------------------------------------------88
ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች .............................................................................88
5.1 ማጠቃለያ ..............................................................................................88
5.2 የመፍትሄ ሀሳቦች፤…………………………………………………………….91
ዋቢ መፃሕፍት .....................................................................................................92
አባሪ...................................................................................................................95
አባሪ «ሀ » የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅፅ፣ ...............................................95
አባሪ «ለ የፅሁፍ መጠይቅ፡ ....................................................................................99
አባር ሐ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች....................................................................103

## የሠንጠረዥ ማዉጫ

ሠንጠረዥ ገጽ

ሠንጠረዥ 4.1 ........................................................................................................ 48
4.1.1.2 የክፍል ውስጥ ምልከታ ከተካሄደባቸው ሃያ ክፍለ ጊዜያት መካከል መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የተጠቀሙባቸው ክፍለ ጊዜያት ብዛት፣ ........................................................................................................ 48
ሠንጠረዥ 4.2 ........................................................................................................ 49
4.1.1.3 በምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ጥራት እሰመልክቶ የተገኘ ውጤት፤ ............................................ 49
ሠንጠረዥ 4.3 ........................................................................................................ 50
4.1.1.4 በምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠን፣ ........................................................................................................ 50
ሠንጠረዥ 4.5 ........................................................................................................ 52
4.1.1.5 የክፍል ምልከታ በተካሄደባቸው ጊዜያት መምህራን አገልግሎት ላይ በአዋሏቸው የቋንቋ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመጠቀም ብቃት፣............ 52
ሠንጠረዥ 4.6 ........................................................................................................ 54
4.1.1.6 መርጃ መሣሪያዎቹ በአገልግሎት ላይ ሲውሉ የነበረው የክፍል ውስጥ መስተጋበርን፣ ........................................................................................................ 54
4.1.1.8 በዕለቱ መምህራን የተገለገሉባቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ማራኪነት በተመለከተ የተማሪዎችን ስሜት የሚዳስስ፤ .................................. 57
ሠንጠረዥ 4.9 ........................................................................................................ 58
4.1.1.9 በአገልግሎት ላይ በዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመጠቀጠም ተማሪዎች የሚያሳዩት የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ውጤት፣............ 58
ሠንጠረዥ 4.10 ........................................................................................................ 59

4.1.1.10 በምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተገቢነት፣ ........................................................................ 59
መምህራን እውነተኛ በሆኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመጠቀም ልምድ፣ 60
ሠንጠረዥ4.12. ........................................................................ 62
4.1.1.12 ከታላሚ ትምህርት ቤቶች ለናሙና በአንዱ (በአርጆ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት እቅድ ውስጥ የተጠቆሙትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት በዓይነት ተለይቶ ሲቃኝ፤ ........................ 62
ሠንጠረዥ 4.13. ........................................................................ 72
በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሓ ትምህርት ውስጥ የተጠቁሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር /አንደኛዉ መንፈቀ ዓመት/ .................................... 72
በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሓ-ትምህርት ውስጥ የተጠቆሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር (የአንደኛው መንፈቀ ዓመት) ................................ 75
ሠንጠረዥ 4.16 ........................................................................ 79
የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ መምህራን ያገኙት የሥራ ላይ ሥልጠና፣ ........................................................................ 79

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የመማር-ማስተማር ሂደት ጥበባዊና ሳይንሳዊ ነዉ፡፡ ‹‹ጥበባዊነዉ››ሲባል ዕዉቀትን፣ አስተሳሰብንና ክሂል አይረሴ በሆነ መንገድ ማስተላለፍን ሲያመለክት፣በቋንቋ መምህሩ/መምህሯ ግላዊ ችሎታና የማስተማር ብቃት የሚገልጽነዉ፡፡ ሳይንሳዊ ነዉ ሲባልደግሞ በሳይንሳዊነቱ የሚለወጥ፣ የሚያድግና የሚማሩት ነዉ፡፡ celceMurcia (1991፤12) መምህሩ (መምህሯ) ዕዉቀትን በተጨባጭ ቅደም ተከተሉን ጠብቆ በሥርዓት በማቅረብ የተፈለገውን ዕውቀት፣ አስተሳሰብና ክሂልን በማስጨበጥ በሳይንሳዊ የቋንቋ መርሖች ማቅረብን ያሳያል Corder (1975)፡፡

በዚህ ረገድ መምህራን ዕውቀታቸዉን፤ የፈጠራ ችሎታቸውንና ልምዳቸውን በመጠቀም ለተማሪዎቻቸው ተገቢ የቋንቋ ዕዉቀትና ክህልን ካስጨበጡ የታሰበውኒ የቋንቋ ዓላማ ስኬታማ ይሆናል፡፡ በማንኛውም ቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት የታቀደውን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ተማሪዎች በእያንዳንዱ የቋንቋ ክሂል ብቃት አገኝተው ታላሚውን ቋንቋ ለማጎልበት ትምህርቱን ግልጽና ቀለል አደርጎ ለማቅረብ ፣ጉልበትና ጊዜን ቆጥቦ ለማስተማር የትምህርት መርጃ መሳርያዎችን መጠቀምን ይጠይቃል፡፡

ኅበዝ መምህራን ለራሳቸው ስብዕናና ለተማሪዎቻቸው ምኞትና ፍላጎት የታቀደውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ፤የተጻፉትን ይዘቶች ለመተግበር በተማሪውና በሚማረው ይዘት መካከል የሚኖረውን ልዩነት ግልጽና ተጨባጭ፣የትምህርት አሰጣጡንም ሣቢና መራኪ ለማድረግ ጊዜና ጉልበታቸውን በአግባቡ ለመገልገል ተገቢ የሆነ የቋንቋ መርጃ መሳርያዎችን ይጠቀማሉ McArthur (1989፣78)፡፡

በተለይ በአሁኑ ጊዜ ይበልጥ ተፈላጊና ውጤታማ በሆነው ተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብና ዘዴ መሠረት ለቋንቋ ተማሪዎች ተገቢነትና ተዛማጅነት ባላቸዉ የተለያዩ የቋንቋ መርጃ መሳርያዎች በመታገዚ የመማር-ማስተማር ሂደቱን ማፋጠን ትኩረት ልሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

ምክንያቱም ቋንቋ ረቂቅና ውስብስብ የመግባቢያ መሳርያ ስለሆነ ነው፡፡ በመሆኑም በመማር ማስተማር ጊዜ በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመርጃ መሣርያ በመታገዝ ከረቂቂነትና ውስብስብነት  በተጨባጭና ግልጽ በሆነ መንገድ  ማቅረብ ተገብ ይሆናል፡፡

በቋንው የመጠቀም ችግርን በተመለከተ (በታላላቆች የትምህርት ተቋማት ሳይቀር፣የዓረፍተ ነገር ባለበት፣ተሳብና ማሰርያ አንቀጽ የሚለይ ተማሪ ለማግኘት እያስቸገረ ነው፡፡ በአገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ የትምህርትን ጥራት ስንመለከት በዬጊዜው፣በየቦታውና በየደረጃው በሚደረገው መደበኛና ኢመደበኛ ትምህርታዊና በአገራዊ ጉዳዮች ላይ የትምህርት ጥራት ወድቋል ፤የትምህርት ትክክለኛነት፣አግባብነት፣ ችግር  ፈችነት ወዘተ አጠያያቅ  ደረጃ ላይ ደርሷዋል የምል ሓሳቦች ይሰማሉ፡፡ ለዚህ ጉዳይም ምስክርነት ሊሆን የሚችለው በየወቅቱ የሚታዩት የተማሪዎች ችሎታ ናቸዉ የምል  በየደረጃዉ ይሰማል፡፡ ይህንን  በማጠናከር ባዬ(2000) የዘመኑ ተማሪ በቋንቋ የመጠቀምን ችሎታውን  ስንመለከት የሥራ ማመልከቻ ይቅርና ተራ ደብዳቤ መጻፍ ተስኖታል፡፡ ይህንን ሀቅ የትምህርት ሚንስተር (1994፣2-3) የኢትዮጵያ ትምህርት የተገብነት፣የጥራት ፣የተቀባይነትና የዋጋ ማጣት ውስብስብ ችግሮች ውስጥ እንዳለ ይገልጻል፡፡

አማሬ (1998፣292) ላይ እንደተገለጸው ፣ለትምህርት ጥራት መውደቅ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩትም ከነዚህ መካከል የተማሪው የፈተና ውጤት ዝቅተኛ መሆን፣የደጋሚዎች  ቁጥር መጨመር፣ የሚያቋርጡ  ተማሪዎች መበራከት፣ ወዘተ ናቸው፡፡ የዚህ ሁሉ ድምር  ውጤት መጨረሻዉ  በህብረተሰብ  ዘንድ የሚጠበቅበት ሃላፊነት መሸከም የማይችል ዜጋ ማፍራትይሆናል፡፡ ለዚህ እንደ መፍትሄ ይሆናል ብሎ ያስቀመጠው የትምህርት መርጃ መሳርያዎችን በመጠቀም ማስተማር ነዉ፡፡

በተመሳሳይ ‹‹መምህራን ከተማሪዎች መካከል ቁሞ በገለጻ ብቻ ከማስተማርና በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጽፎ ተማሪዎች እንዲገለብጡ ከማድረግ በተጨባጭና ከአከባቢ በሚገኙ መርጃ መሳርያዎች አስደግፎ  ማስተማር  ችግሩን  ያቃልላል፡፡  በመርጃ  መሳርያ  አስደግፎ  ማስተማር የሚያስተምረውን መምህር ማበረታታት፣መርጃ መሣሪያ የማይጠቀመውን እንዲጠቀም ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመው ስለ ትምህርት መርጃ መሣርያ አስፈላጊነት በአፅንኦት ሲገልጹት ያለ ትምህርት መርጃ መሣርያ ማስተማር ‹‹በጣት ጥፍር ኢረስ እንደ ማለት ነዉ፡፡››ይላሉ (Amare 1998፣292)፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ስለ ትምህርት መርጃ መሣርያ ሲነሳ መምህራን ስለ ትምህርት መርጃ መሣርያ ያላቸው ዕውቀትና አመለካከት ከግምት ውስጥ ማስግባት ያለበት ጉደይ እነደሆነ ተገልፀዋል ፡፡

ከፍ ስል ከተገለጹት ነጥቦች በመነሳት በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያን መጠቀም አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ሆኖም ግን የትምህርት መርጃ መሣርያን ለመጠቀም የአጠቃቀም ግንዛቤ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

መምህራን ለራሳቸዉ ስብዕናና ለተማሪዎቻቸው ምኞትና ፍላጎት ታላሚውን ይዘት ከግብ ለማድረስ ፤የተጻፉትን ይዘቶች ለመተግበር በተማሪውና በሚማረው ይዘት መካከል የሚኖረዉን ልዩነት ግልጽና ተጨባጭ፣የትምህርት አሰጣጥን አይረሴ ለማድረግ እንዲሁም ጊዜያቸዉንና ጉልበታቸውን በአግባቡ ለመገልገል ተገቢ የሆነ የቋንቋ መርጃ መሳርያዎችን ሊጠቀሙ ይገባል፡፡ McArthur (1989፣78)፡፡

‹‹ተማሪዎች በተለያዩ ተግባራት ከተሳተፉ ተግባቦትን በተገቢ ሁኔታ ያቀላጥፋሉ››ይላሉ፡፡ Clark and Irbing (1996:63)፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ Wong (1998፡168) በቋንቋ የመማር -ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ተምረዋል የሚባለው በተለያዩ ተግባራዊ ክንውን የተማሩ እንደሆነ ነው፡፡ ጥሩ የቋንቋ መምህርም ተማሪዎች በተሳትፎ የበለጠ የሚማሩበትን መንገድ ለመለየት አብዛኛውን ጊዜ በተግባር ክንውኖች በማሳተፍ ተግባቦታዊ በሆነ ዘዴ ተፈጥሯአዊ ወደ ሆነው የቋንቋ አጠቃቀም እንድያዘነብሉና እንዲሳተፉ ያግዛል፡፡

‹‹የቋንቋ መምህራን በተለያዩ መርጃ መሳሪያዎች በመገልገል የተማሪዎችን ትኩረት በመሳብ የተለያዩ የቋንቋ ክህሎትን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸዉ፡፡››በማለትም ያብራራል Aggarwal (1996:153)፡፡

በተጨማርም በድሉ (1996፡63-64) መምህራን በንግግር ተግባራት ጊዜ ማድረግ ከሚገባቸዉ ተግባራት መካከል የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሳርያዎችን መጠቀም እንዳለባቸዉ ይገልጻል፡፡

ይህንን መሠረት በማድረግ አጥኝውም በመማር ማስተማር ሥራ ላይ እያለ በየዓመቱ በሚወጣ መምህራን መገምገምያ መስፍርት ላይ እና በዕለታዊ ዕቅድ ላይ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያን ይጠቀማሉን? የሚል ይዘት ስላለ ይህንን በመመልከቱ ይህ የትምህርት መርጃ መሣርያ ከሌሎች ጉዳዮች ይልቅ ትልቅ ትኩረት የተሰጠበት ዋና ምክንያት ምን ይሁን?የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀምስ ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎች ወደ አህምሮው መተዋል፡፡ ‹‹የቋንቋ መምህራን በተለያዩ መርጃ መሳሪያዎች በመገልገል የተማሪዎችን ትኩረት በመሳብ የተለያዩ የቋንቋ ክህሎትን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸዉ፡፡››በማለትም ያብራራል Aggarwal (1996:153)፡፡

በተጨማርም በድሉ (1996፡63-64) መምህራን በንግግር ተግባራት ጊዜ ማድረግ ከሚገባቸዉ ተግባራት መካከል የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሳርያዎችን መጠቀም እንዳለባቸዉ ይገልጻል፡፡

ይህንን መሠረት በማድረግ አጥኝውም በመማር ማስተማር ሥራ ላይ እያለ በየዓመቱ በሚወጣ መምህራን መገምገምያ መስፍርት ላይ እና በዕለታዊ ዕቅድ ላይ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያን ይጠቀማሉን? የሚል ይዘት ስላለ ይህንን በመመልከቱ ይህ የትምህርት መርጃ መሣርያ ከሌሎች ጉዳዮች ይልቅ ትልቅ ትኩረት የተሰጠበት ዋና ምክንያት ምን ይሁን?የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀምስ ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎች ወደ አህምሮው መተዋል፡፡ ለሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት ጅማ ዩኒቨርቲ ከገባበት ጊዜ ጀምሮም በተለያየ ኮርሶች (ስነ ዘዴ ነክ የሆኑ ኮርሶች) ስለ ትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀም አጤንተአል፡፡ በእነዚህ እና በመሣሠሉት ጉደዮች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን በመታገዝ ማስተማር የተማሪዎችን ችሎታ ከማጎልበት ረገድ ያላዉን ሚና ምን ይሆን ? መምህራን የትምምህርት መርጃ መሣርያ ስጠቀሙ የሚያጋጥማቸው ችግሮች ምን ሊሆን ይችላል? የሚለዉን ጥያቄዎች ለመፈተሽ አጥኝው ተነሳስተዋል፡፡ በዚህ መሠረትም ጥናቱ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎችን ይመልሳል ተብለዉ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መራጃ መሣርያዎች አጠቃቀምን በመፈተሽ በምልከታ፣በቃለ መጠየቅና የጽሑፍ ጥያቄዎችን ለመምህራን ከቀረበ በኃላ ለሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጠዋል፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ምን ይመስላል?

2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያ ሲጠቀሙ የሚያጋጥማቸዉ

እንቅፋቶች ምንድርናቸው?

3 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀም ያላቸዉ ግንዛቤ ምን ይመስላል?

4.የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያን ለመጠቀም ያላቸዉን ፍላጎት እንደት ነው?

## 4.የጥናቱ ዓላማ

### 1.4.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በምስራቅ ወለጋ ዞን፣በጅማ አርጆ ወረዳ ሦስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህረት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የትምህረት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀም መፈተሽ ነዉ፡፡

### 1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀም ምን እንደሚመስል መዳሰስ፣
- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በትምህረት መርጃ መሣርያዎች ሲጠቀሙ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ካሉ መለየት፣
- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀም በተመለከተ ያላቸዉን ግንዛበ መዳሰስ፣

➢ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያን ለመጠቀም ያላቸዉን ፍላጎት መለየት የሚሉ ናቸው፡፡

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

❖ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም እንዲረዱ የሚያመለክት መረጃ ይሰጣል፡፡

❖ ከጥናቱ ዉጤት ከሚሰጡት አስተያየቶችና የመፍትሔ ሓሳቦች በመነሳት የትምህረት መርጃ መሣርያዎችን አጠቃቂም እንድገነዘቡና ትኩረት እንድሰጡ ያደርጋል፡፡

❖ በዚህ ርዕስ ዙሪያ ጥልቅ ምርምር ማድረግ ለሚሹ ባለሙያዎች ተጨማሪ መረጃ ይሰጣል፡፡

❖ ለአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍት አዘጋጆች ፍንጭ ይሰጣል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ ከቦታና ከትምህርት ቤት አንጻር ትኩረት ያደረገዉ በኦሮሚያ ክልል፣በምስራቅ ወለጋ ዞን፣በአርጆ ወረዳ ከሚገኙ አምሳ አንድ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሦስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ‹‹የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀም ፍተሻ ››በሚል ርዕስ ላይ በ2013 ዓ.ም የተሠራ ጥናታዊ ምርምር ነዉ፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

አጥኚዉ በተቻለዉ መጠን ለጥናቱ ከፍተኛ ተነሳሽነት ቢኖረዉም ትምህርት እርከናዊ ወይም ተዋረዳዊ በሆነ መልኩ ስለሚሰጥ የሌሎችን የትምህርት አይነቶችና በተለያዩ ክፍል ደረጃዎች የሚገኙትን የአማርኛ ቋንቋ መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀም እና አዘገጃጀት አላካተተሚ፡፡

ሌላው ውስንነት መረጃ ለመሰብሰብ በቂ የሆኑ መረጃ ሰጪዎች አስፈላጊ ቢሆንም ተጠኚዎቹ በአርጆ ወረዳ ከሚገኙት አምሳ አንድ ትምህርት ቤቶች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ በየትምህርት ቤቶቹ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በቁጥር አነስተኛ

መሆናቸው ውስንነቱን ያሳያል፡፡ከዚህ በተጨማሪ በክፍል ደረጃ ያለውን ልዩነት ለማየት ሲባል ይህ ጥናት የተካሄደው በሁለት የክፍል ደረጃዎች ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ላይ ጥናቱ አለመካሄዱ ሌላው ውስንነት ነው፡፡

## 1.8 የቁልፍ ቃላት እና ሐረጋት ፍቺ

በእንግልዘኛ በአማርኛ

Awudiovisual Aids (የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መረጃ መሣርያ)

Autentic(ኑባራዊ)

DrawingsoundDistirubutionsystem sets (ንድፎች)

Interaction (መስተጋብር)

Real (ዕዉነተኛ)

Simplicty (ቀላልነት)›

Principlles of selection (የአመራረጥ መርሖች)

Specific educational valus (የተለዩ ትምህርታዊ እሴቶች)

Variabils (ተላዉጦዎች)

Awudio (የሚደመጥ)

Classiification (ክፍፍል)

Simulation (ማነቃቀያ)

Demonestiration (ለዕይታ የቀረቡ መረጃዎች)

Study trip (ጥናታዊ ጉዞ)

APPropriates (ተስማምነት)

Clarity (ግልጽነት)

Focus of attention (ትኩረት)

Natural integration (ተፈጥሮአዊ ቅንጅት)

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2. መግቢያ

በምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ፣ መነሻ ችግር፣ ዓላማ፣ መሰረታዊ ጥያቄዎች፣ አስፈላጊነት፣ ወሰንና ውስንነት ተብራርተዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የጥናቱን ንድፈሃሳባዊ መነሻ ከተለያዩ የመማር ንድፈሃሳቦች አንጻር፤ የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ምንነት፣መምህራን ለምን የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን እንደምጠቀሙ፣ ስለሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም፣ስለሚደመጡና ስለሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም፣ለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መምረጥ የሚውሉ መመዘኛዎች፣ስለ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ባሕርያት፣ስለ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም፣ የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን ለማቅረብ (ለማሳየት) ያለዉ መርሐ፣በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቀቀም ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች፣የቋንቋ ትምህርትን በትምህርት መርጃ መሣሪያ ለማስተማር የመምህራን ተግባር፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች በመርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም ያላቸው እገዛ እና የቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ተብራርተዋል፡፡

## 2.1 የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ምንነት

የተለያዩ ምሁራን የትምህርት መርጃ መሣርያዎን በተለያየ ስያሜዎች ይጠሩታል፡፡ የማስተማርያ መገናኛ ብዙሃን፣የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣርያዎች፣ የመማሪያ ምንጮች(Learnig resource) የሚሉት ምሁራን ለትምህርት መርጃ መሣርያዎች ከሰጡት ስያሜዎች ዉስጥ ጥቅቶቹ ናቸዉ Nkuuhe(2000:224) Quist(2000 ፣27)፣Aggrwal (1995፣157)፣Romiszowski (1988፣7) እና Harrison ( 1995፣28)፡፡

የትምህርት መርጃ መሣርያዎች የሚለዉ ጽንስ ሐሳብ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ በተለያ መንገድ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ለየትኛዉም ደረጃ ፣በሁሉም የትምህርት ዓይነትና የትምህርት መስኮች፣ በመምህራንና በተማሪዎች ዘንድ በመማር-ማስተማር ሒደት የዋሉትን ፅንስ ሐሳቦች ሁሉ ያጠቃልላል Nkuuhe (2000፣224)፡፡ Nkuuhe (2000) አያይዘዉ የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ሲባል የህቴመት ዉጤቶች ፣ሞደሎችን፣እዉነተኛ ነገሮችን፣(Real object )

የኤሌክትሮንክስ መገናኛ ብዙሃንና የተለያ ሰለዳዎችን በአጠቃላይ የመማር-ማስተማር ሂደቶች አጠቃላይና ዝርዝር የትምህርት ዓላማዎች ከግብ ለማድረስና የትምህርት ይዘቶችን በተጨባጭ ለማብራት አገልግሎት የሚውሉ የትምህርት አጋዥ መሣርያዎች (Devices) መሆናቸዉን ያስረዳሉ፡፡

Hcinichctal (1996፡8) በበኩላቸዉ ‹‹የትምህርት መራጃ መሣርያዎች ተማሪዎች ትምህርታዊ ይዘቶችን /ዕዉቀት ፣ክሂልንና አመለካከትን/ ከተለያዩ ምንጮች እንደምያገኙ የሚያግዙና ትምህርታዊ ዓላማዎችን ሰኬታማ የሚያደርጉ መሣርያዎች ወይም ቁሳዊ አካሎች ናቸዉ፡፡››ይላሉ፡፡

Harrison (1995፡28) ደግሞ የትምህርት መርጃ መሣረያዎች በትምህርት አቀባበል ላይ ፈርሃትን፣ጭንቀትን ወይም መረበሽን የሚያስወግዱ ፣የንባብና ለሎች ክሂሎት ተማሪዎች እንድያሻሽሉ የሚያግዙንና አንድን ኪሂል ፣ዕዉነታ ወይም ሐሳብ የሚያጎሉና የሚያዳብሩ ናቸዉ ፡፡በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከላይ ከቀረበዉ የምሁራን ሀሳብ እንደምንገነዘበዉ የትምህርት መርጃ መሣርያዎች አንድን የትምህርት ይዘት ተጨባጭ በሆነ መልኩ በማቅረብ ዓላማን በተገብ መንገድ ለማስፈፀም የሚያስችሉ የተለያዩ አጋዥ ነገሮች የምደመጡ እና የሚዳሰሱ ናቸዉ ማለት ይቻላል ፡፡

## 2.2 መምህራን ለምን የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን ይጠቀማሉ?

የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን አግልግሎት በተመለከተ የተለያዬ ምሁራን የተለያዩ አስተያየቶችን ሰጥተዋል፡፡ Harmer( 2001:134 ) እንደሚሉት የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ለተግባራዊ ልምምድ ብሎም የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማነሳሳት ያገለግላል፡፡ እንደ Quist (2000፡104) አገላለጽ ፣የትምህርት መርጃ መሣርያዎች የጽንስ ሐሳቦችን ምንነት በቃል ብቻ ከማብራራት የዕንስ ሐሳቦችን ግልጽ ለማድረግ የሚያስችሉ ተገብነት ያላቸዉ ዉክልናዎች በማቅረብ ረገድ ለተማሪዎችም ሆነ ለመምህራን ዕገዛ አላቸዉ፡፡ ለተማርዉም በቀላከሉ የመማር ልምድ እንድያካብቱ ያስችሉታል፣ለመምህሩም ረቂቅ የሆኑት የትምህርት ይዘቶችን ተጨባጭና ዕዉናዊ በሆነ መልኩ ግልጽ እና ቀለል አደርጎ ለማቅረብ ይረዳል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ Nkuuhe (2000፣226) የትምህርት መርጃ መሣርያዎች የጎላ ጠቀመታ እንዳላቸዉ ሲገልጹ ፣ከስነ ትምህርታዊ ስነ- ልቦና (Educational psychology ) ጋር ያያይዙታል፡፡

ይኸዉም እያንዳንዱ ሰዉ የሚማረዉን  በስመት ሕዋሳቱ (በአፍንጫ በማሽተት፣በዐይን በመመልከት በምላሱ በመቅመስ ፣በአንደበቱ በመናገር ፣በጆሮዎቹ በማዳመጥ እና በእጆቹ በመዳሰስ) የተለያዩ መረጃዎችን በመሰብሰብ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡

በትምህር መርጃ መሣርያዎች ለምን መጠቀም እንደሚያስፈልግ nkuuhe (2000፣226) ሲያብራሩ ፣

- ✓ አንድ ሂደት ወይም ቴክኒክ በተጨባጭ እንድታይ ያደሩጋል፣
- ✓ የቋንቋ መማር -ማስተማር ሂደት የተሳካ እድሆን ያግዛሉ፣
- ✓ የተማርዎችን ትኩረት በመሳብ የመማር ፍላጎት ያነሳሳሉ፣
- ✓ የጽንሰ ሐሳቦችን ዕዉነታ እንዲረዱ ያደርጋል ፣
- ✓ የተማርዎችንም ሆነ የመምህራኒኒ  የፈጠራ ችሎታ ያሳድጋሉ፣
- ✓ በቡድናዊም ሆነ በግላዊ የመማር ልምድን ያጎለብታሉ፣
- ✓ ተማርዎች በዋና ዋና የትምህርት ይዘቶች ወይም ቁልፍ ሓሳቦች ላይ ትኩረት እንድያደርጉ ያስችላሉ፣
- ✓ የአድስ ቃላትን ትርጉም ለመረዳት ስለምያስችሉ ለትርጉም ፍለጋ የሚባክነዉን ጊዜ ይቆጥባል፡፡ይላል፡፡

በአጠቃላይ የአንድን ድርጊት ወይም የአንድን ነገር ተከተላዊ ሂደት በተማሪዎች አዕምሮ ዉስጥ ምናባዊ ምስል በመፍጠር ሓሳቡ በአእምሮ እየተደጋገመ እንድመጣ ያደርጋሉ፡፡ይህም ተተኳር የትምህርት ይዘቱን ተጨባጭና አይረሴ ያደርጋል የሚሊ አንደምታ አለዉ፡፡

በተጨማርም የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን የመጠቀም ምክንያት ሲገልፁ፣ረቂቅ የሆኑ የትምህርት ሐሳቦችን በተጨባጭ በማቅረብ ተማሪዎች ያለ ምንም ችግር የትምህርት ይዘቶችን እንድረረዱና የተማርዎችን የማስታወስ ችሎታ በማፋጠን ተማሪዎች ከአከባብያቸዉ ጋር መስተጋብራዊ ግኑኝነት እንድያደርጉና አከባብያቸዉን እንድወዱ እንድሁም፣ እንድያደንቁ በማገዝ ተማሪዎች ከሂሎትን ለምሳሌ፣የማዳመጥ ፣የምልክት ወይም በእጅ

የመጠቀም፣የመገጣጠም፣ችግር የመፍታት ፣አብሮ የመስተራት ልምዶችን እድያዳብሩና የመማሪ ጉጉት በመቀስቀስ ለመማር የሚኖራቸዉን መነሳሳት በመጨመር፣በተማሪዎችና በመምህራን ዘንድ ፈጠራን ለመቀስቀስ ፣ መምህራን የሚያቀርቡአቸዉ የትምህሪት ይዘቶች ለተማሪዎች ተአማኒ (እዉነተኛ)፣ተገብ እና ትርጉም ያላቸዉ እንድሆኑ ያስችላሉ (Malawi Instiute of Education 20003)::

ከላይ በቀረበዉ ገለፃ መሠረት በትምህርት መርጃ መሣርያዎች በመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ መጠቀም እጅግ በጣም ጥሩ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡በመሆኑ የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን በመጠቀም ትምህርቱን ቀላልና ግልጽ በሆነ መንገድ ለማቅረብ ፣የመምህሩንም ሆነ የተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታን በማጎልበት ፣በመምህሩንና በተማሪዎቹ ወይም ተማሪዎች እርስ በእርሳቸዉ ጥሩ መስተጋብር እንድኖራቸዉ እገዛ በማድረግ ጉልበትንና ጊዜን ከመቆጠብ አንፃር የጎላ ድርሻ አላቸዉ፡፡ትምህርቱንም ለተማርዎች ስሜት በሚያመች መንገድ ለማቅረብና ለተማሪዎቹ ትምህርቱን ከስመታቸዉ ጋር ተጨባጭ በሆነ መልኩ አቅልሎ ለማቅረብ ያስችላል፡፡

በአጠቃላይ በየትኛዉም ደረጃ እና በየትኛዉም የዕድሜ ክልል የትምህረት መርጃ መሣርያዎችን መጠቀም የጎላ ጠቀመታ እንዳለዉ መረዳት ይቻላል Grant (1987፡18)፡፡ ‹‹ተማሪዎች በተለያዩ ተግባራት ከተሳተፉ ተግባቦትን በተገብ ሁነታ ያቀላጥፋሉ ››ይላሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዜ Wong (1998፡168) በቋንቋ የመማር -ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ተምረዋል የሚባለዉ በተለያዩ ተግባራዊ ክንዉን የተማሩ እንደሆነ ነዉ፡፡ጥሩ የቋንቋ መምህረም ተማሪዎች በተሳትፎ የበለጠ የሚማሩበትን መንገድ ለመለየት አብዛንኛ ጊዜ በተግባር ክንዉኖች በማሳተፍ ተግባቦታዊ በሆነ ዘዴ ተፈጥሯአዊ ወደ ሆነዉ የቋንቋ አጠቃቀም እድያዘነብሉና እንድሳተፉ የሚያግዚ ስሰሆነ ነዉ፡፡ ‹‹የቋንቋ መምህራን በተለያዩ መርጃ መሳሪያዎች በመገልገል የተማሪዎችን ትኩረት በመሳብ የተለያዩ የቋንቋ ክህሎትን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸዉ ፡፡››ይላሉ ምሁሩ፡፡

## 2.3 የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

Aggarwal (1996፡157)፣ Wright (1989፡4) እና Bowen (1982፡6) እንደሚገልፁት፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የቋንቋ ትምህርትን በማገዝ ረገድ ቀዳሚውን ሥፍራ ይይዛሉ፡፡ Aggarwal (1996:157) ዋቢ አድርገው እንደጠቀሱት የሰብዓዊ መብት ተሟጋችና ፀሐፊ Desiderious Erasmus (1466-1536) በዘመኑ የነበረውን ቃላዊና በሽምደዳ ላይ ያተኮረ

የትምህርት አሰጣጥን  በመቃወም ሕፃናት በሥዕሎችና በሌሎች የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ መማር እንዳለባቸው በይፋ ማወጁ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የጎላ ድርሻ ያሳያል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ እኒህ ምሁር በጥናታቸው የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ፋይዳ በቀዳሚነት John Amos Comenius (1592-1670)  የተባሉ ምሁር ("Sensulium pictus") በእንግሊዝኛው "The world sense objects" በመባል የሚታወቀው 150 ሥዕሎችን ያካተተ የመማሪያ መጽሐፍ እንዳዘጋጁና ሥዕሎችም በዕለት ተዕለት የሕይወት እንቅስቃሴ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ይህ የመጀመሪያው በሥዕል የተደገፈ የሕፃናት መማሪያ መፅሐፍ ተደርጎ ሊቆጠር እንደሚችልና መጽሐፉም በመላው ዓለም በሚገኙ የትምህርት ማዕከሎች ሰፊ ስርጭት አግኝቶ አገልግሎት እንደሰጠ አክለው ይገልፃሉ፡፡ ሥዕላዊ መግለጫዎች በመማር -ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪውን ስሜትና ፍላጎት ከመቀስቀስ ባሻገር ቋንቋውን የመድበለ ቃላት ዕውቀቱ ከማጎልበትና በቃላትና በሐረጋት ዓረፍተ ነገሮችን ከመመሥረት አንፃር ጥሩ ልምምድ ለማድረግ እንደሚያስችሉት Nunan (1991:136) የሥዕላዊ መጽሐፎችን ፋይዳ በሚገልፁበት አባባል ሐሳቡን አጠናክረውታል፡፡

እንደ Wright (1989:136) ገለጻ፣ ሥዕሎች የተማሪዎችን የማዳመጥና የማንበብ ክሂሎች ለማዳበር ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በተለይ ይህን በተመለከተ ሁለት ምክንያቶች አሉ፡፡ በመጀመሪያ ከቃላት የሚወጡት ትርጉሞች በሥዕሎች ውስጥ በሚገኙበት ዓውዳዊ አገባብ ላይ ይወሰናሉ፤ ወይም ሥዕሎች የተለያዩ አውዶችን በመፍጠር በክፍል ውስጥ ለማስተማር ላቅ ያለ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ብዙ ጊዜ ተማሪዎች ለሥዕሉ ኢ-ንግግራዊ በሆነ መልኩ ምላሽ ቢሰጡ መልካም ነው፡፡ ሥዕሎቹ ኢ-ንግግራዊ ምላሾችን እንዲሰጡ በማድረግ ረገድ ጥሩ ዕድል ይሰጣሉ በማለት ይገልፃሉ፡፡

ተስፋዬናማረው(1993፣63)እንዳሠፈሩት፣ በክፍል ውስጥ የሚከናወን የማዳመጥ ትምህርት በሥዕላዊ መግለጫዎች፣ በካርታዎች፣ በቅርፃ ቅርፃች፣ በምሥሎች፣ ወዘተ. አማካይነት ድጋፍ መስጠት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ እንደነዚህ ዓይነት የድጋፍ መስጫ መሣሪያዎች የማዳመጥን ክሂል ለማስተማርና ትርጉማዊ ለማድረግ አጋዥነታቸው የጎላ ነው፡፡

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አገልግሎት በተመለከተ Bowen (1982:IV)፣መማር ውስብስብ ሂደት እንደሆነ ጠቁመው፣ ይህን ውስብስብ ሂደት በሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም ቋንቋን በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎችን እንደሚያነሳሳ ይገልፃሉ።

በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተማሪዎችን ለመማር ማነሳሳት ብቻ ሳይሆን፣ የትምህርቱን ይዘት በቀላሉና በተጨባጭ መልኩ እንዲገነዘቡት እንደሚያግዟቸውም ያብራራሉ።

ንባብን ከማስተማራቸው በፊት ጽሑፎችን በጥንቃቄ መምረጥ ያስፈልጋል። ተገቢ ንባብን ለመምረጥ በቅድሚያ የንባብ መምረጫ ነጥቦችን ማወቁ ተገቢነት አለዉ። አንድ ንባብ ስመረጥ ሊያሟላ የሚገባ መመዘኛዎች ብዙ ናቸዉ። ከነዚህም መካከል የሚመረጠው ምንባብ በካርታ ፣በግራፍ፣ በሠንጠረዥና በሥዕላዊ መግለጫዎች ቢደገፍ ለተማሪዎች ተገቢ፣ ጠቃሚና ቀላል እንዲሆን ለማድረግ የጎላ ጠቀሜታ አለው።

በጥንቃቄ የተመረጠ ጽሑፍ ደግሞ በተገቢው መንገድ የሚተላለፈውን መረጃ በቀላል ሂደት ለመውሰድ ያስችላል። የንባብ ፍጥነትንም ያጎለብታል Nuttall (1982:25)።

በሥዕል፣ በፍቶግራፍ፣ በሠንጠረዥና በቻርት መሰል በሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አስደግፎ ቃላትን ማስተማር በመካከለኛ የክፍል ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች የቃላት ፍቺ ግልፅ እንዲሆንላቸው እየተመለከቱ ትምህርቱን መከታተል ይኖርባቸዋል Wallace (1992፡42)፣ Grains and Redman (1986፡76)እና Allen (1983:7)።

ከዚህጋር በተያያዘ ለተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ከማስተማር ይልቅ በሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመጠቀም ተማሪዎች የቀደመ ዕውቀታቸውን መሠረት አድርገው የቃላትን ቅርፅ (የትኛው ከየትኛው ቃል ጋር አብሮ ሊገባ እንደሚችል) በመመርመር ራሳቸው ፈልገው እንዲያገኙ እንደሚያስችሉ Harmer (2001:161) ይገልፃሉ።

በድሉ (1996፣63-64) እንደሚገልጹት፣ ንግግር የተለያዩ ንዑሳን ተግባራትን የያዘ ሂደት እንጂ በአንድ ውስን ጊዜ የሚከናወን ተግባር አይደለም። ጥሩ ንግግር ቅድመ ዝግጅትን ይጠይቃል። ንግግር በሚቀርብበት ጊዜና ከንግግሩም በኋላ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ተግባራት

አሉ። እነዚህ ተግባራት የቅድመ ንግግር፣ በንግግር ጊዜና የድኅረ ንግግር ተግባራት ተብለው ይከፈላሉ።

መምህራን በንግግር ተግባራት ላይ ማድረግ ከሚገቸው ተግባራት መካከል በሚታዩ መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም መሆኑን ይገልፃሉ። ይህም መምህራን ተማሪዎችን የንግግር ክሂልን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሲያስተምሩ በመጀመሪያ በተግባር እንዲከውኑ እያደረጉ በማስተማር በአጭር ጊዜ በሥርዓት ንግግር የማድረግን ሁኔታ እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል። ከዓይን አፋርነት ተላቀው አድማጭን ለመሳብ በሚችል መንገድ ንግግር የማድረግ ክህሎትን እንዲያዳብሩ ለማስተማርም ያግዛል። የሕትመት ውጤቶችን በተመለከተ በድሉ (1996፡13) ሲያብራሩ፣ ጸሐፊው የሚፅፈውሕይወትን ነው። ሕይወት ደግሞ በድርጊት ብቻ ሳይሆን በቋንቋ አጠቃቀም ይንጸባረቃል።

እውነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም የአንድን ኅብረተሰብ ሐሳብ ከባህሉ ጋር አመሳጥሮ ያሳያል። ይህን በቋንቋ ክፍል ውስጥ መጠቀም ተማሪውን ካልተከለሰና ለማስተማሪያ እንዲሆን ሆን ተብሎ ካልተዘጋጀ፣ ዕውነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም ጋር እንዲገናኝ ያደርጋል።

በመሆኑም ሥነ ጽሑፍ ሆን ተብለው ለሚዘጋጁ የማስተማሪያ ጽሑፎች ጠቃሚ አጋዥ መሣሪያዎች ናቸው ይሉናል።

ይህንን ሐሳብ ተስፋዬና ማረው (1993፡26) መምህራን የተቀነጨቡ ውህድ አሃዶችን ከመጽሔት፣ ከጋዜጣና ከተለያዩ መጽሐፎች በመውሰድ አባዝተው ለተማሪዎቻቸው በክፍል ውስጥ በማደል መጠቀም የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎችን ለማጎልበት አስተዋፅኦ አላቸው። ምክንያቱም ከራሳቸው፣ ከቤተሰባቸው እና ከሕብረተሰቡ የሕይወት ገጠመኝ የተቀዱ በመሆናቸው ዕውነተኛውን የቋንቋ ዐውድ ወደ መማሪያ ክፍል በማምጣት በቡድንና በጥንድ በመወያየት የመናገርና የማዳመጥ ክሂላቸውን የተገነዘቡትን በመጻፍ፣ የጻፉትን በማንበብ፣ የማንበብ ክሂሎቻቸውን ሲያዳብር ይችላል።

በተጨማሪም ቃላትንና ሰዋስውን ለማስተማር መምህሩ ለቀረፁት የዕለት ትምህርት ዓላማ ማስፈፀሚያ ለተነደፈው ይዘት በተናጠልም ሆነ በቅንጅት ክሂሎችን እንዲሁም የተለያዩ የቃላት ዕውቀትንና የቋንቋ አጠቃቀምን ለማጎልበት የጎላ ጠቀሜታ እንዳላቸው ይገልፃሉ። የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለቋንቋ ትምህርት ያላቸው ፋይዳ ተደጋግሞ ተነሥቷል።

የሚታዩ ትምህርት መርጃ መሣርያዎችን ባሕርያዊ አከፋፈል እንደ አገልግሎታቸው Bowen (1982፡13-14) በሦስት ምድቦች ይከፍሏቸዋል፡፡እነዚህም ሥዕሎች፣ ሠሌዳዎችና ፕሮጀክተሮች ሲሆኑ በውስጣቸውም ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን እንደሚያካትቱ ምሁሩ ይገልፃሉ፡፡

በመሆኑም በሦስቱ አይነት የሚታዩ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሥር የሚካተቱትን ዝርዝር ተዛማጅ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ቀጥለን እንመለከታለን፤ እነሱም፣ ሥዕሎች፣ የግድግዳ ላይ ሥዕሎችና ቻርቶች ፣ ተከታታይ ሥዕሎች ፣ ፍላሽ ካርዶች ፣ የቃላት ፍላሽ ካርዶች ፣ የሥዕል ፍላሽ ካርዶች ፣ የሥራ ካርዶችና የሥራ ወረቀቶች ፣ ሠሌዳዎች - የማስታወቂያ ሰሌዳዎች ፣ የማሣያ ሰሌዳዎች፣ ከወፍራም ሱፍ ጨርቅ የተሰራ ሰሌዳ፣ ፕሮጀክተሮች፣ ከአናት በላይ ፕሮጀክተሮች እና፣ ሌሎች ፕሮጀክተሮች ናቸው፡፡

የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት በቀላሉ ከቦታ ቦታ ሊንቀሳቀሱ መቻላቸውና በመጠነኛ ዋጋ አብዛኛዎቹን እንደልብ ማግኘት መቻሉ አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ለመጠቀም ብዙ አስቸጋሪ አለመሆናቸው ጠቀሜታቸውን ያጎላዋል፤ ግን እንደ መግነጢሳዊ ሠሌዳዎች እና ፕሮጀክተሮች ያሉት እንደልብ ሊገኙ አለመቻላቸው በተወሰነ ደረጃ በአጠቃቀም ችግር ሊኖር ይችላል፡፡

## 2.4 የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

እነዚህ የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ድምፅንና ምሥልን አካተው የያዙ ናቸው፡፡ በመሆኑም በቋንቋው መማር-ማስተማር ሂደት ተማሪው በዓይኑ እየተመለከተ፣ በጆሮው እያዳመጠ እንዲማር የሚያስችሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ናቸው፡፡

Aggarwal (1996:153) እንደሚሉት፣ የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለተማሪዎች የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶችን ግልፅ ለማድረግ፣ ይበልጥ ለማረጋገጥ፣ የትክክለኛ ግንዛቤዎች፣ ትርጉምና አድናቆቶች ተዛምዶ ተዋሕደው መኖራቸውን ተማሪው እንዲለይ በማድረግ የሚያግዙት ተጨማሪ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ ለመምህሩም ቢሆን የማስተማር ሂደቱን ይበልጥ ተጨባጭ፣ ውጤታማ፣ አስደሳችና ትርጉም ያለው አድርጎ ለማቅረብ ያስችሉታል፡፡

እኒህ ምሁር አያይዘው በነዚህ የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመገልገል ዓቢይ ዓላማ በተማሪውና በሚቀርበው የትምህርት ይዘት መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ግልፅ፣ አስደሳችና ተጨባጭ እንዲሆን ሦስት ጎንዮሻዊ የመማር ሂደትን ማለትም ንሺ፣ ክፍፍልን (Classification) እና ማነቃቂያን (Simulation) በማሟላት ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡

Aggarwal (1996፣154) አክለው እንደሚገልፁት፣ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም በተማሪውና በሚቀርበው የትምህርት ይዘት መካከል የሚኖረውን የግንኙነት መሥመር ማጥራት ነው፡፡ በመሆኑም የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች የሚተላለፉትን መረጃዎች እንዳይረሱ በምክንያት አስደግፈው እንዲገልፁ፣ በተግባር እንዲተረጉሙ፣ ትምህርቱ ተወዳጅ እንዲሆንና ምናባዊ ምሥል ፈጥረው ከተማሩት ጋር እንዲያዋሕዱ ያደርጋሉ፡፡ በአጠቃላይ ተማሪዎች የሚያጋጥማቸውን በቋንቋ የመግባባት ክፍተት የመሙላት ኃይል አላቸው፡፡

የBurnsetal.(1999:46)፣McDonough and Shaw (1994:14) እንደሚገልጹት፣ የሚደመጡና የሚታዩ መሣሪያዎችንና «ኦዲዮቪዲዮ»እንደ Clark and Irbing (1996:63) አገላለፅ፣ የመማር-ማስተማር ሂደቱን ግልፅና ተጨባጭ ለማድረግ ተገቢ የሆነ የትምህርት መርጃ መሣሪ ያ መምረጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ተግባር በአግባቡ ሊከናወን ይገባል፡፡

አንድ መምህር መርጃ መሣሪያውን መምረጥ የሚገባው በትምህርት ቤት ውስጥ ብዙ መሣ ሪያዎች ስለሚገኙ ወይም በትምህርት ዕቅድ ውስጥ ለዚህ ተብሎ ማቴሪያሎችን በመጠቀም እያዳመጡ፣ ማስታወሻ እንዲይዙ፣ በአንድ ርዕስ ዙሪያ አጫጭር ንግግሮችን እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተቀናጀ የቋንቋ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡

የGagne, etal (1992:225) በሚደመጡና በሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ምድብ ሥር የሚካተቱ መርጃ መሣሪያዎች ለእይታ የቀረቡ መረጃዎች (demonstrations)፣ ፊልሞች፣ ከተቀዳ ድምፅ ጋር የተቀረፁ ውጤቶች፣ የድምፅ ፊልም፣ ጥናታዊ ጉዞ (study trip)፣ ቴሌቪዥን፣ ቪዲዮ ቴፖችና የመሳሰሉት እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡

## 2.5 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም

የተዘጋጀውን ዓምድ ለመሙላት ወይም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚሰጡትን ጠቀሜታ በመቀበል መሆን የለበትም፡፡ በመሆኑም አንድን ትምህርት ለማስተማር ሲያዘጋጁ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው የሚወስኑት ተጨባጭ የሆኑ ምክንያቶችን ወይም መመዘኛዎችን በመመርኮዝ ነው፡፡ከእነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚቀርጿቸው የትምህርት ዓላማዎች፣ የሚያስተምሯቸው ይዘቶች፣ የተማሪዎቻቸው ቁጥር፣ ሁኔታ፣ ደረጃና ብስለት፣ የሚመርጡት የማስተማር ዘዴ፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለመጠቀም መምህሩ ያለው ችሎታ፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የማግኘት ዕድልና በተግባር የሚታዩ ችግሮች ለምሳሌ የጊዜ፣ የኢኮኖሚ፣ የአስተዳደርና የቦታ፣ ናቸው፡፡ ይህንን ሐሳብ በማጠናከር ተስፋዬና ማሬው (1993፡12-13) እንደገለጹት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚሰጡት ጥቅም ከፍተኛ እንደሆነ ብዙ አያጠያይቅም፡፡ ይሁን እንጂ እንደ ትምህርቱ ይዘት ባሕርይ አግባብ ባላቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም ተገቢ ይሆናል፡፡ የትምህርት መርጃ መሣሪያን መጠቀም የሚገባው አንድን ትምህርት ለማብራራትና ተጨባጭ ለማድረግ የሚረዳ መሆኑ ሲታመንበት ብቻ ነው፡፡

ከነዚህ ምሁራን የምንገነዘበው በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም የሚገባው አስፈላጊነቱ በሚገባ ተጢኖ ሲታመንበት መሆኑን ነው፡፡

### 2.5.1 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የአመራረጥ መርሖ

መምህራን፣ በመማር-ማስተማር ሂደት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአጋዥነት ለመጠቀም በቅድሚያ ለየትኛው የትምህርት ዓላማ መቼ መቅረብ አለበት? እንዴትስ መቅረብ ይኖርበታል? ለነማን? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥ መርሕ መከተል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን መርሕ ተከትሎ የሚመረጡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለትምህርቱ ዓላማ ግብ-መምታት፣ ለመምህሩ የማስተማር ተግባር መቀላጠፍ፣ ለተማሪው የትምህርት አቀባበል ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ መሆናቸውን በመስኩ የተካሄዱ ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡

እንደ Aggarwal (1996:158-160) ገለጻ፣ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ሂደት ውስጥ መከተል የሚገባንን መርሕ በተመለከተ የአዘገጃጀት፣ የአመራረጥ፣ የአካላዊ ቁጥጥር፣

የአቀራረብ፣ የፍላጎት ምላሽና የግምገማ መርሕ በማለት በዝርዝር ይገልጿቸዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ለዚህ ጽሑፍ የሚስማማውን የአመራረጥ መርሕ ብቻ በመውሰድ ቀርቧል፤ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ውጤታማነት የሚረጋገጠው ለታሰበላቸው የትምህርት ዓላማ ግብ መምታትና ለሚማሩባቸው ተማሪዎች የተለያዩ ባሕርያት አመቺ ሲሆኑ ነው፡፡ በዚህም ሁኔታ የሚመረጡት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት የሚከተሉትን የአመራረጥ መርሖዎች (principles of selection) ሲከተሉ ነው፤ ከተማሪዎች ዕድሜ፣ ፍላጎት፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ዳራ፣ የክፍል ደረጃ እና ከሌሎች ባሕርያት ጋር የሚጣጣሙ መሆን አለባቸው፡፡ ስሜትን ከማነሣሣትና ፍላጎትን ከመቀስቀስ ባሻገር የተለዩ ትምህርታዊ እሴቶች (specific educational values) ያሏቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡ የሚወክሉትን እውነተኛ ነገር በትክክል መምሰል ይኖርባቸዋል፡፡ የተፈለገውን የትምህርት ዓላማ እውን ለማድረግ እገዛ የሚያሆን ይኖርባቸዋል፡፡

አንድ የትምህርት መርጃ መሣሪያ በመማር-ማስተማር ሂደት ለመጠቀም በሚመረጥበት ጊዜ ከተማሪዎቹ ዕድሜ፣ ከትምህርት ደረጃ አንጻር ያልተወሳሰበና በቀላሉ የሚረዱት ሊሆን ይገባል፡፡በተጨማሪም ከሚማሩት ተማሪዎች መካከል የተለያዩ አካል ጉዳተኞች መኖርና አለመኖራቸውን መለየት፣ ካሉ ደግሞ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ መጠቀም መቻላቸውንና አለመቻላቸውን፣ እንዲሁም የተማሪዎችን ፆታዊ ልዩነት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን አስቀድሞ ማጤን ይገባል፡፡ ጠቀሜታውም በውበቱና በሳቢነቱ የተማሪዎችን የትምህርት ፍላጎት ቀስቃሽ ብቻ ሳይሆን የተማሪዎችን ሁለንተናዊ ባሕርይ ከመለወጥ አንፃር የተለየ ሚና የሚጫወት መሆን ይኖርበታል፡፡ስለሆነም የሚመረጠው የትምህርት መርጃ መሣሪያ በተቻለ መጠን የሚወክለውን እውነተኛ ነገር ሊመስል ይገባል፡፡ የሚወክለውን እውነተኛ ነገር ካልመሰለ የትርጉም አሻሚነትን ከመፍጠሩ በላይ በተማሪዎቹ ዘንድ ተቀባይነትን ያጣል፣የመምህሩንም የማስተማሪያ መሣሪያ አመራረጥ ብቃትና የትምህርቱን ይዘት ተዓማኒነት ከጥያቄ ውስጥ ሊያስገባው ይችላል፡፡

## 2.5.2 የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥ

መምህራን በመማር-ማስተማር ሂደት የዕለት ትምህርት ዕቅድ ከማዘጋጀታቸው በፊት የትኛውን መርጃ መሣሪያ በትምህርት ዕቅድ ውስጥ ማካተት እንዳለባቸውና በሚያስተምሩበት ወቅትም በዕቅዱ መሠረት መገልገል እንዳለባቸው በበርካታ ጥናቶች የተደገፈና የሚታመንበትም ነው፡፡

ከዚህ አንፃር Irbing (1996:53) መምህራን ማጤን ያለባቸውን ነጥቦች እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ፤ የዕለት ትምህርት ዓላማንና የመርሐ ትምህርቱን አጠቃላይ ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያግዝ መሆኑን፣ ዝርዝር የትምህርት ዓላማን የሚያሳካ መሆኑን፣ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን ትምህርታዊና ባህላዊ ዳራ፣ ቋንቋውን፣ ዕድሜ፣ ፆታ፣ ፍላጎትና ቋንቋውን ለመማር የሚፈልጉበትን ምክንያት ከግምት ውስጥ ማስገባትና በተጨማሪም እንደዓይን ዓፋርነት፣ ጭንቀት ወይም ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ከሚፈጠር የመግባባት ችግር የተነሳ ትምህርቱን ሊያደናቅፉ የሚችሉ የመግባቢያ ዕክሎችን ያገናዘበ መሆኑን፤ የትምህርት ዕቅድ ሲቀረጽ የትኛውን ክሂል ለማዳበር ታስቦ እንደሆነ ያገናዘበ መሆኑንና ለዕለቱ ትምህርት የሚመረጡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እንደልብ (በቀላሉ) ሊገኙ ሊተገበሩና ከቦታ ቦታ ሊንቀሳቀሱ የመቻል (አለመቻል) ሁኔታ ሊታሰብበት የሚገባ መሆኑን በአፅንኦት አስፍረዋል።

## 2.6.1 የትምህርት መሣሪያዎችን ለመምረጥ የሚውሉ መመዘኛዎች

በመማር-ማስተማር ሂደት የተስማማ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለማግኘት የመምረጡ ሂደት ቀላልና ተገቢ የሚሆነው መመዘኛዎችን በመመርኮዝ ሲከናወን ነው። በርግጥ ምርጫውን ለማከናወን የምንጠቀምባቸው መመዘኛዎች እንደትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ ምድብና ቅርፅ ይለያያሉ። ሆኖም ግን አብዛኛዎቹን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመምረጥ የሚያገለግሉና የጋራ የሆኑት ጠቃሚነት (relevance)፣ ተስማሚነት (appropriateness)፣ ትክክለኛነት (accuracy) እና ግልፅነት (clarity) ናቸው (Farrant 1984)።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለመምረጥ የሚያገለግሉ የሚከተሉ ናቸዉ።

1 **ጠቃሚነት** (relevance)፤ የትምህርቱን ይዘት ለማቅረብ ያለው ጠቀሜታና የታሰበውን ይዘት ለማስተላለፍና የታለሙትን የትምህርት ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ያለው አስፈላጊነት፣

1 **ተስማሚነት /ከተማሪው አቅም ጋር መመጣጠኑ** (appropriateness)፣ ለተማሪዎች ልምምድና የብስለት ደረጃ ያለው ተስማሚነት ከተማሪዎች የመረዳት ችሎታ በላይና በታች አለመሆኑ፣

3 **ማራኪነት** (attractiveness)፣ ማራኪ ቀለም ያለውና ትክክለኛ ንድፍ የያዘ የተማሪዎችን ስሜት የሚያረካ፣

4 **ትኩረት** (focus of attention)፣ በተፈላጊው የትምህርት ክፍል ላይ ተማሪዎች እንዲያተኩሩ ማድረግ ጠቃሚውን የትምህርት ሃሳብ ለተማሪዎች በግልፅ የሚያሳይ (የሚያመላክት)፣

5 **መጠን** (size) ፣ ለተማሪዎች በሚገባ የሚታይ የሆነ መጠን ያለው፣

6 **ትክክለኛነት** (accuracy)፣ እውነተኛ ነገር ወይም ድርጊት የተመጣጠነ፣ ትክክለኛነት እንዲታይበት ማድረግ፣ እውነታው ያልተዛባ መሆን፣

7 **ግልፅነት** (clarity) ፣ ለሁሉም ተማሪዎች በግልፅ የሚስማማና የሚታይ መሆን አለበት፡፡ለሁሉም ክፍሎች ግልፅ የሆነና ከውስብስብነትና አደናጋሪነት የፀዳ መሆን፣

8 **ቀላልነት** (simplicity) ፣ ለተማሪዎች መረዳት የማያስቸግርና በብዙ ጭብጦችና ሐሳቦች ያልተሞላ ፣ምንጭ፡- (Farant 1984:13)

### 2.6.2 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ባሕርያት

የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለተፈለገው የትምህርቱ ዓላማ ማስፈፀሚያ የመማር-ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን ከመዘጋጀቱ፣ ከመመረጡና በአገልግሎት ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ ምን ዓይነት ባሕርይ እንዳለውና በምን ዓይነት ሁኔታ መዘጋጀት፣ መመረጥና በአገልግሎት ላይ መዋል እንዳለበት አስቀድሞ ሊጤና ይገባል፡፡ ይህንን ተግባራዊ ማድረግ ደግሞ አዋቂነት ነው፡፡እንደ Aggarwal (1996:157) አገላለፅ፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ባሕርያት እንደሚከተለው ይቀርባሉ፤

- በሙከራ የተረጋገጡ፣
- ለማጓጓዝ ችግር የማይፈጥሩ፣
- ከትምህርቱ ዓላማ ጋር የሚዛመዱ፣
- ትርጉም ሰጭና ምክንያታዊ፣
- ዋጋቸው ርካሽና ተመጣጣኝ፣

- ለዕለቱ ትምህርት አገልግሎት የሚሰጡ፣ ጊዜያቸውን የጠበቁ፣
- ተማሪዎች ሊያዩዋቸው በሚችሉበት መጠን የተዘጋጁ፣
- ለአያያዝ ቀላልና ምቹ የሆኑ፣
- ተማሪዎችን ለትምህርት የሚያነሣሡ፣
- ከተማሪዎች ዕድሜ፣ ደረጃ፣ ባህላዊ፣ ማህበራዊ ዳራና ፍላጎት ጋር የተስማሙ እና
- ለማንኛውም ለሚሠሩበትና እንዲያገለግሉበት ለታሰቡበት ዓላማ ትክክለኛ መሆን አለባቸው፡፡

## 2.6.3 የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም

በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተገቢ መመዘኛ ተጠቅሞ መምረጥ ብቻ የሚፈለገውን ዓላማ ለማሳካት ያስችላል ለማለት አያስደፍርም፡፡ የታሰበውን የትምህርት ዓላማ ለማሳካት በተገቢ መንገድ የተመረጡትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በአግባቡ በጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል፡፡

Heinichetal(1996:22)እንደሚገልፁት፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከተመረጡና ከተደራጁ በኋላ ቀጥሎ የሚመጣው ሥራ መምህራን ራሳቸው መርጃ መሣሪያውን ለማስተማር ተግባር እንዴት ይገለገሉባቸዋል? ተማሪዎችውንስ በመርጃ መሣሪያዎች በመገልገል ትምህርቱን በቀላሉ እንዲረዱ እንዴት ይመሯቸዋል? የሚሉት ቁልፍ ጥያቄዎች በመርጃ መሣሪያዎች አጠቀቀም ረገድ የሚኖረውን ሁኔታ በግልፅ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

የመማር-ማስተማሩን ሂደት እውን ለማድረግ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም በነገሮች ላይ ለሚኖረን እሳቤ እና ግንዛቤ ተጨባጭ መሰረት የሚጥሉ፣ ለግንዛቤያችን ትርጉም የሚሰጡ፣

ሐሳባችንን በተሟላ ትርጉም የሚገልፁ፣ ለቃላዊ ትምህርት በሽታ ፈዋሽ መድኃኒት እንዲሆኑ ይገልፃሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ እኒህ ምሁር የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም የሚያስገኘውን ፋይዳ Aggarwal (1996:154) በሚከተለው መልኩ ይገልፁታል፤

**1.ጤናማ የክፍል ውስጥ መስተጋብር እንዲፈጠር ማበረታታት** (Encouraging healthy classroom interaction) ቀደም ሲል ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት እንደሚያነሳሱ አይተናል፡፡ ስለዚህ በዚህ አጓጊነታቸው፣ አነቃቂነታቸውና በንቃት

የማሳተፍ ኃይላቸው፣ እውነተኛ ነገር ወካይነታቸው ወዘተ. ለመማር-ማስተማሩ ሂደት መሣካት ጤናማ የክፍል ውስጥ መስተጋብር ይፈጥራሉ፡፡

2. **ትምህርቱን በትምህርት መገናኛ ማሰራጨት** (Spread of education on a mass scale) በተለያየ አካባቢ ለሚኖሩ ተማሪዎች ቴክኖሎጅን ተጠቅሞ (ሬዲና፣ ቴሌቪዥን ወዘተ.) ትምህርትን በርቀት በአንድ ጊዜ ለማዳረስ አመች ናቸው፡፡

3. **ሳይንሳዊ እውነታዎችን ማስተዋወቅ** (Promotion of scientific temper) ትምህርትን በንድፈ ሐሳብ ብቻ ሳይሆን በተግባር ለማቅረብ ያስችላሉ፡፡ ተማሪዎች ስለአንድ ነገር ዕውነታ በቃል ከመስማት ይልቅ ሰርቶ በማሳየት ነገሮችንና ክስተቶችን በመመልከት ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ እንዲረዱት ያግዛሉ፡፡ በአጠቃላይ የመማሪያ ክፍሉ አካባቢ ለፈጠራ የተመቻቸ እንዲሆን የላቀ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡

4. **ግለሰባዊ ልዩነቶችን ማጥበብ** (Meeting individual differences) ፣በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች በመካከላቸው በተለያዩ ምክንያቶች ግለሰባዊ ልዩነቶች ይኖሯቸዋል፡፡ ለምሳሌ አንዳንዱ ተማሪ መናገር የሚወድ፣ ሌላው ለእይታ የቀረቡ ነገሮችን በማየት መማር የሚፈልግ፣ ሌሎች ደግሞ በእጃቸው በመነካካት እያደረጉ መማር የሚመርጡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህ አንፃር የተለያየ ዝንባሌ ያላቸው ተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ስለዚህ እንደፍላጎታቸው እንዲማሩ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥሩላቸዋል፡፡

5. **ግልፅነት** (Vividness) ፣የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመማር-ማስተማር ዓወድ ግልፅነት ከፍተኛ ፋይዳ አላቸው፡፡ ለምሳሌ አንድ የጥንት ታሪክ የሚያወራ ጉዳይ በጥሬ

ለማስተማርያነት ከሚቀርብ ስለጉዳዩ በተቀነባበረ ተንቀሳቃሽ ፊልም አማካይነት ቢቀርብ ሐሳቡ የበለጠ ለመረዳት ይቀላል፡፡

6. **እውነቱን እንዳለ ማቅረብ** (Realism) ለትምህርት የሚቀርቡ ይዘቶች ባሉበት ሁኔታ ያላቸው ገፅታ እንዲታይና እንዲዳሰስ ለማድረግ ያስችላሉ፡፡ ለምሳሌ ፊልሞችና ዓውደ-ርዕዮች በመጠቀም ረጅም ጊዜ የሚወስድን የንባብ ሥራ በጥቂት ሰዓታት ጊዜ ውስጥ ለመገንዘብ ይረዳሉ፡፡

የቀረበ ትምህርት ተማሪው የሚቀስመው ልምድ ቀጥተኛ፣ ተጨባጭና ቋሚ ከመሆኑ ባሻገር ትምህርቱን ተፈጥሮአዊ ለማድረግ ያስችላል፡፡

7. **በዓይነት መለያየት** (Variety)፣ በድምፃዊ ወእይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የታገዘ ትምህርት ተማሪው በአይነትና በመጠን የተለየዩ ነገሮችን በመምህሩም ሆነ በተማሪው እጅ እንዲገኝ ያስችላሉ፡፡ ይህም ማለት ተማሪውም በተገቢ መንገድ እንዲማር፣ መምህሩም እንዲያስተምር ምቹ ሁኔታዎች ይፈጥሩላቸዋል፡፡

8. **አዳዲስ ነገሮችን ለመገንዘብ** (Helping in fixing up new learning)፣ በተማሪው አዕምሮ አዳዲስ ነገሮች/ዕውቀቶችና ክሂሎች እንዲቀረፁ፣ ተቀርፀውም በተገቢው ጊዜና ቦታ በተግባር እንዲገለገሉባቸው ያስችላሉ፡፡ ምክንያቱም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የተለያዩ ተግባራትንና ልምዶችን በማቅረብ የተማሪዎችን ስሜትና ፍላጎት በማነሳሳት፣ ትኩረታቸውን ወጥሮ በመያዝ ወደሚፈለገው ግብ እንዲያመሩ ያደርጋሉና፡፡

9.**ትኩረትን ለመሳብ ማገዝ** (Helpful in attracting attention)፣ በመማር-ማስተማር ሂደት በተማሪዎች ፈላጎት ላይ የተመሰረተ የትምህርት አቀባበል ላይ ትኩረት የሰጠ ዘላቂነት ያለው አውድ በመፍጠር የትምህርት አሰጣጥ ሂደቱን ምቹና ማራኪ ያደርጋሉ፤ የመምህሩን የሥራ ጫና ይቀንሳሉ፡፡

10. **በማሰተማር መርሕ ላይ የተመሰረቱ** (Based on maxims of teaching) የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ተጠቅሞ ማስተማር መምህሩ ትምህርቱን ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ፣ ከሚታወቅ ወደማይታወቅ እና ተግባራዊ በሆነ መልኩ ለማስተማር ያስችሉታል፡፡

11. **የማስታወስ ችሎታን ይዞ የማቆየት ብቃት** (Receptivity) የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለስሜት ቅርብ ስለሆኑ (በዓይን ስለሚታዩ፣ በእጅ ስለማዳሰሱ . . .) የትምህርት ልምዶችን የማስታወስ ችሎታን ይዞ የማቆየት ኃይል አላቸው፡፡

12. **ትምህርቱን ለመያዝ፣ ለመፈተሽ ወይም የትምህርቱን ባሕርይ ለመመርመር ዕድል መስጠት** (Opportunities to handle and) manipulate**ድምፃዊ** ወእይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚቀርበውን ትምህርት ተማሪዎች በአዕምሮአቸው እንዲይዙት፣ የተማሩትን መነሻ አድርገው አካባቢያቸውን እንዲፈተሹበት እና እንዲመራመሩበት እድል ይፈጥራሉ፡፡

13. **ነፃነት** (Freedom)

ስለ መርጃ መሣሪያዎቹ በመነጋገር፣ መርጃ መሣሪያዎችን በማንቀሳቀስ፣ በመነካካት፣ በመርጃ መሣሪያዎች በመዝናናት (በመደሰትና በመሣሣቅ) ብሎም ስለመርጃ መሣሪያዎቹ አሰራር፣ ቀለም፣ ወዘተ. አስተያየት በመስጠት እንዲማሩ ለተማሪዎች ነፃነት ይሰጣሉ፡፡

በዚህ ዓይነት ስሜት ውስጥ ተማሪዎችን በማስገባት መምህራን ማሠራት ቢፈልጉ፣ ተማሪዎች ደግሞ እንዲሰሩ ቢታዘዙ ወይም የመሥራት ፍላጎት ቢኖራቸው እንደልባቸው በተግባራዊ ተሳትፎ ቋንቋውን እንዲማሩ ያደርጋሉ፡፡

14 **ለቃል ትምህርት በሽታ ፈዋሽ መድኃኒት መሆን** (Antideste to the disease of verbal instruction) በቃል የሚቀርብ ትምህርት የሚኖረውን ችግር በመቅረፍ ረገድ ተወዳዳሪነት እንደሌላቸው ያጠይቃል፡፡ በመሆኑም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የትምህርቱን ሂደት በቃል ከማቅረብ ወደ ተግባራዊ ተሳትፎ ያሸጋግራሉ፡፡ ለተማሪዎች የሚቀርበው ትምህርት ግልፅ እንዲሆንና ትክክለኛነት እንዲላበስ ያስችላሉ፡፡ ለተማሪዎች በቃል በርካታ ቃላትና ሐረጋትን ልናስተምር እንችላለን፤ ቃላትንና ሐረጋትን በቃል ብቻ ማስተማር በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ቃላትና ሐረጋትን ለማፍለቅ ቢያስችልም ተማሪዎች በቃል የተነገሯቸውን ቃላትና ሐረጋት በሙሉ በአዕምሮአቸው ይዘው መተርጎምና መጠቀም አለመቻል ችግር አለ፡፡ በዚህ ረገድ ተማሪዎች በቃል የተነገራቸውን ቃላትና ሐረጋት የመርሳት ችግር ይገጥማቸዋል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ይህን የመርሳት፣ የተማሩትን ትምህርት አስታውሶ የመጠቀም ችግር የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በመጠቀም ይቃለላል፡፡

**15. የበለጠ መነሣሣትን መፍጠር** (Best motivators) የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት የማነሳሳት ኃይል ስላላቸው ስሜታቸውን በመሣብ ትኩረታቸው ወደ ትምህርቱ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

**16. እውነተኛ የትምህርት ልምዶችን መወከል** (Vicarious experiences) አንድን አዲስ ልምድ በተለመደው የማስተማር ዘዴ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን ይህን አዲስ ልምድ ለተማሪ ማቅረብ ተግባራዊ የማይሆ ንበትን ጊዜያት ይበረክታሉ፡፡ ምክንያቱም በዚህ አዲስ ልምድ ውስጥ በርካታ ለትግበራ የሚያስቸግሩ ሁነቶች ያጋጥማሉ፡፡ ለምሳሌ አዲስ አበባ ለሚማር ተማሪ የሚቀርብለት ምንባብ «የኢትዮጵያ ብርቅዬ እንስሳት»

• መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለማስተማሪያ መርጃነት ከመጠቀማቸው በፊት መርጃ መሣሪያዎቹን በጥንቃቄ በዓይነ ሕሊናቸው መቃኘትና ስለትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ በቂ ግንዛቤ መጨበጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በሌላ አባባል የትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹን አካላዊ ገፅታም ሆነ ምንነት በመጀመሪያ ለራሳቸው መረዳት ያስፈልጋል፡፡

የሚል ሲሆን ብርቅዬ እንስሳት ወደሚገኙበት ቦታ ተማሪውን ወስዶ በአካል ለማሣየት ሁኔታዎች ላይፈቅዱ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለችግር ደራሽ ናቸው፡፡ ማለትም የተለያዩ ብርቅዬ እንስሳትን ምስል /ሥዕል በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡

ምስላቸውን ተጠቅሞ የብርቅዬ እንስሳዎችን ምስል ተማሪዎች ከሚያነቡት ነገር ጋር አዋህደው ትምህርቱን ለመገንዘብ ይችላሉ፡፡ በዚህ ረገድ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የወካይነት ሚና ይጫወታሉ ማለት ይቻላል፡፡

## 2.6.4 የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን የማቅረብ (የማሳየት) መርሖ

Aggarwal (1996:155-156) የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም መርህ የሚሏቸው በሚከተሉት ነጥቦች ቀርበዋል፡፡

• በክፍል ውስጥ ለመማር-ማስተማር መምህራን በአጋዥነት የሚጠቀሙባቸውን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣ የአፈታት፣ የአገጣጠም፣ የአሠራርና የአጠቃቀም ቴክኒኮችን በቅድሚያ ማወቅና መሞከር መቻል አለባቸው፡፡

• የክፍሉ ተማሪዎች በሙሉ መመልከት በሚችሉበት ሁኔታና በምልከታውም የሚፈለገውን ዕውቀትና ክህሎት ለመቅሰም ያስችላቸው ዘንድ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በትክክል በሚታይ ቦታ ሊቀመጡ ይገባል፡፡ • በአጠቃቀም ጊዜ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ ጉዳት እንዳይደርስባቸው በአጠቃቀም ጊዜ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

• በትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ ላይ ሙሉ ትኩረት ለመስጠት ያመች ዘንድ በተቻለ መጠን ትኩረትን የሚሰርቁ ነገሮችን ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ • ከትምህርቱ በኋላ ተማሪዎች ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች ፈጣን መልስ መስጠትና ከዕለቱ የትምህርት ዓላማ ጋር ያለውን ተዛማጅነት ተገቢነትና የአጠቃቀም ቴክኒክ ብቃትን መገምገም ያስፈልጋል፡፡

## 2.6.5 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ሥነልቦናዊ ሁኔታ

(The psychology of using teaching aids) የትምህርት ልምዶችን ተጨባጭና አሳማኝ በማድረግ ማቅረብ ከእውነታ ጋር ያዛምደዋል፡፡ የመማር-ማስተማሩን ሂደት ውጤታማ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም ቋንቋን በመማር-ማስተማር ረገድ ለንባብ ከሚቀርበው ጉዳይ በተጨማሪ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣ ሪያዎች (ሥዕሎች፣ ፊልሞች፣ ተንቀሳቃሽ ፊልሞች፣ መቅረፀ ድምፆች፣ ትምህርታዊ ጨዋታዎች (Mockups)፣ ቴሌቪዥን፣ ወዘተ.) ከመሳሰሉት እውነተኛ የትምህርት ልምድ ውክልና ማግኘት ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የተደገፈ ትምህርት በተማሪው ዘንድ እንደ እውነታ እንዲታሰብ፣ የወከለውን የትምህርት ልምድ እውነተኛ ውክልና አምኖ እንዲቀበል በአጠቃላይ የቀረበው ትምህርት በሃቅ ላይ የተመሠረተ መሆኑን እንዲገነዘቡ ያስችላሉ፡፡ ከዐውድ ጋር ለማገናኘት የሚደረገው ጥረት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይሆንም፡፡ የመማር-ማስተማሩን ሂደት ከስሜት ሕዋሳት ጋር በማዋሐድ የተማሪውን የመማር ፍላጎት በመቀስቀስ፣ የተማሪውን ትኩረት ወደሚፈለገው የባሕርይ ለውጥ በማምጣት ረገድ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የጎላ አስተዋፅኦ እንዳላቸው ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የቋንቋውን ትምህርት ተግባቦታዊ በማድረግ ከንድፈ ሐሳብ ወደ ተግባር እንደሚያሸጋግሩም ተጠቁሟል፡፡ ከዚህ አንፃር Aggrawal (1996:157) እንደሚሉት፣ አንድ ተማሪ ከቀረበለት ትምህርት ውስጥ በተለያዩ የስሜት ሕዋሳቱ አማካይነት የሚቀስመው የትምህርት ልምድ ምን ያህሉን ለረጅም ጊዜ ለማስታወስ እንደሚጠቅመው Cubon (1969)ን በመጥቀስ የሚከተለውን አስፍረዋል፤ ከቀረቡት ትምህርቶች ውስጥ በስሜት ሕዋሳት አማካይነት የማስታወስ ችሎታ ከመቶ ስሌት ሲታይ፣በመቅመስ 1%፤ በመንካት 1.5%፤ በማሽተት 3.5%፤በማዳመጥ 11% ፤በማየት

83% እንደሚይዙ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሰዎችን የማስታወስ ደረጃ ከሚነበብ ነገር 10%፣ ከማዳመጥ 20%፣ ከሚታይ 30%፣ እና እየሠሩ ከሚናገሩት 90% የማስታወስ አቅም መፍጠር እንደሚቻል ይገልፃሉ።

ከዚህ በጥናት የተደገፈ የምሁሩ ሐሳብ በክፍል ውስጥ የሚቀርብ የቋንቋ ትምህርት በተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተደግፎ ሲቀርብ የመርጃ መሣሪያዎቹ ከስሜት ሕዋሳት ጋር ያላቸው ቅርበት የቀረበውን የትምህርት ይዘት ዝርዝር ነጥቦች የማስታወስ ችሎታ እንደሚወስን መገንዘብ ይችላል።

በመሆኑም ከስሜት ሕዋሳቶች ውስጥ ተማሪዎች በማየት የሚማሩትና የተማሩትን በረጅም የማስታወስ አቅም እንዲፈጥርላቸው ብሎም በደረጃ ሲታይ ደግሞ የትምህርቱ አቀራረብ ተማሪዎችን አሳታፊና አወያይ ከሆነ ትምህርቱን የበለጠ አይረሴ እንደሚያደርገው መረዳት ይችላል።

## 2.7.1 በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮች፣

በመማር-ማስተማር ሂደት የዘመኑ ተፈላጊ የማስተማር ዘዴ ተማሪ -ተኮር የማስተማር ዘዴ ነው። ለዚህ ደግሞ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ያላቸው አስተዋፅኦ የጎላ ነው።

ከዚህ አንፃር ተፈላጊነቱ ከቀን ወደቀን እየጨመረ ቢመጣም በአጠቃቀም ላይ የሚታዩ መጠነኛ ችግሮች ይኖራሉ።እነዚህንም Aggrawal (1996:159-161) በሚከተለው አኳኋን ይገልጿቸዋል፤

1. **የተማሪዎች ግድየለሽነት** ፣ በጥራትና በተገቢ ሁኔታ የተዘጋጁ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመማር-ማስተማር ሂደት መጠቀም የተማሪዎችን የትምህርት ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል። በስርዓት ያልተዘጋጀ፣ ግልፅ የሆነ ዓላማ ያልያዘ፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ጠቀሜታ የሌለውና የተማሪዎች ፍላጎት እንዲቀንስና እምነት እንዲያጡ ብሎም ግድ የለሽ እንዲሆኑ ያደርጋል።

2. **የገንዘብ ችግር**፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያን ለመጠቀም መምህራን የተዘጋጀውን ለመግዛትም ሆነ ለማዘጋጀት ወይንም የትምህርት መርጃ መሣሪያን በተመለከተ ሥልጠና ለመውሰድ የገንዘብ ችግር ትምህርት ቤቱ ካጋጠመው የተፈለገው የትምህርት መርጃ

መሣሪያ ላይዘጋጅ ወይም ላይገዛ ይችላል፤ በሥልጠና ላይም መምህሩ ወይም የትምህርት ባለሙያው ላይሳተፍ ይችላል፡፡

3. **የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ፋይዳ ቢስ መሆን** ፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ፋይዳቢስነት የሚከሰተው በመምህሩ ችሎታ ማነስና ግድየለሺነት ወይም ተገቢ የሆነ ምርጫ ባለማካሄድ፣ የአቀራረብና አጠቀቀም ችግር፣ በአጠቃላይ መርሕን ያልተከተለ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መረጣና አጠቃቀም የተነሳ ነው፡፡

እንደ እነዚህ ዓይነት ችግሮች ካሉ ደግሞ በመማር-ማስተማር ሂደት የምንጠቀምባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ጠቀሜታ ፋይዳ ቢስ ይሆናል፡፡

4. **የመምህራን ግድየለሽነት**፣ትምህርቱን ያለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በቃል ብቻ ማስተማር አሰልቺ፣ ጊዜን አባካኝ እና ውጤታማ ያልሆነ መሆኑን በግልፅ አምነው ሊቀበሉ ይገባል፡፡ በትምህርት መርጃ መሣሪያ አመራረጥና አጠቃቀም ረገድ ግድየለሽነት ካጠቃቸውና ሚናና ተግባራቸውን በአግባቡ ካልተወጡ የመማር-ማስተማር ሂደቱ ችግር ያጋጥመዋል፡፡

5. **የኤሌክትሪክ ኃይል ያለመኖር**፣አብዛኛዎቹ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እንደሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና ፕሮጀክተሮች ያለ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ሊሰጡ አይችሉም፡፡ የኤሌክትሪክ ስርጭት ደግሞ በገጠር ትምህርት ቤቶች እንደልብ የማይደርስበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በዚህ መንገድ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ችግር ሊከሰት ይችላል፡፡

6. **የሥልጠና እጥረት**፣የማሠልጠኛ ኮሌጆች ወይም የትምህርት ሥልጠና ማዕከላት መምህራንንና የትምህርት ባለሙያዎችን በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ረገድ ተገቢ ክሂሎት እንዲጨብጡ የማድረግ ሚና ይጫወታሉ፡፡እንደነዚህ ያሉ የትምህርት የሥልጠና ማዕከላትና የማሠልጠኛ ኮሌጆች በማይኖሩበት አካባቢ ባሉ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራንና የሚያገለግሉ የትምህርት ባለሙያዎች ሥልጠናውን የማግኘት አጋጣሚ ዝቅተኛ ይሆናል፤ ሥልጠና ባለማግኘታቸው ምክንያት በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቀቀም ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡

7. **በአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁስ የመጠቀም ፍላጎት ማነስ**፤ በአነስተኛ ወጭ የአካባቢ ሀብትን በመጠቀም በመማር-ማስተማር ሂደት በመርጃ መሣሪያ የተሟላ የመማሪያ ክፍል ሊኖር ይገባል፡፡ ነገር ግን ባካባቢ በሚታዩ ማሕበረሰባዊ፣ ትምህርታዊና ሥነልቦናዊ ምክንያቶች

የተነሳ በአካባቢ በሚገኙ ቁሳቁሶች የመጠቀም ሁኔታው ዝቅተኛ ነው፡፡ የእነዚህ ተፅዕኖዎችና ከአካባቢ የሚገኙ ነገሮችን ምንም ትምህርት እንደማይቀስምባቸው እንደዝቅተኛ ነገር መመልከት፣ ከፋብሪካ ተመርቶ ካልመጣ ወይም ውድ ከሆኑ ነገሮች ካልተዘጋጀ ጠቀሜታ ያለው ስለማይመስላቸው የመምህራንም ሆነ የተማሪዎች የስነትምህርታዊ አስተሳሰብ ችግር የአካባቢ ቁሳቁሶችን የመጠቀም አቅምን ዝቅተኛ ያደርጋል፡፡

8. **ተማሪዎች ጉብኝት** ፣የሚያደርጉባቸው ቦታዎች (የትምህርት ማዕከላት)በበቂ ሁኔታ ያለመኖር ተማሪዎች በመማር-ማስተማር ሂደት በትምህርት ቤት በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከሚቀርቡላቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ውጭ ትምህርታዊ ጉብኝት

የሚያካሂዱበት፣ የተደራጁ እና ደረጃቸውን የጠበቁ የፊልም ቤተሙከራዎች፣ የሚደመጥና የሚታይ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሙዚየም፣ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ዓውደ-ርዕዮች፣ የሥዕል ሙዚየም፣ የፎቶግራፍ ክምችት፣ ታሪካዊ መረጃዎች ወዘተ. በትምህርት ባለሙያዎች በተለያዩ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ሊዘጋጁና ለጉብኝት ሊቀርቡ ይገባል፡፡ የእነዚህ ዕጥረት ወይም ምቹነት አለመኖር በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

9. **የትምህርት መርጃ መሣሪያን በተገቢ ሁኔታ መምረጥ አለመቻል**፣የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ የመማር-ማስተማር ክንውኑን ለማፋጠን የሚያግዙ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ መምረጥ ካልተቻለ የተማሪዎችን ፍላጎት በመቀስቀስ የታለመውን የትምህርት ዓላማ ተግባራዊ ማድረግ ዓይቻልም፡፡ ስለዚህ በተገቢ ሁኔታ መርጦ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም በቅድሚያ የመማር-ማስተማር ሂደቱን ለማፋጠን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በሁለት መንገድ ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡የመጀመሪያው መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት ለተማሪዎች ግልፅ ለማድረግ የሚጠቀሙበት ሲሆን፤ሁለተኛው ተማሪዎች በንቃት ለመሳተፍ እንዲችሉ ለማድረግ የሚገለገሉባቸው ናቸው፡፡

ከትምህርቱ ጎናዊና ተዋረዳዊ ዝምድና አንፃርም የወደፊቱን የመማር- ማስተማር ሁኔታ በማሰብ መጠቀም ቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ ዛሬ ለማስተማር አገልግሎት ላይ የዋለው

የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለሚቀጥለውና በተከታታይ ለሚቀርበው ትምህርት መሠረት ሊሆን ይገባል፡፡ ለአንድ ጊዜ ብቻ ተጠቅመው ለሌላ ጊዜ እንደማያገለግል ቆጥረው በሥርዓት የማያስቀምጡ ከሆነ ከትምህርቱ ተለጣጣቂነት፣ተከታታይነትና ተዛማጅነት አንፃር የሚሰጠው ፋይዳ አይኖርም፡፡

## 2.7.2 የሥልጠና ጉዳይ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ዙሪያ

ቀደም ሲል የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት መገልገል ያለው ሥነትምህርታዊ ፋይዳ ተዳሷል፡፡ የላቀ ሥነትምህርታዊ ፋይዳ የሚኖረውም ከተቀረፀው ዓላማና ዓላማዉን ለማስፈጸም ከቀረበዉ የትምህረት ይዘት ጋር የሚጣጣሙ የትምህርት መርጃ መሣርያዎች በጥንቃቄ በመምረጥና በአግባቡ መጠቀም ሲቻል እንደሆነ ተዳሷል፡፡ ቀጣዩ ሥራ የተነደፈውን የትምህርት ዓላማ ከግቡ ለማድረስ የሚያስችሉ ተገቢ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መርጦ የመጠቀም ክህሎት እንዴት ይገኛል? የሚል ይሆናል፡፡ የጥያቄው ምላሽም «በሥልጠና»መሆኑ አያጠረጥርም፡፡

ከዚህ አንፃር Newbyetal (1996፡22)እንደሚሉት በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዙሪያ የሚሰጡ ሥልጠናዎች በንድፈ ሐሳባዊ ትንታኔ ላይ ብቻ ከሚያተኩሩ ከተግባራዊ ክንዋኔዎች ጋር ተዋሕደው ቢቀርቡ የተሻለ ውጤት ይኖራቸዋል፡፡ በተለይ በዓውደ ጥናቶች /workshops/ እና በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የሚሰጡ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ሥልጠናዎች በተግባራዊ ልምምድ ላይ ትኩረት የሰጡ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡

Betsate (2000:73)፣ Melvin (1973)ን ጠቅሰው ተግባራዊ ሥልጠና የሚያስገኘው አመርቂ-ውጤት በጥናት የተደገፈ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ እኒህ ምሁር በማስረጃነት ያቀረቡት ጥናት በኦውበርን ዩኒቨርሲቲ በተከታታይ ከሁለት ዓመታት በላይ ጥናት ተካሂዶ ነበር፡፡ ዓላማውም ለሠልጣኝ መምህራን ውጤታማ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥና አጠቃቀም ላይ ተግባራዊ የሚሆን የማስተማሪያ ስልት በመለየት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡

የጥናቱ ውጤትም ሠልጣኞቹ በገለፃና በውይይት ከሚሰጥ ትምህርት ይልቅ በኑባራዊ ተግባራዊ ልምምድ(authentic practice experiences)ይበልጥ እንደሚሳተፉ፣በንቃት እንደሚከታተሉና እንደሚተገብሩ ይገልፃል፡፡ በመሆኑም እኒህ ምሁር እንደሚያብራሩት፣ ሠልጣኞች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ ጥናታዊ ጽሑፎችን እንዲፅፉ፣የፕሮጀክት ሥራ ሠርተው ስለጥናቱ በዘገባ መልክ እንዲፅፉ፣በውነተኛ የመማሪያ ክፍል ውስጥ በተግባር እንዲለማመዱ፣

እንደሚሆን አያጠራጥርም፡፡Newby etal.(1996:263) ይህን አስመልክተው መምህራን ወደሥራ ዓለም ከመሠማራታቸው በፊት ወይም በሥራ ላይ እያሉ ሥልጠና በመስጠት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥና አጠቃቀም ክህሎት ማስጨበጥ እንደሚቻል ይገልፃሉ፡፡

እነዚህ ምሁራን አያይዘውም ሥልጠና ብቻውን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ መርጦ የሚጠቀም ሊቅ አያፈራም ይላሉ፡፡ ከዚህ ይልቅ መምህራን በሥልጠና ወቅት ያገኙትን መንደርደርያ ሐሳብ መነሻ በማድረግ በተግባር በመማር-ማስተማር ክፍል ውስጥ የተረጎሙት እንደሆነ ከራሳቸው ጋር የተዋሃደ፣ በዕለተ ተዕለት ህይወታቸው የሚጠቀሙበት ዘላቂነት ያለው ክህሎት እንደሚያጎናፅፋቸው ይገልፃሉ፡፡

## 2.8 የቋንቋ ትምህርትን በትምህርት መርጃ መሣሪያ ለማስተማር የመምህራን ተግባር፣

በቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት የታቀደውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ መምህራን ትምህርቱን ግልፅ፣ ቀላልና ተጨባጭ ለማድረግ በትምህርት መርጃ መሣሪያ መጠቀም በማስተማር በኩል ወሳኝ ሚና አላቸው፤ መምህራን በተለያዩ የመማር-ማስተማር ስልቶች ተጠቅመው ተማሪዎችን በታላሚው ቋንቋ እንዲገለገሉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህራን ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣት የመማር ማስተማር ሂደቱን የተሳካ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ Gower et al. (1983:154) ይህን ሐሳብ እንዲህ በማለት ይገልጹታል፤ የመማር ሁኔታውን ተቆጣጥረው በተማሪዎች ዘንድ መስተጋብር እንዲኖር ማድረግ የመምህራን ተግባር ነው፡፡ ተማሪዎች በቋንቋው የመግባባት ሂደትን እንዲማሩ በክፍል ውስጥ መስተጋብርን ይሻሉ፤ የመምህራን ተግባርም የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በመጠቀም ለተማሪዎች የጥንድና የቡድን ሥራዎችን መስጠት፣ መቆጣጠር፣ ማማከርና መገምገምነው፡፡

Burns etal(1999:337) ተማሪዎችን ማበረታታትና ለመማር-ማስተማር ምቹ የሆኑ የክፍል ውስጥ ሁኔታን መፍጠር እንዳለባቸው በመግለፅ በጣም ጠቃሚ ከሆኑ የመምህራን ኃላፊነቶች አንዱ የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያን መጠቀም እንደሆነ ያስረዳሉ፤ ጥሩ መምህራን ይህንን እውን በማድረግ የቋንቋውን ትምህርት ኑባራዊነት ባለው ሁኔታ ያቀርባሉ (Burns et al. 1999:536)፡፡

በክፍል ውስጥ ተማሪዎች እርስ በርስ በመወያየት ሐሳብ እንዲለዋወጡ መምህራን በተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም አለባቸው፡፡Hittleman (1988:69-70) መምህራን ከክፍል ክንውኖች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የሕትመት ውጤቶች፣(የተለያዩ መጻሕፍት፣ መጽሔት፣ ጋዜጣ) እና ታሪኮች፤ ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ማንበብ፣ የክፍል ውይይት ማድረግ፣ ንባብን ወይም ንግግርን መምራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም የቋንቋውን ትምህርት ዓላማ ግብ እንዲመታ ለማድረግ የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው ገልፀው፤ የመምህሩ ትልቅ ኃላፊነት በተግባር ሊተረጎም የሚገባው መሆኑን ያብራራሉ፡፡

ባአጠቃላይ መምህራን የክፍሉን ሁኔታ በመቆጣጠር የትምህርት መርጃ መሣሪያን በመጠቀም ጥሩ የመማር-ማስተማር ሂደት ከፈጠሩ፣ ተማሪዎች በሚገባ ቋንቋን ለተግባቦታዊ ዓላማ ያውሉታል፡፡

ተማሪዎች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ታግዘው ፍላጎታቸው ከተነሣሣ በተለያዩ የጥንድና የቡድን ክንውኖች ሲሳተፉ ተፈጥሮአዊ የሆነውን ቋንቋ ይገለገላሉ ማለት ነው፡፡ በዚህ ስልት የታላሚውን ቋንቋ ትምህርት ዓላማ ግልፅ፣ ቀላልና ተጨባጭ በሆነ መንገድ እንዲጠቀሙበት በር ይከፍታል፤ የመምህራንም ትልቁ ተግባራና ኃላፊነት ይህ ነው፡፡

## 2.9 የማስተማሪያ መሣሪያዎች በመርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም ያላቸው እገዛ

የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሣሪያዎች የምንላቸው በዚህ ጥናት መርሓ ትምህርትን፣ የተማሪን መጽሐፍ፣ የመምህሩ መምሪያን ብቻ ያጠቃለሉ ናቸው፡፡ የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሣሪያዎች የቋንቋ ትምህርት ሂደትን የተሳካ ለማድረግ የሚመሩ የትምህርት መሣሪያዎች ናቸው፡፡Nunan (1988:105) የትምህርት መሣርያዎች በቋንቋ ትምህርት ክፍልና በእውኑ ዓለም ያለውን ግንኙነት ግልፅ የሚያደርጉ እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ መሣሪያዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ የተለያዩ ቁም ነገሮችን ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ ቢሆንም እዚህ ላይ ለማየት የተፈለገው ለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚሰጡትን ትኩረትና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ለማስተማር በትምህርት መርጃ መሣሪያ ለመጠቀም ያላቸውን እገዛ ነው፡፡ ቀጥሎ የተማሪው መጽሐፍ፣ የመምህሩ መምሪያና መርሐ ትምህርቱን ለማየት ይሞከራል፣

### 2.9.1 የተማሪ መጽሐፍና የመምህሩ መምሪያ

Harmer(2001:257)፣Sheldon (1987:238)፣ Richards and Rogers (1986:25) የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የቋንቋ መማር ማስተማርን የሚመሩ፣የቋንቋ ትምህርቱን መነሻና

መድረሻውን የሚጠቁሙ፣ የተለያዩ ይዘቶችን በምሳሌ አስደግፈው የሚያቀርቡ መልመጃዎችንና የተለያዩ ተግባራትን በማቅረብ ተማሪዎችን እንዲለማመዱ የሚያደርጉ፣ በአጠቃላይ መሠረታዊ እውቀትንና የተለያዩ ጽንሰ ሐሳቦችን ለተማሪው የሚያስጨብጡ፣ ለመምህሩም ሥራ አጠቃላይ መማር-ማስተማር ሂደት እንቅስቃሴ መረጃ የሚሰጡ በመሆናቸው በጥንቃቄ ሊዘጋጁ እንደሚገባቸው ያስገነዝባሉ፡፡

በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎች የመማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍቱ በሚዘጋጁበት ጊዜ የቋንቋን ትምህርት በትምህርት መርጃ መሣሪያ አስደግፎ በማስተማር ተማሪውን በተለያዩ ተግባራት እንዲሳተፍ ትምህርቱን ቀላል፣ግልጽና ተጨባጭ እንዲሆን የሚያደርጉ መሆናቸውን በመግለፅ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

## 2.9.2 መርሐ ትምህርት፣

መርሐ ትምህርትና ሥርዓተ ትምህርት በአንዳንድ ሀገራት አንዱ አንዱን እየተካ የሚያገለግልበት ሁኔታ ይታያል፡፡ በዚህ ጥናት ግን የሚከተለውን ሀሳብ የያዘ ብያኔ ተቀባይነት አለው፡፡ መርሐ-ትምህርት ከሥርዓተ-ትምህርት በጠበበ መልኩ የአንድ የትምህርት ዓይነት ይዘቶችን ለማዋቀር በመነሻነት የሚያግዝ፣ የትምህርቱን አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች የሚያሳይ፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እና ትምህርቱ የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ የሚያመላክት እንዲሁም የትምህርትመርጃ መሣሪያዎችንና የግምገማ ስልቶችን የሚጠቁ ሰነድነው (Cunningworth 1989:22) ፣(Ur 1996:176)እና (Hutchinson 1987:65)፡፡

Widdowosen (1990:129) መርሐ ትምህርት ለመምህራን እንደመምሪያ እንደሚያገለግላቸው የተለያዩ ሥነዘዴዎችን በማሳየት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በመጠቆም የመማርማስተማር ሂደቱን እንዴት እንደሚተገብሩ፣ ለመምህራን መሪ የትምህርት መሣሪያ ሆኖ እንደሚያገለግል ያስረዳሉ፡፡

Yalden (1987፡81)፣Olshtain(1986፡79)፣Nunan (1988፡43) እንደሚሉት መርሐ ትምህርት ተማሪው ምን መማር ይገባዋል? ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ፣ የሃገሪቱን አጠቃላይ የትምህርት ፍልስፍናና የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ መነሻ አድርጎ መምህሩ ማስተማር የሚገባውን፣ ተማሪው መማር ያለበትን የሚገልፅ መሠረታዊ የቋንቋ ትምህርት ሰነድ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር መርሐ ትምህርት የአንድን ሀገር የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ ስለሚያንፀባርቅ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አደራጆች የመማሪያ መሣሪያ አዘጋጆች፣መምህራን፣ፈተና ክፍሎች

በአጠቃላይ የሚመለከታቸው አካላት የሀገሪቱን የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ ተመርኩዘው ለማዘጋጀት አስፈላጊውን መረጃ የሚያገኙት ከመርሐ ትምህርቱ ነው፡፡

## 2.8 የቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ጥናት አቅራቢ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶችን ለማየት ባደረገው ፍተሻ ስድስት የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎችን አግኝቷል፡፡በመሆኑም ከጥናቶቹ ርእስ፣ አላማ፣ የአጠናን ዘዴና የደረሱበትን ዲምዳሜ በመግለጽ፤ ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ተመሳሳይነትና ልዩነት ለመቃኘት ይሞከራሌ፡፡

- አንዱ በጌታቸው ለገሰ (1992)፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ «በአዲስ አበባ መስተዳድር ለ7ኛ ክፍል የሚተላለፈው አጋዥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሬዲዮ የቋንቋውን ትምህርት ጥራት ለማሻሻል ሊያበረክተው የሚችለው አስተዋፅኦ» በሚል ርዕስ ጥናቱን አካሂዷል፡፡

  ጥናቱ የመርጃ መሣሪያ ዓይነት በሆነው በሚደመጡ መሣሪያ በሬዲዮ ላይ የተጠና ሲሆን፣ ይህ ጥናት ግን በአጠቃላይ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመምህራን አጠቃቀም ላይ የሚያተኩር በመሆኑ በዓላማው፣ በጥናቱ አካባቢ እና በክፍል ደረጃው ይለያል፡፡
- በአበበ ዛዉደ (1997) በትምህርት ፋኩልቲ በካሪኩለምና ኢንስትራክሽን ትምህርት ሥልጠናና በሥራ ላይ ሥልጠና በወሰዱ መምህራን መካከል ባለው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥና አጠቀቀም የንፅፅር ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት ግን የሚያተኩረው አሁን በሥራ ላይ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በመሆኑ በዓላማው በጥናቱ አካባቢና በትምህርት ዓይነቱ በክፍል ደረጃው ይለያል፡፡
- በመሆኑም የጌታቸዉ ለገሰ ጥናት ትኩረት በሬዲዮ በሚደመጡ መርጃ መሣሪያ ላይ በአይነታዊ አጠናን ዘዴ የተጠና ስሆን የአበበ ዛዉደ ጥናት ትኩረት ደግሞ በትምህርት ፋኩልቲ በካሪኩለምና ኢንስትራክሽን ትምህርት ሥልጠናና በሥራ ላይ

ሥልጠና በወሰዱ መምህራን መካከል ባለው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥና አጠቀቀም  በንፅፅር የተጠና ነው፡፡ስለሆነም በጥናቱ ትኩረትና አጠናን ዘዴ፣ከመርጃ መሰብሰብያ መሣርያ እና ከጥናቱ ጊዜና ቦታ ይለያያሉ፡፡

ይህ ጥናት ደግሞ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን ብቻ የሚመለከት በመሆኑ በጥናት አካባቢ እና በአጠናን ዘዴ ይለያል፡፡ሆኖም ግን በመጠኑ ስለ ትምህርት መርጃ መሣርያ ስለምያወሱ ይመሳሰላል፡፡

- የሚቀጥለዉ ጥናት ደግሞ በBetsate (2000) በትምህርት ፋኩልቲ በካሪኩለምና ኢንስትራክሽን ትምህርት መስክ “Application of instructional materials in pre-primary school of SNNPR” በሚል ርዕስ በአይነታዊ ጥናት ዘዴ የተጠና ሲሆን ይህ ጥናት ግን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም የሚመለከት በመሆኑ በዓላማው፣ በጥናቱ አካባቢ፣በአጠናን ዘዴ እና በጥናቱ ዓይነት ይለያል፡፡
- ተከታዩ ጥናት ደግሞ በጌታቸው ኮቼ፣(2000)፣በኢትዮጵያ ቋንቋቸውና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል «በቦንጋ ከተማ አምስት የመጀመሪያ ደረጃ እርከን ትምህርት ቤቶች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በማስተማር ሂደት የቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎች እና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም» በሚል ርዕስ በቅይጥ አጠናን ዘዴ የተጠና ጥናት ሲሆን ጥናቱ የሚያተኩረው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በማስተማር ሂደት መሆኑ ከጥናቱ ጋር ስመሳሰል፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት መጨመሩ ግን ከዚህ ጥናት ይለየዋል፤ ምክንያቱም ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን ብቻ የሚመለከት በመሆኑ በጥናት አካባቢ፣በትምህርት ዕርከኑ፣በጥናቱ ጊዜ እና ቦታ ይለያል፡፡
- የመጨረሳ ደግሞ በአሰፉ ደሳለኝ፡(2001)በአድስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ መርሓ ግብር ‹‹በጎንደር ከተማ አራት አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀም ›› የምል በአፈ-ፊትነትና በኢአፈ-ፊትነት ፣በክልልና በክፍል ደረጃ ይለያል፡፡

- ሌላዉ ደግሞ ጅክሳ (2010) ዓ.ም በጅማ ዩኒቨርሲቲ ፣የትምህርት መርጃ መሣርያ አጠቃቀምና ፋይዳ የሚል በአፋን ኦሮሞ የሠራው በትምህርት አይነት፣በዓላማ እና በጥናቱ አከባብ ይለያል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ያየናቸው ቀደምት ስራዎች ከዚህ ጥናት ጋር ያሏቸው ተመሳሳይነት ማእከላዊ ጉዳያቸው ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያ አጠቃቀም ጋር የተያያዘ በመሆኑ ሲሆን፣ከዚህ ጥናት ጋር ከትኩረት አቅጣጫ አንጻር ሰፊ ሊዩነት አሏቸው፡፡ልዩነቱም ከላይ እንደተገለጸዉ የጌታቸዉ ለገሰ(1992) ጥናቱ የመርጃ መሣሪያ ዓይነት በሆነው በሚደመጡ መሣሪያ በሬዲዮ ላይ የተጠና ሲሆን፣ ይህ ጥናት ግን በአጠቃላይ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመምህራን አጠቃቀም ላይ የሚያተኩር በመሆኑ በዓላማው፣ በጥናቱ አካባቢ በጥናቱ ዘዴ እና በክፍል ደረጃው ይለያል፣የአበበ ዛዉደ (1997) በትምህርት ፋኩልቲ በካሪኩለምና ኢንስትራክሽን ትምህርት ሥልጠናና በሥራ ላይ ሥልጠና በወሰዱ መምህራን መካከል ባለው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥና አጠቀቀም የንፅፅር ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት ግን የሚያተኩረው አሁን በሥራ ላይ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም በመሆኑ በዓላማው፣በጥናቱ አካባቢ፣በትምህርት ዓይነት እና በክፍል ደረጃው ይለያል፡፡በተመሳሰዳይ የጌታቸዉ ለገሰ(1997) ጥናት ትኩረት ደግመ በሬዲዮ በሚደመጡ መርጃ መሣሪያ ላይ በአይነታዊ አጠናን ዘዴ የተጠና ስሆን የአበበ ዛዉደ ጥናት ትኩረት ደግሞ በትምህርት ፋኩልቲ በካሪኩለምና ኢንስትራክሽን ትምህርት ሥልጠናና በሥራ ላይ ሥልጠና በወሰዱ መምህራን መካከል ባለው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አመራረጥና አጠቀቀም በንፅፅር የተጠና ነው፡፡ስለሆነም በጥናቱ ትኩረትና አጠናን ዘዴ፣ከመርጃ መሰብሰብያ መሣርያ እና ከጥናቱ ጊዜና ቦታ ይለያያሉ፡፡ይህ ጥናት ደግሞ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን ብቻ የሚመለከት በመሆኑ በጥናት አካባቢ እና በአጠናን ዘዴ ይለያል፡፡ለላዉ ጥናት ደግሞ በBetsate (2000) በትምህርት ፋኩልቲ በካሪኩለምና ኢንስትራክሽን ትምህርት መስክ “Application of instructional materials in pre-primary school of SNNPR” በሚል ርዕስ በአይነታዊ ጥናት ዘዴ የተጠና ሲሆን ይህ ጥናት ግን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን

የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም የሚመለከት በመሆኑ በዓላማው፣ በጥናቱ አካባቢ፣በአጠናን ዘዴ እና በጥናቱ ዓይነት ይለያል፡፡ተከታዩ ጥናት ደግሞ በጌታቸው ኮቼ፣(2000)፣በኢትዮጵያ ቋንቋቸውና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል «በቦንጋ ከተማ አምስት የመጀመሪያ ደረጃ እርከን ትምህርት ቤቶች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በማስተማር ሂደት የቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎች እና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም» በሚል ርዕስ በቅይጥ አጠናን ዘዴ የተጠና ጥናት ሲሆን ጥናቱ የሚያተኩረው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በማስተማር ሂደት መሆኑ ከጥናቱ ጋር ስመሳሰል፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት መጨመሩ ግን ከዚህ ጥናት ይለየዋል፤ ምክንያቱም ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን ብቻ የሚመለከት በመሆኑ በጥናት አካባቢ፣በትምህርት ዕርከኑ፣በጥናቱ ጊዜ እና ቦታ ይለያል፡፡

የመጨረሳ ደግሞ በአሰፉ ደሳለኝ፡(2001)በአድስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ መርሓ ግብር ‹‹በጎንደር ከተማ አራት አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀም ›› በምል የተሠራዉ  በአፊ-ፊትነትና በኢአፊ-ፊትነት ፣በክልልና በክፍል ደረጃ ይለያል፡፡ሌላዉ ደግሞ የጅክሳ (2010) ዓ.ም በጅማ ዩኒቨርሲቲ ፣የትምህርት መርጃ መሣርያ አጠቃቀምና ፋይዳ የሚል በአፋን ኦሮሞ የሠራዉ በትምህርት አይነት፣በዓላማ በጥናቱ ዘዴ እና በጥናቱ አከባብ ይለያል፡፡

ለምሣሌ የጌታቸው ለገሰ ጥናት የመርጃ መሣሪያ ዓይነት በሆነው በሚደመጡ መሣሪያ በሬዲዮ ላይ በአይነታዊ አጠናን ዘዴ የተጠና ሲሆን፣ ይህ ጥናት ግን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችአጠቃቀም ላይ የሚያተኩር በመሆኑ በዓላማው፣ በጥናቱ አካባቢ፣በጥናቱ ዘዴ፣ በመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎች፣በጥናቱ ጊዜናቦታ፣ከጥናቱ ተተኳሪዎች እንድሁም ደረጃው እጅግ የተለዬ ነዉ፡፡

በአጠቃላይ  የቀደምት ስራዎች ከዚህ ጥናት ጋር ያሏቸው ተመሳሳይነት ማእከላዊ ጉዳያቸው ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያ አጠቃቀም ጋር የተያያዘ በመሆኑ ሲሆን፣ከዚህ ጥናት ጋር ከትኩረት አቅጣጫ አንጻር ሰፊ ልዩነት አሏቸው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ዘዴ እና አካሄድ

## 3. 1 መግቢያ

የዚህ ጥናት ዋና ኣላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያ አጠቃቀም ምን እንደሚመስል መፈተሸ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጥናቱ የተለያዩ ዘዴዎችን በመከተል ተከናውኗል፡፡ ስለሆነም በዚህ ምዕራፍ የአጠናን ዘዴ፣የጥናቱ አካላይ፣የናሙና አመራረጥ ዘዴ፣ የምርምሩ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችና የመረጃ ትንተና ዘዴ የሚሉት ርዕሰ ጉዳዮች ተብራርተው ቀርበዋል::

## 3.2 የጥናቱ ስልትና ንድፍ

ጥናቱ የተከተለዉ የአጠናን ዘዴ ዐይነታዊና መጠናዊ (ቅይጥ) በመጠቀም በገላጭ ምርምር ስልት ተተንትነዋል። መረጃዎች በመጠናዊ የመተንተኛ ዘዴዎች ከተሰላ በኋላ በቁጥር የተገለጸው ደረጃ አይነታዊ በሆነ መልኩ ተብራርተዋል። በተመረጠው ጥናት ንድፍ መሰረትም የክፍል ውስጥ ምልከታ ለሁለት-ሁለት ጊዜ በአጠቃላይ ለሃያ ጊዜ አጥኝውና እንደ ረዳት የተመረጠዉ መምህር ምልከታውን አካሂደው በስምምነት ላይ የተደረሰውን አስፍረዋል። በተጨማርም በንድፉ መሰረት አስራ-ሰባት ዝግና ክፍት የጽሁፍ መጠይቆች በጠቅላይ ንሞና ለተመረጡት አሰር መምህራን ቀርበው እንድሞሉ በማድረግ እና አስራ ስድስት ቃለ-መጠይቆች በውይይት መልክ ከተጠኝዎች ጋር ተካሂደዋል። በቃለ-መጠይቆቹ ላይ በቡድን ከተወያዩበት በሓላ የውይይቱ ሐሳብ ተጨምቀው ቀርበዋል።

## 3.3 የትምህርት ቤቱ ናሙና አመራረጥ

ምንም እንኳ በጅማ አርጆ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች አምሳ አንድ (51) ትምህርት ቤቶች ቢሆኑም ጥናቱ የተካሄደዉ በአርጆ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ በ2013 ዓ/ም በሦሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ አመች ናሙና አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ነዉ።

ጥናቱ አይነታዊና መጠናዊ ስልትን የተከተለ መሆኑ የትኛውም ትምህርት ቤት ቢመረጥ መሰራት ይችላል። ሆኖም ለአጥኚው የስራ አካባቢ ቅርብ ቢሆን ጥናቱን በቅርበት ለመከታተል፣ በጥናቱ የሚሳተፉ መምህራንና መረጃውን ለመሰብሰ ብሎም ትብብር ለማግኘት፣ የምርምር ወጭ ድጋፍ ለማግኘት በማሰብ ከወረዳው ትመህርት ብሮ ፣ ከትምህርት ቤቱና ከተጠኝ መምህራን ፍቃድ ስላገኜ አካባቢውም ሆነ ትምህርትቤቱ የተመረጡት አመች ናሙና ዘዴን በመጠቀም ነው።

በመሆኑም የተመረጡት ትምህርት ቤቶች ዘጠነኛ እና አስረኛ ከፍል ሲሆኑ፣የተመረጡት ትምህርት ቤቶችም አርጆ ሁለተኛ ደረጃ፣ጎምቦ ሁለተኛ ደረጃ እና ቁንባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነበር። እንድሁም ትምህርት ቤቶች ስመረጡ አጥኝዉ ከአምስተኛ እስከ አስረኛ ክፍል ያሉትን ታሳቢ በማድረግ በአርጆ ወረዳ ሦስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ ስላሉ እና አሁን በአንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለሚሰራና ትምህርት ቤቶቹ በአንድ ክላስተር ሲለምገኙ መረጃዎችን በበቂ ሁኔታ ማግኘት ይችላለው ብሎ ስላመነ ነዉ።

## 3.4 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

የክፍል ደረጃ ናሙና የተመረጠው በዓላማ ተኮር ናሙና ስሌትን (Purposive Sampling) በመጠቀም 9ኛ ክፍልና አሰረኛ ክፍል ተመርጠዋል፡፡ የክፍል ደረጃው የተመረጠበት ምክንያት ደግሞ በመሠረቱ የትምህርት መርጃ መሣርያ መጠቀም የክፍል ደረጃን አይወስንም፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ ግን ስለ ትምህርት መርጃ መሣርያ አጠቃቀም አስመልክተው በተለያዩ ስልጠናዎችና ውይይቶች ላይ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችም እንደሚያስፈልግ በትኩረት ስወሳ ተሰምተው አይታወቅም፡፡ እንድሁም በተመረጠው ክፍል ደረጃ በአማርኛ ቋንቋም ሆነ በሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የትምህርት መርጃ-መሣርያ አጠቃቀም አስመልክተው የተጠና ጥናት ማግኘት አለመቻሉ ነው፡፡ ነገር ግን የተሠሩ ምርምሮችን ለማየት እንደተሞከረው በአንደኛ ደረጃ አፍ መፍቻ ላይ ነው፡፡

ከላይ ከተጠቀሰው ምክንያት በተጨማሪ በክልላችን ትምህርት እቅድ መሠረት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚጀምረው ከአምስተኛ ክፍል በመሆኑ በደረጃው የሚገኙት ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን በቂና አስተማማኝ መረጃ ልሰጡ አይችሉም ተብለው ስለታመነ ዘጠነኛና አስረኛ ክፍል በአርጆ ወረዳ የሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን የምያስተምሩ መምህራን አሰፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

## 3.5 የመማርያ ክፍሎች አመራረጥ ዘዴ

የጥናቱ ዋና ትኩረት በተጠኝ ትምህርት ቤቶች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያ አጠቃቀም ሁኔታ ለመፈተሽ ስለሆነ ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት መምህራን ከሚገቡት ክፍሎች ሁለት ሁለት ክፍሎች በዕጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ በመጠቀም በጠቅላላ ሃያ ክፍሎች መርጠዋል፡፡በዚህው መሠረት የመማርያ ክፍሎች አመራረጥ በሚከተለዉ ተካዕደዋል፡፡ አርጆ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ካሉት ሃያ ሰባት(27)ዘጠነኛ(9)እና አስረኛ(10ኛ) ክፍሎች ውስጥ አስር ክፍሎች በእጣ ናሙና ተመርጠዋል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ከጎንበ ትምህርት ቤት ካሉት አስር ክፍሎች ዉስጥ አምስት ክፍሎች ስመረጡ፣ ከቁንባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግሞ ካሉት አስራ አንድ ክፍሎች አምስት ክፍሎች በእጣ ናሙና ተመርጠዋል፡፡በዚህ ዜደ የተመረጡበት ምክንያት ለሎች ክፍሎችን ታሳብ በማድረግ ከተመረጡት በቂ መረጃዎች ልገኝ ይችላል ብሎ ስላመነ ነዉ፡፡

## 3.6 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ዘዴ

በጥናቱ ዓላማ ላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረዉ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በምስራቅ ወለጋ ዞኒ በጅማ አርጆ ወረዳ በተመረጡት ሦስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መርጃ መሣርዎች አጠቃቀም ለመፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአርጆ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ አምስት ወንድ መምህራን ብቻ በማስተማር ስራ ላይ ይገኛሉ፤በጎንቦ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሁለት ወንድ ብቻ በማስተማር ስራ ላይ ሲገኙ በተመሣሣይ ሁኔታ በቁንባ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ደግሞ ሁለት ወንድ መምህራን ብቻ በማስተማር ሥራ ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማር የአርጆ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንድ ወንድ ሱፐርቫይ-ዘር በመምህራን ናሙና ተካተዋል፡፡ ሱፐርቫይ-ዘሩ በመምህራን ናሙና ውስጥ የተካተተው ለሦስቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስለምሰራና በትምህርት አደረጃጀትና ዕቅድ ሁለተኛ ዲግሪ ያለውና በቂ ልምድ ስላለው አስተማማኝ መረጃዎችን ልሰጥ ይችላል ተብሎ ታሚኖ ነው፡፡

በዚህ መሠረት በጠቅላላ ከሦሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዘጠኝ ወንዶች እና አንድ ሱፐርቫይ-ዘር በመማር ማስተማር ስራ ላይ ሲሆኑ ሁሉንም መምህራን በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጠዋል፡፡ በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ስልት የተመረጠበት ዋና ምክንያት የመምህራን ቁጥር አነስተኛ ስለሆኑ ከሁሉም መምህራን በቂና አስተማማኝ መረጃዎች ይገኛሉ ተብለዉ ስለታመነ ነዉ፡፡

## 3.7 የመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎች

ለዚህ ጥናት ተገቢ ናቸው ተብለው የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የክፍል ዉስጥ ምልከታ፣የጽሁፍ መጠይቅ እና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ የጥናቱ ትኩረት የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቀቀም በመሆኑ፣ የተሰበሰቡት መረጃዎች በሦስት ማዕዘናዊ ዘዴ እውነታውን ለማረጋገጥ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰብያ መሣሪያዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡ መረጃ መሰብሰብያዎቹም በአጥኚው ተዘጋጅተው፣ በጥናቱ አማካሪ እና ልምድ ባላቸዉ ባለ ሙያዎች ተረጋግጠዉ ተከናውነዋል፡፡ በነዚህም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተዘጋጁት መጠይቆችና ቅፆች በሥራ ጓደኞቼ አስተያየት ከተሰጠባቸው በኋላ ተገቢነታቸውና ትክክለኛነታቸው የተረጋገጠው ልምድ ባላቸዉ ሙያተኞች እና በአማካሪዬ ነበር፡፡

### 3.7.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ

ጥናቱ በዋናነት መሠረት ያደረገው ምልከታን ነው፡፡በምልከታዉ ጊዜ በመሠረታዊ ሀሳቦች ላይ በማዉጠንጠን ማለትም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን መጠቀማቸዉና አለመጠቀማቸዉን ለማወቅ፣የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያዎች ስትጠቀሙ የሚያጋጥማቸዉ ችግሮች ካሉ ለመለየት፣ስለ አጠቃቀሙ ያላቸዉ ግንዛበ ምን እንደምመስል ለመፈተሽ፣ የትምህርቱ መርጃ መሣርያ ለትምህርቱ ያለው እገዛ ምን እንደሆነ ለማወቅ የሚሉትን መሠረታዊ ጥያቀዎች ላይ በማዉጠንጠን ተካሄደዋል፡፡ ምልከታ የተካሄደዉ በተራ እጣ ናሙና አመራረጥ ስልት በመጠቀም ከእያንዳንዱ ተጠኝ ትምህርት ቤት የተመረጡትን ክፍሎች ለእያንዳንዱ ተጠኝ የክፍል ደረጃ ሁለት-ሁለት ጊዜ ምልከታ በማድረግ ተሠርተዋል፡፡ በአጠቃላይ ሃያ ጊዜ ምልከታ በማድረግ ፍተሻው ተካሄደዋል፡፡ በምልከታውም ወቅት ተጨባጭነት ያላቸው አስተያየቶችና ዳኝነቶችን ለመስጠት፣ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎችን ለመሰበሰብ፣ የDay (1990)ን ሐሳብ መሠረት በማድረግ ለጥናቱ በሚመች መልኩ ቅፆችን በማዘጋጀት የተካሄደ ሲሆን ቅፆቹም«እጅግ በጣም ጥሩ»፣«በጣም ጥሩ»፣«ጥሩ»፣«በቂ»እና«አነስተኛ»የሚሉናቸዉ፡፡

የምልከታዉ ቅፆችም ተገቢነታቸውና አስተማማኝነታቸው በጥናቱ አማካሪዎች ከተረጋገጠ በኃላ መረጃዎቹ ተሰብስበዋል፡፡ በምልከታው ጊዜ እንደ ረዳት ተደርገዉ ከየትምህርት ቤቱ አንዳንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመጨመር ጥናቱ ተካሂደዋል፡፡ መምህራኑም በማስተማር ሥነ-ዘዴ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተመረቁ በመሆናቸው ከክፍል ምልከታ የተገኘውን መረጃ አስተማማኝ ከማድረጉም በላይ በአንዳንድ ልዩነት ላይ ልስማሙ ይችላሉ ተብለዉ ይታመናል፡፡Best and Kahn (2003:225) መሠረት የሚገኘውን የመረጃ ልዩነትን ማጥበብ ተችለዋል፡፡ በክፊል ውስጥ የተካሄደዉ ምልከታዉ በ3.4.1 ላይ የተገለፀዉ መሠረታዊ ሀሳቦች ላይ በማዉጠንጠን ተካሂደዋል፡፡የምልከታውን ክስተት በቪዲዮና መቅረፀ ድምጽ አስደግፎ መሰብሰቡ የሚሰጠው የውሳኔ ሐሳብ ተጨባጭባጭነት ከማረጋገጡም በላይ አጥኚው የነበረውን እውነታ አይቶ ወዱያው ከአንዱ ዲምዳሜ ላይ ከመድረሱ በፉት የተቀረፀውን ቪዱዮና መቅረፀ-ድምጽ ደጋግሞ በማየትና በማዲመጥ ሁኔታዎችን በአግባቡ እንዲመረምር እድል እንዱያገኝ ይረደዋል፡፡አጥኝዉም ቪዱዮውን ተመሌክተውና አዲምጠው አስተያየቱን በመስጠት የበለጠ ተጨባጭ የሆነ ውሳኔ (ዲምዳሜ) ላይ እንዲደርስ ረድተዋል፡፡

የተሌያዩ የመስኩ ባሌሙያዎች Allwright (1980) ፣Mc-Donoughና Shaw (1993)፤ Gay et al (2009) በገለፁት መሠረት የቀረፃው ምልከታ ሊደረግባቸዉ የታሰቡትን ክፍሎች ሁሉ የሚያጠቃልል ሳይሆን ፍቃድ በተገኘባቸዉ ክፍሎች ላይ ብቻ የተወሰነ ነዉ፡፡በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ቀረፃው ፈቃድ ከተገኘባቸው የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በዓላማ-ተኮር ንሞና በተመረጡና ውስን በሆኑ የትምህርት ክፊሌ ጊዚያት ላይ ተከናውኗል፡፡ በቀረፃው የተወሰደት ወደ ፅሁፍ ተለውጠው በገለፃ ተብራርተው በጥናቱ ወረቀት መጨረሻ በመረጃነት በአባሪነት ቀርበዋሌ፡፡

### 3.7.2 የጽሁፍ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት የተመረጠው ሌላኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ደግሞ የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ የጽሁፍ መጠይቁም በጥናቱ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል የሚያስተምሩ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ ነው፡፡መጠይቆቹም የተዘጋጁት ከጥናቱ ዝርዝር አላማ አንጻር ነው፡፡

የተዘጋጀው የጽሁፍ መጠይቅ ሶስት ክፍሎች ሲኖሩት የመጀመሪያው የመምህራኑን ዳራ የተመለከተ ሲሆን ሁለተኛውና ሶስተኛው ክፍል ደግሞ የመምህራኑ የትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ በዝግና በክፍት ጥያቄዎች የቀረበ ነው፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያ አጠቃቀም አስመልክቶ ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢ የሆኑ ጥናቶች የተጠቀሙትን እንደሞዴል በመውሰድና ከዚህ ጥናት ጋር እንዲስማማ በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡ የፅሑፉ መጠይቅ ቅፆች የተዛመጅ ፅሑፎችን ወይም ንድፈሃቦችን መነሻ በማድረግ ተዘጋጅተዉ ተገቢነታቸውና ትክክለኛነታቸው በጥናቱ አማካሪዎች ተረጋግጠዉ መረጃዎቹ ተሰብስበዋል፡፡ በዚህም መሰረት የተዘጋጀው መጠይቆች ለአስር መምህራን ተሰራጭቶ መረጃው ተሰብስበዋል፡፡

## 3.7.3 ቃለ መጠይቅ

ቃለ-መጠይቅ አንድ ተመራማሪ መረጃ ከሚያገኝባቸው መሳሪያዎች ውስጥ ከባለ ጉዳዮቹ ጋር በግንባር በመገናኘት በቃል የሚደረግ ውይይት ነው፡፡ Flick (2006)ና Dornyei በዚህ ስልት ጥያቄዎቹ የቀረቡት በያለው (2006፡86) ሞዴልነት ተዘጋጅተዋል፡፡ መረጃውን (ምላሹን) በመቅረፀ ድምፅ በመቅዳት ወደ ጽሑፍ በመመለስ በአባሪነት ለማያያዝ ቢሞከርም በኮቨድ-19 እና ድምፀ ቀረጻ መሣርያ ይዞ ገብቶ መጠቀም አይቻልም ስለተባለ መረጃዉ በድምጸ ቀረጻ መስራት አልተቻለም፡፡

በመሆኑም ከላይ በመረጃ ሰጪነት የተገለፁት አካላት ከተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያስተምህሩ ሲሆን፣ከአርጆ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ አምስት ወንድ መምህራን፤ከጎንቦ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሁለት ወንድ መምህራን፣ከቁንባ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ደግሞ ሁለት ወንድ መምህራን እና የሦስቱ ትምህርት ቤቶች አንድ ወንድ ሱፐርቫይዘር በመምህራን ናሙና ተካተዋል፡፡መምህራኑ በዓላማ-ተኮር ንሞና ተመርጠው ቃሌ-መጠይቅ ቀርቦላቸዋል፡፡ በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡትም ተተንትኖዋል፡፡ በመጨረሻም በአባሪ ናሙና ላይ ቀርበዋል፡፡

በዚህ መሠረት በጠቅላላ ከሦሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አስር ወንዶች በመማር ማስተማር ስራ ላይ ሲሆኑ፣ሁሉንም መምህራን በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጠዋል፡፡ በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ስልት የተመረጠበት ዋና ምክንያት የመምህራን ቁጥር አነስተኛ ስለሆኑ ከሁሉም መምህራን በቂና አስተማማኝ መረጃዎች ይገኛሉ ተብለዉ ስለታመነ ነዉ፡፡

## 3.5 የመረጃ አተናተን ስልት

በጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተሰበሰቡት መረጃዎች የተተነተኑት በቅይጣዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት ነው፡፡ ምክንያቱም ከክፍል ምልከታ፣ ከመምህራን ጽሑፍ መጠየቅ እና ቃለመጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በአይነታዊ የመረጃ ትንተና ስልትና በመጠናዊ የመረጃ ትንተና ስልት ተብራርተዉና ተተንትነዉ ቅይጣዊ የመረጃ ትንተና ስልትንተከትለዋል፡፡ ተያይዞም የተገኘው መረጃ ተተርጉሞ ማብራሪያ ተሰጥቶበታል፡፡ በተጨማሪም ከአንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ የተገኘው ምላሽ ከሌላው ጋር ያለው ትስስሮሽ እየተጠና ደረጃ በደረጃ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

በመጨረሻም በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍሎች ውስጥ የተካሄዱትን የምልከታ ውጤቶች በአጋዥነት ከተሰበሰቡት ከጹሑፍ መጠይቅና ከቃለ መጠይቅ ውጤቶች በመነሣት በንዑስ ክፍል 1.2 ለቀረቡት የጥናቱ ዓላማ ጥያቄዎች ምላሽ በመስጠት ትንተና ተደርጓል፡፡ ትንተናውም መረጃዎቹ በሚያነሱት ጉዳይ ተከፋፍሎ በሠንጠረዥ ውስጥ በቁጥርና በመቶኛ ስሌት (%) ቀርቧል፡፡

# የመረጃ ትንተናና የውጤትማብራሪያ

## 4 መግቢያ

ቀደም ሲል በምእራፍ ሶስት የጥናቱን ዓላማ ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አዘገጃጀታቸውን እና የሚተነተኑባቸውን ዘዴዎች ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ እንዱሁም ለዋናው ጥናት በግብአትነት ሊያገለግሉ የሚችሉ መሰረታዊ ጉዳዮችን ለመየት የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ-መጤይቅ በጥናቱ ንድፍ መሠረት ተካሂደዋል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ ከተገኙ መረጃዎች በመነሳት የዋና ጥናቱ የውጤት ትንተና እና ማብራሪያ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ እንድመልሳቸዉ የታሰቡ መሠረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉ ናቸዉ፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ምን እንደሚመስል? በመዳሰስ ምላሽ ለመስጠት፣

2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያ ሲጠቀሙ የሚያጋጥማቸዉ

እንቅፋቶች ምን? እንደ ሆነ መለየት፣

3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀም ያላቸዉ ግንዛቤ ምን? እንደምመስል በመፈተሽ ስለ መርጃ መሳርያ አጠቃቀም ያላቸዉን ዕዉቀት በዝርዝር ለማስቀመጥ፣

4.የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያን ለመጠቀም ያላቸዉን ፍላጎት ለመዳሰስ፣

ጥያቄዎቹንም ለመመለስ በንድፉ መሠረት በሦስት ክፍሎች በመመደብ ማለትም የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም፣ የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለመጠቀም የቋንቋ ማስተማሪያ መሣሪያዎች እና የመምህራንን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃት የሚወሰኑ ተላውጦዎች በሚል ተመድቦ የክፍል ዉስጥ ምልከታ

ለዘጠነኛና አስረኛ ክፍል ሃያ ዙር ሲካሄድ፣አስራ ስድስት ቃለ መጠይቅ በሦስት ቡድን ተጠኝዎቹ ተወያይተውበታል፡፡ እንድሁም አስራ ሰባት ክፍትና ዝግ የሆኑ የጽሑፍ መጠይቆች በዓላማ ተኮር በጠቅላይ ናሙና ለተመረጡ አስር መምህራን ቀርቦላቸው መረጃዎቹ ተሰብስበዋል፡፡የተሰበሰቡት መረጃዎችም እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

## 4.1. የመረጃ ትንተና

### 4.1.1 ከክፍል ዉስጥ ምልከታ የተገኘ ትንተና

#### 4.1.1.1 የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም አስመልክተው የተገኙ ውጤቶች

በመማር-ማስተማር ሂደት ጊዜ የተማሪዎችን ፍላጎት በሚያሟላ ሁኔታ መምህራን ከትምህርቱ ዓላማዉ ጋር በቀጥታ ተዛማጅነት ያላቸዉን የትምህርት መርጃ መሣርያዎች በክፍል ዉስጥ አዘወትረዉ ይጠቀሙ አይጠቀሙ እንደሆን ለመለየት በተወሰኑ ክፍለ ጊዜያት ብቻ የክፍል ዉስጥ ምልከታ በማድረጊ የተሟላ መረጃ ይገኛል ማለት አያስደፍርም፡፡ደይ/1990፡42/ እንደገለጹት በዓመት ወይም በመንፈቀ ዓመት ከሚማሩት ክፍለ ጊዜያት ዉስጥ ቢያንስ 30%ቱ ያህልምልከታ መካሄድ እንዳለበት ይገልጻሉ፡፡ሆኖም ግን በኮቨድ-19 በሽታ ምክንያት የክፍል ዉስጥ ምልከታ የተሻለ አማራጭ ቢሆንም በቂ የክፍል ዉስጥ ምልከታ ሊደረግ አልተቻለም፡፡በመሆኑም በሦስቱም, ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ ታላሚ የሆኑ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍሎች/ለሃያ ክፍሎች/ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሲያስተምሩ በክፍል ውስጥ በመገኘት እያንዳንዳቸውን ለሁለት ሁለት ክፍለ ጊዜያት ለመመልከት ተችለዋል፡፡ በተጨማሪም ከላይ የተጠቀሰውን የመረጃ ተዓማኒነት ለማረጋገጥ የዓመቱን ትምህርት ዕቅድ በመመልከት በመንፈቀ ዓመቱ ላይ የተጠቀሱት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ጋር መጣጣምና አለመጣጣሙን ለማገናዘብ ተሞክረዋል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በአጠቃላይ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመማር ማስተማር ሂደት ጊዜ ምልከታ የተደረገባቸው ሃያ ክፍለ ጊዜያት ናቸው፡፡ ለ9ኛ ክፍል አስር ምድቦች (Sections)አስር ክፍለ ጊዜያት የክፍል ውስጥ ምልከታ ሲደረግ፣ለ10ኛ ክፍል አስር ምድቦች አስር ክፍለ ጊዜያት፣በአጠቃላይ ሃያ ክፍለ ጊዜያት ምልከታ ተካሂዷል፡፡ በዚህም መሠረት ምልከታ ከተካሄድባቸው ሃያ ክፍለ ጊዜያት መካከል መምህራን የትምህርት መርጃ

መሣሪያዎችን ለምን ያህል ጊዜ ተጠቅመዋል? የሚለው ጥያቄ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ውስጥ ቀርቧል፤

ሠንጠረዥ 4.1

**4.1.1.2 የክፍል ውስጥ ምልከታ ከተካሄደባቸው ሃያ ክፍለ ጊዜያት መካከል መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የተጠቀሙባቸው ክፍለ ጊዜያት ብዛት፣**

| ምልከታዉ የተካሄደባቸዉ የክፍሎች ደረጃ | ምልከታዉ የተካሄደባቸዉ ጠቅላላ ክፍለ ጊዜያት ብዛት | መምህራን በትምህርት መርጃ መሣርያዎች የተጠቀሙባቸዉ ክፍለ ጊዚያት ብዛት | | መምህራን በትምህርትመርጃ መሣርያዎች ያልተጠቀሙባቸዉ ክፍለ ጊዚያት ብዛት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 9ኛ | 10 | 2 | 20% | 8 | 80 |
| 10ኛ | 10 | 3 | 30% | 7 | 70% |
| ብዛት | 20 | 5 | 25% | 15 | 75% |

ከላይ በቀረበዉ ሠንጠረዥ አንድ እንደሚንረዳው በሶስቱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች በተደረገው የአስር አስር ጊዜ የክፍል ውስጥ ምልከታ በዘጠነኛ ክፍል ሁለት ጊዜ(20%)በአስረኛ ክፍል ሦስት ጊዜ (30%) መምህራኑ በትምህርት መርጃ መሣሪያ ታግዘዉ እንደአስተማሩ ያሳያል፡፡በአንፃሩ በ9ኛ ክፍል ስምንት ጊዜ (80%)፣በ10ኛ ክፍል ደግሞ ሰባት ጊዜ (70%) ያለ ትምህርት መርጃ መሣሪያ በቃል ብቻ ትምህርቱን እንደሰጡ ያሳያል፡፡

በምልከታው ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ጥራትና መጠን በተመለከተ በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በተደረገው ምልከታ በተራ ቁጥር አስራ አምስት ሥር በቀረበው ጥያቄ መሠረት እንደሚከተለው ለማሳየት ተሞክሯል፤

ሠንጠረዥ 4.3

4.1.1.3 በምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ጥራት እሰመልክቶ የተገኘ ውጤት፤

| የክፍል ደረጃ | በአግልግሎት ላይ የዋሉ መርጃ መሣርያዎች ብዛት | የ ጥ ራ ት ደ ረ ጃ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እጅግ በጣም ጥሩ | | በጣም ጥሩ | | ጥሩ | | በቂ | | አነስተኛ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ % | በቁጥር | በመቶኛ % | በቁጥር | በመቶኛ % | በቁጥር | በመቶኛ ስለት % | በቁጥር | በመቶኛ ስለት% |
| 9ኛ | 3 | - | - | - | - | - | - | 1 | 25% | 2 | 75% |
| 10ኛ | 4 | - | - | - | - | - | - | 3 | 75% | 1 | 25% |

መግለጫው የሚያስገነዝበው በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች መምህራን የተጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የጥራት ደረጃቸዉን ስንመለከት በ9ኛ ክፍል የተጠቀሙት በቁጥር ሦስት ሲሆን (75%)ቱ አነስተኛ፤1(25%)ቱ ደግሞ በቂ የጥራት ደረጃ መጠቀማቸዉ ያሳያል፣በ10ኛ ክፍል ደግሞ በቁጥር ከተጠቀሙት አራቱ(75%)በቂ፣25%ቱ በአነስተኛ የጥራት ደረጃ እንደተገለገሉ ያሳያል፡፡

በጥናቱ ምዕራፍ ሁለት 2.2.1 ላይ እንደተገለጸዉ ለትምህርት መርጃ መሣርያዎች መምረጫ የሚዉሉ መመዘኛዎች መሠረት ለተማሪዎች በደንብ የሚታይ መሆን እንዳለበት ይጠቀሳል፡፡በተጨማርም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ባሕርያት ተብለው ከተቀመጡት አሥራ አንድ ነጥቦች መካከል አንዱ፣ጥሩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በክፍል ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች በሙሉ በሚታይ ሁኔታ ሰፋ ባለ መጠን መዘጋጀት ይኖርባቸዋል ይላል፡፡በዚህም መሠረት በመማር-ማስተማር ሂደት በክፍል ምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ

የዋሉትን የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ጥራት ሲታይ ኋላ ለተቀመጡት ተማርዎች ስለማይታይ አነስተኛ እንደሆነ ማወቅ ተችለዋል፡፡

በመቀጠል ደግሞ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያዎች መጠን እና የመጠን ደረጃዉን እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ሦስት ቀርቧል፡፡ የመጠን ደረጃውም «እጅግ በጣም ሰፊና ጉልህ»፣ «በጣም ሰፊና ጉልህ»፣«በቂ»እና«አነስተኛ»በሚሉት ገላጭ ሐረጋት እድታይ ተደርጓል፤

ሠንጠረዥ 4.4

4.1.1.4 በምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠን፣

| የክፍል ደረጃ | በአግልግሎት ላይ የዋሉየቋንቋ ትምህረት መርጃ መሣርያዎች ብዛት | በአግልግሎት ለይ የዋሉ የቋንቋትምህርት መርጃ መሣርያዎች መጠን | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እጅግ በጣም ሰፍና ጉልህ | | በጣምሰፍና ጉልህ | | በቂ | | አነስተኛ | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 9ኛ | 3 | - | - | - | - | - | - | 3 | 100% |
| 10ኛ | 4 | - | - | - | - | 2 | 50% | 2 | 50% |

ከሠንጠረዥ 4፡4 እንደሚንረዳዉ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በመማር-ማስተማር ወቅት መምህራን የተጠቀሙበት የመርጃ መሣሪያዎች መጠን ሲታይ 3(100%)አነስተኛ መጠን በዘጠነኛ ክፍል ሲጠቀሙ፣በአስረኛ ክፍል ደግሞ 2(50%)በቂ፣2(50%)አነስተኛ መጠን እንደተጠቀሙ ያሳያል፡፡

በሠንጠረዥ 4.1 እና 4..2 ላይ እንደተገለጸው፣መምህራን በክፍል ውስጥ ለማስተማሪያነት የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በጥራትም ሆነ በመጠን አነስተኛ ደረጃ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠን አነስተኛ መሆንና ጎልቶ አለመታየት በተለይ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ወደ ኋላ ለሚቀመጡ ተማሪዎች ለእይታ ስለሚያስቸግረዉ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ አማካይነት ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ሊያዛባው ይችላል፡፡ያለመጠቀማቸዉ ደግሞ ትምህርቱን ተጨባጭ፣ሳብ እና ስኬታማ አያደርግም፡፡

ሠንጠረዥ ሁለት፣የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ መሣርያ አነስተኛ የጥራት ደረጃ መሆኑን ስያመለክት፣ሠንጠረዥ ሦስት ደግሞ መምህራን በክፍል ውስጥ ለማስተማሪያነት የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በጥራትም ሆነ በመጠን አነስተኛ ደረጃ እንደሆነ መረዳት ተችለዋል፡፡ኂላ ለተቀመጡ ተማሪዎች በደንብ አለመታየቱ ሊተላለፍ የተፈለገዉን መልዕክት ሊያዛባ ስችል፣ያለመጠቀማቸዉ ደግሞ ትምህርቱን ተጨባጭ፣ሳብ እና ስኬታማ አለማድረጉን መረዳት ተችለዋል፡፡

የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ መሣርያዎቹም የተዘጋጀዉ በመምህራኑ አስተባባርነት በየ ዓመቱ ተማሪዎች እድሰሩ በማድረግ የተሠራ መሆኑ፣አስፈላጊና አጋዥ ብሆንም ጥራቱ እና መጠኑ እምብዛም አጥጋብ እዳልሆኔ መረዳት ተችለዋል፡፡

የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃት፣

መምህራን በቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ ዕሙን ነው፡፡ መምህራን የቋንቋውን ትምህርት፣ ብቃት ባላቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አስደግፈው ማቅረብ ለዓላማው ስኬት ወሳኝ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የመምህሩን ችሎታ ይጠይቃል፡፡በመሆኑም የመምህራንን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃት በተመለከተ በምልከታ ጥያቄ ተራ ቁጥር አስራ ዘጠኝ ላይ የተገኘው ምላሽ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፤

ሠንጠረዥ 4.5

**4.1.1.5 የክፍል ምልከታ በተካሄደባቸው ጊዜያት መምህራን አገልግሎት ላይ በአዋሏቸው የቋንቋ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመጠቀም ብቃት፣**

| ምልከታ የተካሄደ ባቸው ክፍሎች ደረጃ | በአገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | መምህራን አገልግሎት ላይ በአዋሏቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመጠቀም ብቃታቸው | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እጅግ በጣም ጥሩ ነው | | በጣም ጥሩ ነዉ | | ጥሩ ነው | | አነስተኛ ነው | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 9ኛ | 3 | 1 | 25% | - | - | 1 | 25% | 2 | 50% |
| 10ኛ | 4 | 1 | 25% | 1 | 25% | - | - | 2 | 50% |
| 9ኛና10 ኛክፍል | 7 | 2 | 25% | 1 | 12.5 % | 1 | 12.5 % | 2 | 25% |

በሠንጠረዥ አራት ላይ እንደምታዬዉ በሦሥቱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል መምህራን ከተጠቀሙባቸው ሦሥት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አንዱ (25%) እጅግ በጣም ጥሩ፣አንድ(25%)ቱጥሩ፣ሁለት(50%)አነስተኛ የሆነ የመጠቀም ብቃት እንደተገለገሉበት ያመለክታል፡፡በተመሳሳይ መልኩ በአስረኛ ክፍል ላይ ከተጠቀሙባቸው አራት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አንዱ(25%)እጅግ በጣም ጥሩ፣አንዱ(25%)ቱ በጣም ጥሩ እና ሁለቱ(50%) አነስተኛ የመጠቀም ብቃት እንደሆነ መረዳት ተችለዋል፡፡

ከዚህም ሌላ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች መምህራን ከተጠቀሙባቸው ሰባት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሁለቱ ብቻ«እጅግ በጣም ጥሩ»በሆነ ሁኔታ የተገለገሉባቸው ቢሆንም አጠቃቀማቸው ሙሉ በሙሉ ብቃት አለው ለማለት አያስደፍርም፡፡

ይህ ደግሞ በምዕራፍ ሁለት 2.5.3 ላይ እንደተገለጸው የመምህራኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ብቃት ማነስ ሊሆን የሚችለው የመምህሩ ችሎታ ማነስ ወይም ግድየለሽነት፣የስልጠና እጥረት፣እና የትምህርት መርጃ መሣርያን በተገብዉ ሁነታ መምረጥ አለመቻል መሆኑ Aggrawal(1996:159-161)ላይ ገልጸዋል።በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመጠቀም ማስተማር ጤናማ የክፍል ውስጥ መስተጋብር እንደሚፈጥር በምዕራፍ ሁለት በ2.2.3 ላይ ተገልጿል። መርጃ መሣሪያዎች የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት በመቀስቀስ በንቃት የመሳተፍ ሀይል ይጨምራሉ። የሚቀርበውን ትምህርት እውነተኛነት ስለሚያጎላው ለመማር-ማስተማሩ ሂደት መሣካት ፋይዳ ያለው ጤናማ የክፍል ውስጥ መስተጋብር ይፈጥራሉ።ከዚህ አንፃር መምህራኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ የነበረውን የክፍል ውስጥ መስተጋብር በተመለከተ በምልከታዉ ጥያቄ ቁጥር ሃያ አምስት አማካኝነት ለመዳሰስ ተሞክሯል፤

ሠንጠረዥ 4.6

4.1.1.6 መርጃ መሣሪያዎቹ በአገልግሎት ላይ ሲውሉ የነበረው የክፍል ውስጥ መስተጋበርን፣

| ምልከታ የተካሄደ ባቸው ክፍሎች ደረጃ | መምህራን የተጠቀሙ ባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | መርጃ መሣሪያዎቹ አገልግሎት ላይ ሲውሉ የነበረው የክፍል ውስጥ መስተጋበር | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እጅግ በጣም ጥሩ ነው | | በጣምጥሩ ነዉ | | ጥሩ ነዉ | | አነስተኛ ነዉ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛስሌት(%) | በቁጥር | በመቶኛስሌት(%) | በቁጥር | በመቶኛስሌት(%) | በቁጥር | በመቶኛስሌት(%) |
| 9ኛ | 3 | - | - | - | - | - | - | 3 | 100% |
| 10ኛ | 4 | - | - | - | - | - | -- | 4 | 100% |

ከላይ በተገለፀዉ ሠንጠረዥ አምስት መሠረት መምህራን በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለማስተማር ከተገለገሉባቸው ሰባት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ውስጥ ሠባቱ (100%)«አነስተኛ»የሆነ የተማሪዎች የእርስ በርስ መስተጋብር ፈጥረዋል፡፡መስተጋብሩ «አነስተኛ»የሆነበት ምክንያት በምዕራፍ ሁለት2.1.2 ላይ እንደተገለጸዉ የትምህርት መርጃ መሣርያ ታላምዉ ትምህርት በተጨባጭ እንድታይ፣የተሳካ እንድሆን፣የመማር ፍላጎት የምያነሳሳ፣የጽንስ ሓሳቦች ዕዉነታ እንድረዱ የምያደርግ፣የፈጠራችሎታ የሚያሳድግ፣ልምድ የሚያጓላብት፣ወዘተ ፋይዳዎች ብኖሩትም ተማሪዎች በነቃ አዕምሮአቸዉ ከመመልከት በስተቀር በቋንቋዉ የመጠቀም ችሎታ ስለሌላቸዉ ጥሩ መስተጋብር አልተፈጠረም፣እንድሁም በአስረኛ ክፍል ተመሳሳይ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በቋንቋ ትምህርት አገልግሎት ላይ ከዋሉት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች «እጅግ በጣም ጥሩ» የተማሪ-ለተማሪ የእርስ በርስ መስተጋብር የፈጠረ መርጃ መሣሪያ እንደሌለ ከተገኘው መረጃ ለመመልከት ተችሏል፡፡ጥቅም ላይ የዋለዉ መርጃ መሣሪያዎች በተማሪዎች መካከል የእርስ በርስ መሰተጋብር እንድፈጠር የሚያሳይ እና ተማሪዎቹ በቋንቋዉ እድጠቀሙ ሁነታዎች ብመቻቹም የተማሪዎች የእርስ-በእርስስ መስተጋብር እንዳልተፈጠረ ለመረዳት ተችለዋል፡፡

ይህ ደግሞ በምዕራፍ ሁለት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ የመጠቀም ፋይዳ ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዱ ጤናማ የክፍል ዉስጥ መስተጋብር እንዲፈጠር ማበረታታት እንደሆነ የሚያመላክት ብሆንም ከተብራራው ሀሳብ አንፃር ሲታይ ደግሞ ክፍተት እንዳለው ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

በምልከታ ጥያቄ ተራ ቁጥር 22 በተመለከተ ተማሪዎች ታላሚዉን ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ታግዞ የቀረበላቸውን የትምህርቱን ዋና ዓላማ ምን ያህል እንዳወቁት ለመገምገም መምህራኑ ላቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምን ያህል?ተገቢ ምላሽ መስጠት እንደቻሉ ለሚዳስሰው ጥያቄ የተገኘው መረጃ ቀጥሎ ቀርቧል፤

**ሠንጠረዥ 4.7**

**4.1.1.7 በመርጃ መሣሪያዎች ታግዞ የቀረበውን ትምህርት በተመለከተ ለተማሪዎች ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ የፍጥነት ደረጃ፣**

| የክፍል ደረጃ | በአግልግሎትላይ የዋሉት የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ብዛት | በመርጃ መሣሪያዎች ታግዞ የቀረበውን ትምህርት በተመለከተ ለተማሪዎች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች የተሰጠው ምላሽ የፍጥነት ደረጃ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እጅግ በጣም ፈጣን ነው | | በጣምፈጣን ነዉ | | ዝቅተኛ ነዉ | | በጣም ዝቅተኛ ነዉ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛስሌት(%) | በቁጥር | በመቶኛስሌት(%) | በቁጥር | በመቶኛስሌት(%) | በቁጥር | በመቶኛስሌት(%) |
| 9ኛ | 3 | - | - | 3 | 100% | - | - | - | - |
| 10ኛ | 4 | - | - | 3 | 75% | - | - | 1 | 10% |

ሠንጠረዥ 4.7 የሚያመለክተው ተማሪዎች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተደግፎ የቀረበላቸውን የቋንቋ ትምህርት መሠረት በማድረግ መምህራኑ ለሚያቀርቡላቸው የግምገማ ጥያቄዎች የሚሰጡትን ምላሽ በተመለከተ በተገኘው መረጃ መሠረት፣የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች

መምህራን ከተገለገሉባቸው ሦስት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መካከል በሦስቱ (100%) ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ ተምረው ለሚጠየቁት ጥያቄ  ሓሳቡን ተረድተዉ ምላሽ ለመስጠት«በጣም ፈጣን»በሆነ ሁኔታ ምላሽ ለመስጠት ብሞክሩም በቋንቋዉ የመጠቀም ችሎታቸዉ በጣም አናሳ ነዉ፡፡በአንፃሩ አስረኛ ክፍል በአንዱ(25%) «በዝቅተኛ» ደረጃ ነው መልስ ስሰጡ፣በሦስት(75%)ቱ በጣም ፈጣን በሆነ መልኩ ምላሽ ለመስጠት መሞከራቸዉን ማወቅ ተችለዋል፡፡ሆኖም ግን በቋንዉ የመጠቀም ብቃታቸዉ በጣም አነስተኛ ነዉ፡፡

ቋንቋን በመማር-ማስተማር ሂደት መምህራኑ የተገለገሉባቸውን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከማራኪነት አንፃር፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ማራኪ ቀለም ያላቸው ትክክለኛ ንድፍ የያዙ እና የተማሪዎችን ስሜት የሚያረኩ ሊሆኑ ይገባል የሚል ሐሳብ በምዕራፍ ሁለት 2.2.2 ላይ ተገልጿል፤ይህም ተስማሚ የሆነ ትምህርት መርጃ መሣሪያን አግኝቶ ለመጠቀም ካሏቸው ሰባት መመዘኛዎች አንዱ ማራኪነት ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ በክፍል  ምልከታ ዉስጥ በጥያቄ ተራ ቁጥር 22 ላይ በዕለቱ ስለቀረበው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ ማራኪነት፣«ለሁሉም ተማሪዎች»፣«ለአብዛኛዎቹ»«ለግማሹ የደስታ መንፈስ የፈጠረባቸው» መሆኑን የሚመለከትና «ምንም ደስታ አልፈጠረባቸውም»በሚሉ ገላጭ ሃረጋት እንዲለካ ተደርጓል፡፡ ይህንም በሚቀጥለው ሠንጠረዥ እንመልከት፤

ሠንጠረዥ 4.8

**4.1.1.8 በዕለቱ መምህራን የተገለገሉባቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ማራኪነት በተመለከተ የተማሪዎችን ስሜት የሚዳስስ፤**

| የክፍል ደረጃ | በአግልግሎትላይ የዋሉት የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ብዛት | በዕለቱ መምህራን የተገለገሉባቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ማራኪነት በተማሪዎች ላይ ያሳደረው የደስታ ስሜት፣ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ለሁሉም የደስታ ስሜት ፈጥሯል | | ለአብዛኛዎቹ ተማሪዎች የደሰታ ስሜት ፈጥሯል | | ለግማሾቹ ተማሪዎች የደስታ ስሜት ፈጥሯል | | ለተማሪዎቹ ምንም የደስታ ስሜት አልፈጠረባቸውም | |
| | | በቁጥ/ር | በመቶኛስሌት(%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት(%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት(%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት(%) |
| 9ኛ | 3 | - | - | - | - | 3 | (100%) | - | - |
| 10ኛ | 4 | - | - | - | - | 4 | (100%) | - | - |

በዕለቱ በመማር-ማስተማር ሂደት በአገልግሎት ላይ የዋለውን የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ ማራኪነት፤የተማሪዎችን ስሜት በተመለከተ መግለጫውን ስንዳስስ፣በሁለቱ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለግማሾቹ ተማሪዎች የደስታ ስሜት እንደፈረጠረባቸዉ መረዳት ተችለዋል፡፡በአጠቃላይ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የደስታ ስሜት የነበራቸው ሲሆን ይህም በምዕራፍ ሁለት በተራ ቁጥር 2.2.2 ከተገለፀው ሀሳብ ጋር የተስማማ መሆኑን ያመላክታል፡፡

የክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደትን የተሟላ ለማድረግ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ ማስተማር ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ እሙን ነው፡፡ስለትምህርት መርጃ መሣሪያዎችም አጠቃቀም በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተገለጸው በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም በተማሪዎች አዕምሮ ላይ አዳዲስ ዕውቀቶችና ክሂሎች እንዲቀረጽ፣ተቀርፀውም በተገቢው ጊዜና ቦታ በተግባር እንዲገለገሉባቸው ያደርጋሉ፡፡ምክንያቱም የትምህርት መርጃ

መሣሪያዎች የተለያዩ ተግባራትንና ልምዶችን በማቅረብ የተማሪዎችን ፍላጎት በማነሳሳት፣ ትኩረታቸውን ወጥሮ በመያዝ ወደሚፈለገው ግብ እንዲያመሩ በክፍል ውስጥ ጥሩ ተሳትፎ እንዲያሳዩ መምህራን የሚገለገሉበት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያና አጠቃቀም ይወስናል በማለት ተገልጾ ነበር፡፡

ከዚህ ሐሳብ በመነሣት መምህራን የተገለገሉባቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የማድረግ ደረጃውን በተመለከተ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ «እጅግ በጣም ጥሩ ነው»፣ «በጣም ጥሩ ነው»፣ «ጥሩ ነው»፣ «አነስተኛ ነው» በሚሉ ገላጭ ቃላት እንዲለካ ተደርጎ ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.9**

**4.1.1.9 በአገልግሎት ላይ በዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመጠቀጠም ተማሪዎች የሚያሳዩት የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ውጤት፣**

| ምልከታ የተካሄደ ባቸው ክፍሎች ደረጃ | በአገልግሎትላይ የዋሉት የትምህርትቋንቋ መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | በአገልግሎት ላይ በዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመቀጠም ተማሪዎች የሚያሳዩት የክፍል ውስጥ ተሳትፎ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እጅግበጣምፈጣን ነው | | በጣምፈጣን ነዉ | | ፈጣ ነዉ | | ዝቅተኛ ነዉ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛስሌት(%) | በቁጥር | በመቶኛስሌት(%) | በቁጥር | በመቶኛስሌት(%) | በቁጥር | በመቶኛስሌት(%) |
| 9ኛ | 3 | - | - | - | - | 3 | 100% | - | - |
| 10ኛ | 4 | - | - | - | - | 4 | 100% | - | - |

ከሠንጠረዥ 4.9 የምንረዳው መምህራን በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ በመታገዝ ሲያስተምሯቸው ተማሪዎች ያላቸው የክፍል ውሰጥ ተሳትፎ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ሲታኝ በሁለት በሁለት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመጠቀም የሚያሳዩት የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በቋንቋዉ የመጠቀም ችሎታቸዉ በጣም አናሳ ብሆንም ተማሪዎች በክፍል ዉሰጥ የምያሳዩት የተሳትፎ እንቅስቃሰያቸዉ«ፈጣን»መሆኑን ያመለክታል፡፡ምንም እንኳን

መምህራን የተገለገሉባቸው በቁጠር «አነስተኛ»የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የተጠቀሙ ቢሆኑም የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በጥሩ ደረጃ ላይ መገኘቱን ያመለክታል፡፡ይህም የታየዉ በሚጠቀሙት ቋንቋ ችሎታ ሳይሆን ባላቸዉ ፍላጎትና ተነሳሽነት ነዉ፡፡ ቀጥለው ደግሞ በአገልግሎት ላይ የዋሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተገቢነት እንመልከት፣

የጥናቱ ታላሚ መምህራን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በሚያስተምሩባቸው ክፍሎች የተጠቀሙባቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በዕለቱ ሊሰጥ የታቀደውን ረቂቅ የትምህርት ይዘት ተጨባጭና ግልፅ ከማድረግ አኳያ ምን ያህል ተገቢነት እንዳላቸው በክፍል ውስጥ ምልከታ ጊዜ ለመቃኘት ተምክሯል፡፡የተገቢነት ደረጃውም«እጅግ በጣም ጥሩ»፣ «በጣም ጥሩ»፣«ጥሩ»እና«አነስተኛ»በሚሉት ገላጭ ቃላት እንዲለካ ተደርጓል፡፡በዚህም መሠረት በክፍል ውስጥ ምልከታ በጥያቄ ተራ ቁጥር 11 ላይ የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ እንደሚከተለው ቀርቧል፤

**ሠንጠረዥ 4.10**

**4.1.1.10 በምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተገቢነት፣**

| ምልከታ የተካሄደ ባቸው ክፍሎች ደረጃ | አገልግት ላይ የዋሉት የቋንቋ መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | በአገልግሎት ላይ የዋሉ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተገቢነት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እጅግ በጣምጥረ ነው | | በጣም ጥሩ ነዉ | | ጥሩ ነዉ | | ዝቅተኛ ነዉ | |
| | | በቁ ጥር | በመቶኛ ስሌት(%) | በቁጥ ር | በመቶ ኛስሌ ት(%) | በቁጥ ር | በመቶ ኛስሌ ት(%) | በቁጥ ር | በመቶኛ ስሌት(%) |
| 9ኛ | 3 | - | - | 2 | 66.66 | 1 | 33.33 | - | - |
| 10ኛ | 4 | - | - | 4 | 100 | - | - | - | - |

ከዚህ ሠንጠረዥ የሚንረዳዉ አብዛኛዎቹ መምህራን እጅግ ውስን በሆኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አልፎ አልፎ ቢጠቀሙም፣ የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ከማሳካት አኳያ የተደረገው የአጠቃቀም ብቃት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ተገቢነት የሚያንፀባርቅ ነው፤በአንፃሩ ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም የጥቂት መምህራንን የቅድመ ዝግጅት ብቃት ማነስን ያመላክታል፡፡

መምህራን እውነተኛ በሆኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የመጠቀም ልምድ፣

በእውነተኞ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም ቶሎ ሊረሱ የሚችሉትን ረቂቅ የሆኑ አስተሳሰቦችን፣የነገሮችን እንቅስቃሴ፣ጥልቀት፣ክብደት፣ጠረን፣ስሜት፣ጣዕምና፣ቀለም በተጨባጭ ከማስረዳት አኳያ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለውና ከተቻለ አዲስና ወጥ በሆነ እውናዊ የትምህርት ልምምድን ተጠቅሞ ማስተማር ሌሎች ወካይ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ከመጠቀም ይልቅ የተሻለ እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ላይ በተራ ቁጥር 2.2 ላይ ተገልጾ ነበር፡፡በዚህም መሠረት በመማር-ማስተማር ሂደት የክፍል ውስጥ ምልከታ በተካሄደበት ወቅት የተስተዋሉን፣የተመዘገቡትን እና በመምህራኑ ዓመታዊ ዕቅድ የ2013 ዓ.ም. የአንደኛ መንፈቀ ዓመትየዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዕቅድ መካከል የአንድ ትምህርት ቤት ተወስዶ ከየርዕሶቹ አንፃር የተጠቆሙትን እውነተኛ የሆኑትን አጋዥ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት ለመቃኘት ተሞክሯል፤

ሠንጠረዥ 4.11.

4.1.1.11 በክፍል ምልከታ ወቅት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከዓይነት አንፃር ሲታዩ፣

| የክፍል ደረጃ | አገልግት ላይ የዋሉት የቋንቋ መርጃ መሣሪያ ዎች ብዛት | በአገልግሎት ላይ የዋሉ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዓይነትና ብዛት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እውነተኛ የትምህርትመርጃ መሣሪያዎች ብዛት | | ዕይታዊ የትምህርትመርጃ መሣሪያ ብዛት | | ድምፃዊየትምህ ትመርጃ መሣሪያዎች ብዛት | | ድምፃዊና ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት | |
| | | በቁጥር | በመቶኛስሌት(%) | በቁጥር | በመቶኛስሌት(%) | በቁጥር | በመቶስሌት(%) | በቁጥር | በመቶኛስሌት(%) |
| 9ኛ | 3 | 1 | 33.33% | - | - | - | - | 2 | 66.66% |
| 10ኛ | 4 | 2 | 50% | - | - | - | - | 2 | 50% |

ከሠንጠረዥ 4.11. መረዳት የሚቻለው በክፍል ምልከታ ወቅት ለዘጠነኛ ክፍል የመማር-ማስተማር ሂደት መምህራኑ ከተጠቀሙባቸው ሦስቱ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መካከል አንዱ(33.33%)እውነተኛ ሲሆን፣በአስረኛ ክፍል ከቀረቡት ከአራቱ አንዱ ብቻ(25%) እውነተኛ ነዉ፡፡

እነዚህንም በዝርዝር ሲታዩ ዘጠነኛ ክፍል ከቀረበው በሦስቱ ትምህርት ቤቶች በአንደኛው ላይ (አርጆ ሁለተኛ ደረጃ) በተካሄደ የክፍል ውስጥ ምልከታ የትምህርቱ ርዕስ ምዕራፍ ሁለት«ስነ-ቃል»ነበር፡፡በተማሪዎች ሥነ-ቃል ተሰብስበዉ በክወና እንዲያቀርቡ ሲደረግ፣ ተማሪዎቹም የሰበሰቡትን ሥነቃል በክወና መልክ ተግብረዋል፡፡ይህ ደግሞ በድራማ መልክ ቀርበዉ እንደ እውነተኛ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ሆኖ አገልግሎዋል፤በተመሳሳይ መልኩ በአስረኛ ክፍል የክፍል ውስጥ ምልከታ ተደርጎዋል፡፡የትምህርቱ ርዕስ ልበለድ ነበር፤መምህሩ በነገራቸዉ መሠረት ተማሪዎቹ የጎበዝ ተማሪ እና የሰነፍ ተማሪ ባህር በክፍል ዉስጥ የሚያሳዩትን ባህር ለማሳየት ገፀ-ባህር ሆኖ አሳይተዋል፡፡ይህ ደግሞ እንደ እዉነተኛ የትምህርት መርጃ መሣርያ ሆኖ አገልግለዋል፡፡

በሠንጠረዥ4.11. በ2013 ዓ.ም.የአንደኛ መንፈቀ ዓመት ለናሙና የአንዱን ትምህርትቤት (አርጆ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን) በመውሰድ እውነተኛ የሆኑ አጋዥ መሣሪያዎች ተዳስሰዋል፡፡በዳሰሳዉም ትምህርት ቤቱ በክፍል ምልከታ ወቅት እና ከመምህራን የመንፈቀ ዓመት ዕቅድ መረጃዎች በመነሳት ለመማር ማስተማር ሂደት በአጋዥነት በአገልግሎት ላይ የዋሉት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በዓይነት ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፤

**ሠንጠረዥ4.12.**

**4.1.1.12 ከታላሚ ትምህርት ቤቶች ለናሙና በአንዱ (በአርጆ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት እቅድ ውስጥ የተጠቀሙትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት በዓይነት ተለይቶ ሲቃኝ፤**

| የክፍል ደረጃ | በዕቅድ ደረጃ የተጠቀሙየቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያዎች ብዛት | የሚታዩየቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያ ብዛት | | የሚደመጡ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያዎች ብዛት | | የሚደመጡና የሚታዩየቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያዎች ብዛት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት (%) |
| 9ኛ | 13 | 1 | 7.7% | 2 | 15.38% | - | - |
| 10ኛ | 11 | 2 | 50% | 2 | 50% | - | - |

ከዚህ በላይ ከቀረበው መረጃ ማወቅ የሚቻለዉ በተያዘው የትምህርት ዘመን አንደኛ መንፈቀ ዓመት፣ከታላሚ ትምህርት ቤቶች በአንደኛው ለሁለቱም የክፍል ደረጃዎች መምህራን ሊጠቀሙ ከአቀዷቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መካከል ዕውነተኛ የሆነ መርጃ መሣርያ የሚጠቁም በቂ አይደለም፡፡

በምዕራፍ ሁለት በተራ ቁጥር 2.3.2 እንደተገለፀው የሚታዩ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በሁሉም የትምህርት እርከኖች ያገለግላሉ፡፡የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያ በመማር-ማስተማር ሂደት ትምህርቱን ግልፅ፣ ቀላልና ተጨባጭ አድርጎ ለማቅረብ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ መምህራን ከየትኛውም የትምህርት መርጃ መሣሪያ ዓይነት ይልቅ በሚታዩ

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ ማስተማር ይቀላቸዋል፤ያዘወትራሉም፡፡በተለይም ቻርቶች፣ ሥዕሎች፣ ሰሌዳዎች፣ ፍላሽ ካርዶች እና የመሳሰሉት የቋንቋ ትምህርት መምህራን በቀላሉ የሚጠቀሙባቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሊሆኑ ይችላሉ በማለት ተገልጿል፡፡

በመሆኑም ከላይ በቀረበዉ ሠንጠረዥ 4፡3.10. መረዳት እንደሚቻለዉ በክፍል ምልከታ ጊዜ በአጠቃላይ ሰባት የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ተጠቅመዋል፡፡በ9ኛ ክፍል ከተጠቀሙት መካከል አንድ የሚታይ(ሥዕልና ቻርት) የትምህርት መርጃ መሣርያ ተጠቅመዋል፡፡የተቀረዉ ሁለቱ የሚደመጥ(በመምህሩ ስለ ስነ-ቃል ዘዉጎች ተነበዉ ተማሪዎች እንድለዩ የተደረገ) የትምህርት መርጃ መሣርያ ስጠቀሙ፤በአስረኛ ክፍል ደግሞ ሁለት ያህሉ ብቻ የሚደመጥ የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን ተጠቅመዋል፡፡ የተቀረዉ ሁለቱ ደግሞ በቻርት(ስለእማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቺ፣በሰሌዳ ላይ የልበወለድ ፍሬ ነገሮች፣የአጭር ልቦለድና የረጅም ልቦለድ ልዩነቶችን)በማሳየት ተጠቅመዋል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ከሠንጠረዥ 4.12. ላይ የሚንረዳዉ በአንደኛ መንፈቀ ዓመት ትምህርት ላይ ከተጠቀሱት አስራ ሦስት የትምህርት መርጃዎች መካከል 1/7.69%/ያህል የሚታይ የትምህርት መርጃ መሣርያ እና 2/15.38/ የሚደመጥ የትምህርት መርጃ መሣርያ ብቻ በ9ኛ ክፍል ሲጠቀስ፣በአስረኛ ክፍል ደግሞ ከተጠቀሱት አስራ አንድ የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ሁለቱ/18%/የሚደመጥ የትምህርት መርጃ መሣርያ፣ሁለቱ/18%/ ዕይታዊ የትምህርት መርጃ መሣርያዎች በአንደኛ መንፈቀ ዓመት በዓመታዊ ዕቅድ ላይ መጠቀሱን መረጃዉ ያመለክታል፡፡

የሚደመጥ፣የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መጠቀም መምህሩ የማስተማር መርሖዎች ማለትም፣ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ እና በተግባር እየከወኑ መማር የሚሉትን ዓይነት መርሕ መምህሩ/መምህሯ/ እንዲከተል ከማስቻላቸውም በተጨማሪ በክፍል ውስጥ በመማር-ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በፍላጎታቸዉ ላይ ተመሠርተዉ እንድቀበሉ ለማድረግ የትምህርቱ አቀባበል ዘላቅነትና ምቹ ዐወድ በመፍጠር፤የትምህርት ሂደቱን ምቹ ከማድረጋቸውም በላይ የመምህሩን የሥራ ጫና ያቃልላሉ የሚል በምዕራፍ ሁለት በተራ ቁጥር 2.1.4 ተጠቅሰው ነበር፡፡ሆኖም ግን የተፈለገዉን ያህል እዉነተኛ፣የሚደመጥ፣የሚደመጥና የሚታይ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያዎችን እንዳልተጠቀሙ መረጃዉ ያመለክታል፡፡የተጠቀሙትም የትምህርት መርጃ መሣርያ ትኩረት ሰተዉ ሳይሆን አጋጣሚ የክፍል ምልከታ ስለነበሬ ይመስላል፡፡

በአጠቃላይ በተጠኝ ትምህርት ቤቶች የተጠቀሙትና በ2013 ዓ.ም በመንፈቀ ዓመቱ ዕቅድ ላይ የተጠቀሱት የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ማለትም የሚደመጥ፣የሚደመጥና የሚታይ በበቂ ሁነታ እንዳልተጠቀሙ ያመለክታል፡፡ይህ ደግሞ በምዕራፍ ሁለት 2.1.2 ላይ እንደተገለጸዉ የአንድን ድርጊት ወይም የአንድን ነገር ተከተላዊ ዕደት በተማሪዎች አዕምሮ ዉስጥ ምናባዊ ምስል በመፍጠር ሓሳቡ በአዕምሮ እየተደጋገመ እንድመጣ አያደርግም፤የተማሪዎች የማሰብ ችሎታ አያፋጥንም፤ከአከባብያቸዉ ጋር መስተጋብር አያደርጉም፤አከባብያቸዉን አይወዱም፤

አያደንቁም፤የመማር ፍላጎትን አይቀሰቅስም፤መምህራን የሚያቀርቡላቸዉን የትምህርት ይዘቶች ተአማን (እዉነተኛ) አያደርግም፤ተገብ ትርጉም አንድኖራቸዉ አያስችልም (Malawi institute of Education 20003)፡፡

ከላይ የቀረበዉን ጥያቄ መሠረት በማድረግ የሚደመጥ፣የሚደመጥና የሚታይ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያን በሚመለከት መኖርና አለመኖራቸዉን ለማወቅ መምህራን ተጠይቀዉ የሰጡት ምላሽ አስሩም መምህራን አንድም የለም በማለት መልሰዋል፡፡ለምን ተብለዉ ስጠየቁ ትምህርት ቤቱ አያዘጋጅም በማለት መልሰዋል፡፡ትምህት ቤቱ ባያዘጋጅም ጥቅም አለዉ ብላችዉ ካመናቹት ለምን በትብብር አታዘጋጁም ተብለዉ ስጠየቁ አራቱ እንደመገረም ሆኖ የሚንጠቀመዉም ለግምገማ ብለን እንጅ ሁነታዎች ተመቻችተዉና ፍላጎት ኑሮን አይደለም ስሉ፣ስድስቱ ደግሞ ባጀት ስለምጠይቅ ትምህርት ቤቱ ስለማይተባበረን ለማዘጋጀት ፍላጎት የለንም በማለት መልሰዋል፡፡ሆኖም ግን አንዱ መምህር ለወደፍት ልታሰብበትይገባል ብለዋል፡፡ይህ ደግሞ በጽሑፍ መጠይቅ ተራ ቁጥር 25 ላይ ቀርበው መምህራን ከሰጡት ምላሽ ጋር ይመሳሰላል፡፡

ከፍ ብሎ ከተዘረዘሩት የመምህራን ምላሾች መረዳት እንደሚቻለው ስለ ትምህርት መርጃ መሣርያ የሚመለከታቸዉ አካላት ትኩረት እንዳልሰጡትና ለማዘጋጀትም ሆነ ለመጠቀም ፍላጎት እንደለላቸዉ ለማወቅ ተችለዋል፡፡

### 4.1.2 መምህራን በኅትመት ውጤቶች የመጠቀም ልምድ በተመለከተ፤

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በትምህርት መርጃ መሣርያ በመጠቀም ለማስተማር ያጋጠሙ ችግሮች አለ?ተብለው ስጠየቁ፤አብዛኛዎቹ 90%ቱ መምህራን አዎ አጋጥሞናል ብለወዉ መልሰዋል።ምንድርነዉ ያጋጠማችሁት ስባሉ፤በትምህርት መርጃ-መሣርያ ለመጠቀም ፍላጎት ብኖረንም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ለምሳሌ መጽሔቶች፤የድምፅ ቀረጻ መሣርያዎች እና የተለያዩ የኅትመት ዉጤቶች ከአከባብያችን ማግኘት አንችልም ስሉት፤አንዱ /10%ቱ/ ደግሞ ለመጠቀም ትኩረት ሰጥቼ አስበቤት አላዉቅም በማለት መልሰዋል።ስለሆነም መምህራን ምንም ዓይነት የኅትመት ውጤቶች ያልተጠቀሙና በዕቅዳቸው ውስጥም ያልተካተተ መሆኑን በጥናቱ ጥያቄና መልስ ውጤት መመልከት ተችሏል።

### 4.1.3 መምህራን በተለያዩ ሠሌዳዎች የመጠቀም ልምድ አስመልክተው የተገኘ ውጤት

የመማሪያ ክፍሎች በተለየዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መሟላትና መዋብ እንደሚኖርባቸው ይታመናል።እነዚህም መርጃ መሣሪያዎች የተለያዩ ሠሌዳዎችን ያካትታል።

በምዕራፍ 2.1.3 ላይ እንደተገለፀው በአንድ መማሪያ ክፍል ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸው ሠሌዳዎች ዓይነት፣ የተለያዩ ትምህርታዊ ማስታወቂያ የሚለጠፍበት ሰሌዳ፣ የተለያዩ ፍላሽ ካርዶች፣ሥዕሎች፣ፎቶግራፎችና ቻርቶች፣ወዘተ.የሚንጠለጠሉበት ከወፍራም ሱፍ ጨርቅ የተሠራ ሻሽ ሠሌዳ እና ብረት ነክ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚያያዙበት መግነጢሳዊ ሠሌዳዎች ምልከታ በተካሄደባቸው የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሉም።የቋንቋ መምህራኑ የሚጠቀሙባቸውን የተለያዩ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በሚገባ በተዘጋጁ ሠሌዳዎች መጠቀም ትልቁ የመምህራን ቁልፍ ተግባር ነው። በእርግጥ በፋብሪካ የሚመረቱ እንደመግነጢሳዊ ሠሌዳ ዓይነቶችን ማግኘት ሊያስቸግር ይችላል።

ነገር ግን በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ እንደማስታወቂያ ሠሌዳ፣ሻሽ ሠሌዳ በመሳሰሉት በመጠቀም በሥርዓት የመማር-ማስተማር ሂደቱን መተግበር ይቻል ነበር። ይህም የክፍሉን ውበት ከመጠበቁም በላይ የተማሪዎችን ስሜት በማነቃቃትና ፍላጎታቸውን በመቀስቀስ ረገድ ጥሩ ሚና ይኖረው ነበር። ነገር ግን የቋንቋ መምህራኑ በሠሌዳዎች የመጠቀም ልምዳቸው እጅግ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል።

### 4.1.4 ታላሚ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በተመለከተ ስለአጋጠማቸው ችግር አሰመልክተው የሰጡት ምላሽ፣

በቋንቋዉ መምህራን አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት መርጃ መሣርያዎች እንድዘጋጅ ትምህርት ቤቱ ባጀት እንድበጀትለት ብጠየቅም ፍቃደኛ ከመሆን ፈጣሪ ነህ ሁልጊዜ አዲስ ተጠቀም በማለት ተገቢ ያልሆነ አመራር መኖር፤አጋር ድርጅቶችን ጠይቀን አስፈላጊ ነገሮችን ለማሟላት ብታሰብም ቤትምህርት ቤታችን ላይ የሚሠራ ድርጅት አለመኖር፣ከአከባብያችን ከሚገኙ ነገሮች ሠርተን ለመጠቀም ፍላጎትና ተነሳሽነት አለመኖር፣የተሠራዉንም በአግባብ አስቀምጦ አለመጠቀም፣ካለዉ ነባራዊ ሁነታ የተነሳ ተማሪዎች በቋንቋዉ የመጠቀም ችሎታቸዉ እጅግ አናሳ መሆን የሚሉት ሐሳቦች እንደ ችግር የሚቆጠሩ ናቸዉ ብለዉ መልሰዋል፡፡አጥኚዉ በዬዓመቱ ለምን በዓመታዊ ዕቅድ ላይ ይቀርባል?ብለዉ ስጠይቅ የተለመዴ ሆኖ ነዉ እጅ ትኩረት ተሰጥቶበት ለመጠቀም ሣይሆን በዬስምስተሩ መገምገሚያ መስፍርት ላይ ስለምቀርብ ለዉጤት ተኮር ነጥብ ማግኘት ተብለዉ የማስመሰል ሥራ ነዉ ስሉ መልሰዋል፡፡ሆኖም ግን ተማሪዎቹ ለትምህረቱ ፍላጎትና ችሎታ ብኖራቸዉ የቋንቋዉ ትምህርት መርጃ መሣርያ አሳታፍ እና አነቃቅ እንደሆነ እናዉቃለን በማለት ተመሳሳይ መልስ ሰተዋል፡፡ በተጨማርም እራሱን የቻለ የቋንቋ ክፍል አለመኖር፤የማስተማሪያ መሣሪያዎች ተሟልተው አለመገኘት ያጋጠሙን ችግሮች ናቸው በማለት ተጠኝዎቹ ገልፀዋል፡፡

### 4.1.5 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችና የማስተማሪያ መሣሪያዎች

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችና የማስተማሪያ መሣሪያዎች በሚል የተጠቃለሉት መርሐ ትምህርቱ፣ የተማሪው መጽሐፍ እና የመምህሩ መምሪያ ናቸው፡፡ እነዚህ መሣሪያዎች በምዕራፍ ሁለት እንደተጠቀሰው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በመጠቀም በኩል ለመምህሩ ያላቸው እገዛ ከፍተኛ ነው፡፡ የዚህ ክፍል ዋና ትኩረትም በ2007ዓ.ም.ተሻሽሎ የተዘጋጀ የዘጠነኛ እና የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርሐ-ትምህርት፣የመምህሩ መምርያ እና የተማሪዉ መማርያ መጽሐፍት መምህሩ እንዲጠቀም ምን ያህል እገዛ እንደሚያደርግላቸው ለማወቅ በቃልና በጽሑፍ መጠይቅ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ነበር፡፡ የተገኘውም መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፤

## 4.2. ለመምህራን ከቀረበው ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

በዚህ ክፍል የማስተማሪያ መሣሪያዎቹ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም ለመምህራኑ የሚያደርጉትን እገዛ ለማወቅ ከቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሚከተለው ምላሽ ተገኝቷል፤

ጥያቄ ሰባት፣የቋንቋ ትምህርትን በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያ አስደግፌዉ ማስተማር ለተማሪዉና ለመምህሩ ይጠቅማል?ተብለዉ ስጠየቁ የሰጡት መልስ፣አስሩም ተጠያቅዎች አዎ ይጠቅማል ብለዉ መልሰዋል፡፡ለምን ተብለዉ ስጠየቁ የሚከተለዉን ብለዋል፡፡

መ1እናመ7፣ትምህርቱን አይረሰ ያደርጋል፣ያሳትፋል፣ያነቃቃል፣የእዉቀት አድማስ እንድያሰፋ

ያደርጋል፡፡

መ2፣3እና8፣በመርጃ መሳርያ ማስተማር ትምህርቱን ተጨባጭ ያደርጋል፡፡

መ4፣የቋንቋዉን ትምህርት በቀላሉ እንድረዱ ያደርጋል፡፡

መ5፣መ6፣መ9ና 10 የይዘቱን ዓላማ ዕንድረዱ ያደርጋል፣የመማር ፍላጎትን ያነሳሳል፣የፈጠራ ችሎታን ያሳድጋል ብለዉ ተመሳሳይ መልስ ሰተዋል፡፡

መ7፣መ8 ጊዜን ይቆጥባል፣በትምህርቱ ዓላማ ላይ ትኩረት እንድያደርጉ ያደርጋል፡፡

መ9 እና መ10 በተመሳሳይ በግል እና በቡድን የመማር ልምድን ያሳድጋል፡፡

በአጠቃላይ የአንድን ድርጊት ወይም የአንድን ነገር ተከተላዊ ሂደት በተማሪዎች አዕምሮ ዉስጥ ምናባዊ ምስል በመፍጠር ሓሳቡ በአእምሮ እየተደጋገመ እንድመጣ ያደርጋሉ፡፡ይህም ተተኳር የትምህርት ይዘቱን ተጨባጭና አይረሴ ያደርጋል፤ረቂቅ የሆኑ የትምህርት ሐሳቦችን በተጨባጭ በማቅረብ ተማሪዎች ያለ ምንም ችግር የትምህርት ይዘቶችን እንድረረዱና የተማሪዎችን የማስታወስ ችሎታ በማፋጠን ተማሪዎች ከአከባብያቸዉ ጋር መስተጋብራዊ ግኑኝነት እንድያደርጉና አከባብያቸዉን እንድወዱ እንድሁም፣ እንድያደንቁ በማገዝ ተማሪዎች ክሂሎትን ለምሳሌ፣የማዳመጥ፣የምልክት ወይም በእጅ የመጠቀም፣የመገጣጠም፣ችግር የመፍታት፣አብሮ የመስተራት ልምዶችን እድያዳብሩና የመማሪ ጉጉት በመቀስቀስ ለመማር የሚኖራቸዉን መነሳሳት በመጨመር፣በተማሪዎችና በመምህራን ዘንድ ፈጠራን ለመቀስቀስ ፣ መምህራን የሚያቀርቡአቸዉ የትምህሪት ይዘቶች ለተማሪዎች ተአማኒ (እዉነተኛ)፣ተገብ እና

ትርጉም ያላቸዉ እንድሆኑ ያስችላል ብለዋል፡፡ ይህ ደግሞ በምዕራፍ ሁለት ነጥብ አንድ ሁለት ከተገለፀዉ ጋር ተመሳሳይ አንደምታ አለዉ፡፡

በጥያቄ ተራ ቁጥር ስምንት ላይ የቀረበዉ፤የቋንቋ ማስተማሪያ መሣሪያዎቹ የቋንቋ ትምህርትን በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም እገዛ አላቸው? ለምን? የሚል ጥያቄ ቀርቦ፣ሁሉም መምህራን (አስሩ)100% በጣም ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡ለምን ለሚለው ጥያቄ አብዛኞቹ(75%)ቱ መምህራን መርሓ ትምህርቱና የመምህሩ መምሪያ በምን ዓይነት እና እንዴት?መጠቀም እንደሚገባን፣ዓይነታቸውንና አጠቃቀማቸዉን በመጠቆም በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስላላቸው ማግኘት የሚቻል ብሆን የተጠቆመውን ስለምንጠቀም የተማሪው መፅሀፍ በጥንድ፣በቡድንና በተናጠል ምንን? እንዴት? መጠቀም እንዳለብን ስለሚጠቁም ለአጠቃቀም እጅግ ከፍተኛ እገዛ አላቸው ሲሉ ቀሪዎቹ ሁለቱ መምህራን (25%) መርሓ ትምህርቱ ካለ ሁሉንም አጠቃሎ ስለሚይዝ መርሓ ትምህርቱ ነው የበለጠ ጠቀሜታ ያለው፤ይሁን እንጂ በደረጃ ሁሉም እንደሚያስፈልጉ ግልፅ ነው የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጥያቄ ተራ ቁጥር ዘጠኝ፤በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ ለመጠቀም ያግዘናል ብለው በማሰብ የሚገለገሉት የትኛውን የማስተማሪያ መሣሪያን ነው? በሚል ለቀረበው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የሚከተለው ነው፤ሁሉም መምህራን (100%) አንዱ በተጓደለበት ሁኔታ መርጃ መሣሪያን ተጠቅሞ የቋንቋን ትምህርት ማስተማር አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም አንዱ በተጓደለበት የተሟላ የመማር ማስተማር ሒደት አይተገበርምና፤ነገር ግን አስሩም መምህራን (100%) በየትምህርት ቤታቸው ከተወሰነ የተማሪ መጽሐፍ ሌላ መርሓ ትምህርትም ሆነ የመምህሩ መምሪያ የሌለ መሆኑ ገልፀዋል፡፡በዚህ ምክንያት የተሟላ የቋንቋ ትምህርት ይሠጣል ተብለዉ ማሰብ አስቸጋር ነዉ፡፡

ጥያቄ ተራቁጥር አስር፤የሚትጠቀሙባቸዉ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርዎች ከየት ያገኛሉ ለምለዉ ጥያቄ፣አስሩም መምህራን ከትምህርት ቤትና ከአከባብዉ የሚገኘዉ ጥረ እቃዎች ነዉ የምል መልስ ሰጠዋል፡፡እንደት ያገኛሉ ለሚለዉ ደግሞ እብዛም አይኖርም እንጅ ያለዉን ከትምህርት ቤቱ ቅርንጫፍ ማዕከል እናገኛለን አሉ፡፡ነገር ግን ቅርንጫፍ ማዕከል ለእስሙላ ብቻ ያለ በመሆኑ ያሉት የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ተበታትነዉ የሚገኙ ናቸዉ፡፡

ጥያቄ ተራቁጥር አስራ አንድ፤ላይ የቀረበዉ በማስተማር ሙያ ላይ እያሉ የትምህርት መርጃ መሣርያን በተመለከተ የሙያ ላይ ስልጠና ወስደዉ ያዉቃሉ?ለምለዉ ጥያቄ ሁላቸዉም ምንም ስልጠና ወስደን አናዉቅም ብለዋል፡፡

ጥያቄ 12፣ስለትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም በመምህራን መገምገሚያ ስለመስፈሩ ያለዎት አስተያየት ምንድን ነው?ተብለዉ ስጠየቁ ሁለም በተመሳሳይ መልክ ተለምደኣዊ ሆኖ እንጅ ትኩረት ሰተዉ መማር ማስተማርን ተግባራዊ ለማድረግ ታስቦ አይደለም ብለዉ መልሰዋል፡፡

ጥያቄ13፣በመማር-ማስተማር ሂደት በትምህርት መርጃ መሣሪያ ከተገለገሉ በኂላ የዕለቱ ትምህርት ለተማሪዎች ግልፅ መሆኑን እንዴት ያውቃሉ?100%ቱ ተጠኝዎች ይህማ ግልጽ ነዉ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ለተማሪዎች ግልጽ መሆኑና አለመሆኑን ማወቅ ይቻላል፡፡

ጥያቄ14፣በትምህርት ቤትዎ የትምህርት መርጃ መሣሪያን ለመጠቀም የሚያገዙ የተመቻቹ የቴክኖሎጂ ውጤቶች አሉ?አብዛኞቹ በማጉረምረሚ እና በሣቅ የተመቻቹ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ማዘጋጀት ይቅርና ለትምህርቱ ደንታ የላቸዉም ብለዉ መልሰዋለ፡፡

ጥያቄ15፣የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ በትምህርት ቤትዎ ሃሳብ የሚለዋወጧቸው መምህራን አሉ?በሙያዎት ላይስ ምን ያህል እገዛ አድርጓል?ተብለዉ ተጠይቀዉ መወያት ጥሩ ነዉ ነገር ግን፣ስለ ትምህርት መርጃ መሣርያ አስመልክተዉ ሁለም መምህራን ከተመሳሳይ ድፓርትመንታቸዉ ጋር እንጅ ከለላ ድፓርትመንት ጋር የመወያየት ልምድ የሌም፡፡እኛም በተመሳሳይ መልኩ ከራሳችን ዲፓርት መንት ጋር እንጅ ከለላ ጋር ሀሳብ የመለዋወጥ ልምድ የለንም ብለዋል፡፡ከእርስ በእርሳችን ጋር መወያት በሙያችን ላይ ጥሩ እገዛ አለዉ ስሉም አክለዋል፡፡

ጥያቄ አስራ ስምንትና አስራ ዘጠኝ፣አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ አይነት ምን አይነት ነው? ለምን? አብዛኛውን ጊዜ የትምህርት መርጃ መሣሪያ የሚጠቀሙት የትኛውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ለማስፈፀም ነው?ለምን?ለምሉት ጥያቄዎች አራቱ/40%/ መምህራን የንግግር ቋንቋና የሰዋሰዉ ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ ነዉ ስሉ፣አምስቱ/50%/ደግሞ በፍጹም አይሆንም አንዱን የቋንቋ ክህል ለብቻዉ ማስተማር አይቻልም፣በአንዱ ላይ ትኩረት በማድረግ ሁሉንም በጋራ ማስተማር እንጅ በተናጠል ማስተማር አይቻልም፣እንድሁም ክሂልን ስማሩ ሰዋሰዉንም ማስተማር የግድ ነዉ ብለዉ

መልሰዋል፡፡አንዱ/10%/ደግሞ የሚወሰነዉ የዕለቱ ትምህርት ዓለማ ነዉ ብለዉ መልስ ሰተዋል፡፡

ጥያቄ 20፣ለወደፊቱ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ መሆንና መደረግ ስለአለበት ሁኔታ ያለዎት አስተያየት ምንድን ነው?ለምለዉ ጥያቄ የትምህርት መሣርያዎች ማለትም መርሓ ትምህርት፣የተማሪ መማርያ መጽሐፍት እና የመምህሩ መመርያ ለመምህራን ማዘጋጀት፣የስራ ላይ ስልጠናዎች መስጠት፣ከአቻ ትምህርት ቤት ጋር የልምድ ልዉዉጥ ማድረግ፣የሚመለከታቸዉ አካላት በትኩረት እድሰሩ ማድረግ፣ባጀት ብበጀትለት፣በተክኖሎጅ ዉጤቶችን መጠቀም በጣም አስፈላጊ ናቸዉ በማለት አስሩም ከላይ የተዘረዘሩትን ሐሳቦችን ሠንዝረዋል፡፡

### 4.3. ለመምህራን ከተሰራጨው ጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

ከምልከታዉና ከቃለ መጠይቁ የተገኘዉን መረጃዎች በጽሑፍ መጠይቅ ለማጎልበት ከቃለ መጠየቅ ጥያቄ ስድስት፣የማስተማሪያ መሣሪያዎች መምህራን በትምህርት መርጃ ታግዘው እንዲጠቀሙ አጋዥ ናቸው? እንዴት? የሚል ጥያቄ ለመምህራኑ ቀርቦ የተገኘው መልስ አስሩም መምህራን (100%) «አዎ»

ከተጠኝዎቹ ቃለ መጠየቅና ጽሑፍ መጠየቅ ከተገኘዉ ምላሽ መረዳት እንደተቻለዉ የጥናቱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች መምህራን መርሓ ትምህርት እና የመምህሩ መምሪያ የሌላቸውና የተወሰኑ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍት ብቻ እንዳላቸው ነው፡፡ እነዚህ የትምህርት መሣሪያዎች ባልተሟላ ወይም ጎደሎ በሆኑበት ሁኔታ በቂ የቋንቋ ትምህርት እየተሰጠ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡

መምህራን የዓመቱን የትምህርት ዕቅድ ለማዘጋጀት መሣርያዎቹ እጅግ አስፈላጊ ናቸዉ፡፡በምዕራፍሁለት Widdowson(1990:129)ማስተማሪያ መሣሪያዎች ለመምህራን የመማር ማስተማር ሂደቱን እንዴት እንደሚተገበሩና ምን? ለምን? እንደሚጠቀሙ መሪ ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡ከዚህ አንፃር የተሟላ ትምህርት እየተሰጠ ነው ለማለት እንደማያስችልና እነዚህ መሣሪያዎች ባለመኖራቸው ምክንያት የዓመቱንም ሆነ የዕለት ዕቅዳቸውን ለማቀድና ለመጠቀም እንደአማራጭ የወሰዱት የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ መጠቀምን ነው፡፡በዚህ ምክንያት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም

በየትምህርት ቤቶቹ መማር-ማስተማር ሂደት ላይ ያለውን ሁኔታ ለማነፃፀር የሚረዳን መረጃ ቀጥሎ በቀረቡት ሠንጠረዦች እንዳስስ፡፡

መግለጫዎቹ በ2007 ዓ.ም.ተዘጋጅተው አገልግሎት በሚሰጡት የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት ውስጥ ለአንደኛ መንፈቀ ዓመት ትምህርት የተጠቆሙት የዘጠነኛ እና የአስረኛ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣በተጓዳኝ ደግሞ በየክፍል ደረጃዎቹ ያለ እነዚህ በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ብቻ በመጠቀም ያቀዱትና በዚህ የመንፈቀ ዓመት ዕቅድ ላይ የጠቆሟቸውን የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር ደረጃ በደረጃ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ከመንፈቀ ዓመቱ ጋር ቅርበት እንዲኖረው የአንደኛዉ መንፈቀ ዓመት በአስረጅነት ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 4.13.

**በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሓ ትምህርት ውስጥ የተጠቁሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር /አንደኛዉ መንፈቀ ዓመት/**

| ምዕራፍ | የቋንቋ ትምህርት ክፍል | የትምህርት ይዘት | የተጠቆሙት የትምህርት መረጃ መሣሪያዎች |
|---|---|---|---|
| 1 | አንብቦ መረዳት መናገር፣ማዳመጥ ጽፈት | ቋንቋ | ቋንቋና ሕብረተሰብ የሚለዉ ምንባብ፣ መዝገበ ቃላት |
| | -- | --- | ---- |
| | -- | --- | ---- |
| 2 | አንብቦመረዳት መናገር፣ማዳመጥመጻፍ | ቋንቋ | የስነ-ቃል ምንባብ |
| | ሰዋሰዉ | ሰዋሰዉ | ምዕላድ፣ስነ-ግጥም |
| | ስነ-ጽሑፍ | ስነ-ጽሑፍ | ስነ-ግጥም/አጫጭር ግጥሞች/ |
| 3 | አንብቦ መረዳት ማዳመጥ፣መናገር፣መጻፍ | ቋንቋ | ቤተ-መጻፍትናሥነ-ጽሑፍ ሚለዉ ምንባብ፣ አንቀጽ፣ሥራተ.ነጥብ፣ልበቦለድ፣ድርሠት/ታሪክ፣ ገላጭ፣አመዛዛኝ፣ሥዕላዊ ድርሠት/ |
| | ሰዋሰዉ | -- | ----- |
| | ስነ-ጽሑፍ | --- | --- |
| 4 | አንብቦ መረዳት ማዳመጥ፣መናገር፣መጻፍ | ቋንቋ | ስለልቦለድ ምንባብ፣መዝገበቃላት |
| | ሰዋሰዉ | ሰዋሰዉ | እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍች፣ የቃል ክፍሎች፣ሐረጎች |
| | ስነ-ጽሑፍ | ስነ-ጽሑፍ | ልቦለድ፣ዘይቤዎች፣ፈሊጥ |
| 5 | አንብቦ መረዳት መናገር፣ማዳመጥመጻፍ | ቋንቋ | አጫጭር ግጥሞች፣አያያዥና መሸጋገርያ ቃላት |
| | ሰዋሰዉ | ሰዋሰዉ | ዓረፍተ ነገሮች |
| | ስነ-ጽሑፍ | ስነ-ጽሑፍ | ልቦለድ፣ዘይቤዎችናፈሊጣዊ ንግግሮች፣ |

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለዉ በአንደኛ መንፈቀ ዓመት የቀረቡት ይዘቶች የቋንቋ ክህሎት፣ሰዋሰዉ እና ስነ-ጽሑፍ ናቸዉ፡፡እነኝን ይዘቶች ተግባራዊ ለማድረግ የቀረቡት የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ቋንቋና ሕብረተሰብ የሚለዉ ምንባብ፣የስነ-ቃል ምንባብ፣ምዕላድ፣አጫጭር፣ግጥሞች፣ቤተመጻፍትና/ሥነጽሑፍ፣አንቀጽ፣ሥራተነጥብ፣ልበቦለድ፣ድርሠት/ታራክ፣ገላጭ፣አመዛዛኝ፣ሥዕላዊ-ድርሠት/፣ስለልቦለድምንባብ፣መዝገበቃላት፣እማሪያዊና ፍካሪያዊፍች፣የቃልክፍሎች፣ሐረጎች፣ልቦለድ፣ዘይቤዎች፣ፈሊጥ፣ዓረፍተነገሮች፣ልቦለድ፣ዘይቤዎ ችና ፈሊጣዊ ንግግሮች ናቸዉ፡፡የተጠቀሱት የትምህርት መርጃ መሣርያዎች በመርሓ ትምህርቱ ዉስጥ በትምህርቱ አተገባበር ላይ ምንና እንደት በምን አጋዥነት እንደምተገበር የተገለጹ ናቸዉ፡፡ ምንጭ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚንስቴር /2007/

በመሆኑም ከሠንጠረዡ የሚንገነዘበዉ በዘጠነኛ ክፍል አንደኛ መንፈቀ ዓመት በአማርኛ ቋንቋ መርሓ ትምህርት ዉስጥ ሃያ አንድ የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ተጠቅሰዋል፡፡በአንጻሩ ደግሞ መምህራን ባዘጋጁት አንደኛ መንፈቀ ዓመት ዕቅድ ዉስጥ አሰራ ሦስት ያህል / ሥራተ ነጥብ የሚያሳይ፣የአንቀጽ ቅርጾችን የሚያሳይ ሥዕል፣እማሪያዊና ፍካሪያዊ የሚያሳይ ሠንጠረዥ፣ጠብቆና ላልቶ ሲነበብ የምሰጡትን ትርጉም የሚያሳይ ሠንጠረዥ፣ቻርት፣መጣጥፎች፣ምንባቦች ወዘተ የሚሉት የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ተጠቅሰዋል፡፡

በመሠረቱ ትምህርት ለተማሪዎች መሰጠት ስላለበት ብቻ በግምት የሚዘጋጅ አይደለም፡፡የአዘገጃጀቱና የአሰጣጡ ሁኔታ መቼ? የት? ለምን ያህል ጊዜ? ለማን? በማን? የሚሉ ጥያቄዎችን መመለስ በሚችል አግባብ መዘጋጀት አለበት፡፡በመሆኑም መርሃ ትምህርት ሲነደፍ በቅድሚያ የተማሪው ማንነት፣ ፍላጎት ፣ የትምህርት ልምዱ ፣ ትምህርቱ የታቀደበት ቦታና ጊዜ፣ በመወሰን የትምህርቱን ይዘትም ሆነ መጠን በዝርዝር ተተምኖና ተሸንሽኖ የተተግባሪነቱ ሁኔታ በቅድሚያ መረጋገጥ አለበት ይላሉ (Hutchinson and waters 1987, 80 and Yalden 1987 87)፡፡

በርካታ ምሁራን ስለ መርሓ ትምህርት እንደሚከተለዉ ይገልፃሉ፡፡ የአንድ ኮርስ ይዘት መስፈርት ነው፣ Richards (2001p.2)፣የትምህርት ይዘቶችን አደራጅቶ የያዘ መመሪያ ነው፡፡

Brumfit (1984)፣ለመማር አስፈላጊ የሆኑ ታዕታይ ግባቶችንና አደራጅቶን በአንድ ላይ አሰባስቦ የያዘ መሳሪያ ነው፡፡ብራውን(1985)፡፡

ከቋንቋ መርሃ ትምህርት መሰረታዊ ክፍሎች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎች፣የመማር ማስተማር ክንውን፣የግምገማ ስልት፣የማስፈጸሚያ ጊዜያት፣ፈጻሚ አካላትን እና የመሳሰሉ ሁኔታወችን አካቶ መያዝ አለበትይላሉ Dubinand Osishtain (1997)፡፡

በተጨማርም መርሐ ትምህርት የሃገሪቱን አጠቃላይ የትምህርት ፍልስፍና፣ የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ መነሻ አድርጎ መምህሩ ማስተማር የሚገባውን፣ ተማሪው መማር ያለበትን የሚገልፅ መሠረታዊ የትምህርት አካል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር መርሐ ትምህርት የአንድን ሀገር የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲ ስለሚያንፀባርቅ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አደራጆች፣የመማሪያ መሣሪያ አዘጋጆች፣መምህራን፣የፈተና ክፍሎች፣በአጠቃላይ የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን መረጃ

የሚያገኙት ከዚሁ ሰነድ ነው የሚል በምዕራፍ ሁለት በተራ ቁጥር 2.7.2 ተጠቅሷል፡፡ ነገር ግን በታላሚ ትምህርት ቤቶች የታየው ዕቅድ አወጣጥ ከመርሐ ትምህርቱ በቅርፅና በይዘት ያልተስማማ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የአስረኛ ክፍል አንደኛ መንፈቀ ዓመት መርሐ ትምህርት እና የአስረኛ ክፍል አንደኛ መንፈቀ ዓመት በመምህራን ዕቅድ ላይ የተጠቀሙት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣርያዎች ንፅፅር በተመሳሳይ ሁኔታ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 4.14

**በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐ-ትምህርት ውስጥ የተጠቆሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝርዝር (የአንደኛው መንፈቀ ዓመት)**

| ምዕራፍ | የቋንቋ ትምህርት ክፍል | የትምህርት ይዘት | የተጠቆሙት የትምህርት መረጃ መሣሪያዎች | ለአጠቃላይ መርጃ መሣርያ የሚያገለግል |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አንብቦ መረዳት መናገር፤መጻፍ | ቋንቋ | ስለምለዉ ምንባብ፣መዝገበ ቃላት | ታሪኩ ፈንታዬ/2001/ አማርኛ፤ከመለስተኛ እስከ ኮለጅ/ጌታሁን፤አማረ/1989/ የአማርኛ ሰዋሰዉ በቀላል አቀራረብ |
| | ሰዋሰዉ | ሰዋሰዉ | ሐረጋት፣ዓነገር፣የድርሰት ዓይነቶች | |
| | ስነ-ጽሑፍ | ሥነ-ጽሑፍ | ዜይበዎች፣ምሳለያዊ አነጋገሮች | |
| 2 | አንብቦ መረዳት መናገር፤መጻፍ | ቋንቋ | ምንባብ፣ጋዘጦች፣መጽሔቶች፣ መጽሐፍት | -- |
| | ሰዋሰዉ | ሰዋሰዉ | ሐረጋት፣ዓረፍተነገሮች | |
| | ስነ-ጽሑፍ | ስነ-ጽሑፍ | ልቦለድ፣በባህላዊ ጋብቻ ዙርያ ሚነገሩ ምሳለያዊ አነጋገሮችና ቃላዊ ግጥሞች | |
| 3 | አንብቦ መረዳት መናገር፤መጻፍ | ቋንቋ | ምንባብ፣ጋዘጦች፣መጽሔቶች፣ መጽሐፍት፣የአንቀጽ ቅርፆች | መዝገበ ቃላት/የኢትጵያ ቋንቋዎች ኢንሲቲቲት/ ቅድመ ኮለጅአማርኛ/ደበበ ሰይፉ/ ዘርሁን አስፋሁ፣ስነ-ጽሑፍ መሠረታዊያን፣/2000/ |
| | ሰዋሰዉ | ሰዋሰዉ | የዓ.ነገር አይነቶች፣እማረያዊና ፍካረያዊ ፍች | |
| | ስነ-ጽሑፍ | ስነ-ጽሑፍ | ፈሊጣዊ አነጋገሮች | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 4 | አንብቦ መረዳት መናገርመጻፍ | ቋንቋ | ምንባብ፣መዝገበቃላት | ኮለጅአማርኛ/ደበበ ሰይፉ/ አበበ ጎይለ ጓርግስ ቅድመ ኮለጅ አማርኛ ለ11ኛና12ኛ የተዘጋጀ |
| | ሰዋሰዉ | ሰዋሰዉ | ዓ፣ነገሮች፣ሥርሃተ ነጥቦች | |
| | ስነ-ጽሑፍ | ስነ-ጽሑፍ | ----------- | |
| 5 | አንብቦ መረዳት መናገር፤መጻፍ | ቋንቋ | ቀና አመለካከት ሚለዉ ምንባብ | የስነ-ጽሑፍ መሠረታዊያን/ዘርሁን አስፋዉ/ |
| | ሰዋሰዉ | ሰዋሰዉ | ዓ፣ነገር፣ሐረጋት | |
| | ስነ-ጽሑፍ | ስነ-ጽሑፍ | ዘይበዎች፣ምሳለያዊ አነጋገሮች | |

በተደጋጋሚ በሁሉም ምዕራፍ የቀረቡት የትምህርት ይዘቶች፤ቋንቋ፣ሰዋሰዉ እና ስነ-ፅሑፍ ስሆኑ እነኝን ይዘቶች ተግባራዊ ለማድረግ የተጠቀሙ የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ደግሞ፤የተመረጡ ምንባብ፣ሐረጋት፣ዓ.ነገሮች፣የተዘጋጀዉ የድርሰት አይነቶች፣ዘይቤዎች፣ ምሳለያዊ አነጋገሮች፣መዝገበ ቃላት፣ጋዘጦች፣መጽሔቶች፣ጋዘቶች፣ልቦለዶች፣በባህላዊ ጋብቻ ዙርያ የቀረቡ ቃላዊ ግጥሞች፣የአንቀጽ ቅርፆች፣እማረያዊና ፍካረያዊ አነጋገሮች፣ፈሊጣዊ አነጋገሮችና ሥርዓተ ነጥቦች ናቸዉ።እነኝ የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ መሣርያዎች በግልጽ የተቀመጡ ሳይሆን በትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች ዉስጥ የተጠቀሱ ናቸዉ። ምንጭ የኢትዮጽያ ፌደራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚንስቴር /2007፣74-90/

ስለሆነም በሠንጠረዥ አስራ አምስት ላይ እንደሚታየው በአስረኛ ክፍል የአንደኛዉ መንፈቀ ዓመት መርሐ ትምህርት ውስጥ ሠላሳ ዓይነት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እንዲያገለግሉ ተጠቁመዋል።በአንፃሩ ደግሞ የ2013 ዓ.ም.የመምህራን የትምህርት ዕቅድ ውስጥ ሁለት የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ብቻ በአጋዥነት እንዲያገለግሉ ተደርገው ተጠቁመዋል። በዕርግጥ በመምህራኑ በተዘጋጀው የአንደኛዉ መንፈቀ ዓመት ዕቅድ ላይ የተመለከቱትን የትምህርት ይዘቶችን ስናይ ሁሉም በመረጃ መሣሪያ መደገፍ የነበረባቸው ሲሆኑ በዝግጅት ማነስና መርሐ ትምህርት ባለመኖሩ ምክንያት የተነሳ ያለመርጃ መሣሪያ

ታቅደዋል፡፡የተጠቀሱትም በመርሓ ትምህርት ውስጥ ከተጠቆሙት ጋር  የይዘትም ሆነ የቅርጽ ተመሳስሎ የላቸዉም፡፡

በአጠቃላይ መግለጫዎቹ የሚያመላክቱት ለሁለቱም ክፍሎች በተዘጋጁት መርሓ ትምህርቶች ውስጥ በተዘረዘሩት የትምህርት ይዘቶች፣ለይዘቶቹ ማስተማሪያ በተጠቁሙት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፣መምህራኑ ያለ መርሓ ትምህርት ባዘጋጁት የመንፈቀ ዓመት ዕቅዶች ላይ በተጠቆሙት ይዘቶችና የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መካከል የታየው መመሳሰል እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ መረዳት ተችለዋል፡፡

በተጨማርም በመርሓ ትምህርት ዉስጥ የተጠቀሱት የትምህርት መርጃ መሣርያዎች እና በመምህራን የተዘጋጀዉ መንፈቅ ዓመት ዕቅድ ስታይ በቁጥርም ሆነ በዓይነት የማይመሳሰል መሆኑ መረዳት ተችለዋል፡፡ለዚህ ጉዳይ እንደ ምክንያት የሆነዉ ደግሞ መርዓ ትምህርት አለመኖሩ ነዉ፡፡

### 4.3.1. የመምህራንን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃት የሚወሰኑት ተላውጦዎች /Variables/

በዚህ ክፍል በጥናቱ የተካተቱ ታላሚ መምህራን የቋንቋ ትምህርት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ምን እንደሚመስልና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎ የብቃት ደረጃ በምን በምን መልክ ሊገለፅ እንደሚችል በዝርዝር ተገልጿል፡፡ በዚህም ዙሪያ የተሰበሰቡት መረጃዎች በሁለት መንገድ ተከፍለው ተብራርተዋል፡፡ እነዚህም በግለሰባዊ ተላውጦዎች ዙሪያ እና በተቋማዊ አመራሩ አካላት (በትምህርት ቤት አመራር አካላቱ) ባሉ ተላውጦዎች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው፡፡

### 4.3.1. የመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ፣

የቅድመ የሥራ ላይ ሥልጠና ለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተግባራዊነት፣ውድቀትም ሆነ ዕድገት፣እውቀትና ብቃት በጣም አስፈላጊና ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው፡፡የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም የሚጎለብተው ለመምህራን በሚሰጥ ቅድመ ሥራ ላይ ሥልጠና እና በሥራ ላይ በሚያደርጉት ተግባራዊ ልምምድ መሆኑ እሙን ነዉ፡፡በመሆኑም ከዚህ አንጻር ለታላም ትምህርት ቤቶች መምህራን የቅድመ ሥራ ላይ ሥልጠና ማግኘታቸዉንና አለማግኘታቸዉን ቀጥለዉ በሚቀርበዉ ሠንጠረዥ እንመልከት፡፡

ሠንጠረዥ4.15.

የታላሚ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያን በተመለከተ የቅድመ ሥራ ላይ ሥልጠና፣

| መምህር | ዕድሜ | ፆታ | የትምህረት ደረጃ | በዋናነት የሰለጠኑት የትምህርት መሰክ | የአግልግሎት ዘመን | | | | የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን በተመለከተ ቅድመ ሥራ ላይ ስልጠና ራሱን በቻለ በኮርስ ደረጃ ወስደዎታል; | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | በሰርት ፍከት | በዲፐ ሎማ | በዲ ግሪ | ድምር | አዎ | ለም |
| 1 | 57 | ወ | ዲግሪ | አማርኛ | 11 | 13 | 10 | 34 | - | የለም |
| 2 | 48 | ወ | ዲግሪ | አማርኛ | 9 | 10 | 9 | 28 | - | የለም |
| 3 | 46 | ወ | ዲግሪ | አማርኛ | - | 10 | 13 | 23 | - | የለም |
| 4 | 42 | ወ | ዲግሪ | አማርኛ | - | 7 | 10 | 17 | - | የለም |
| 5 | 43 | ወ | ዲግሪ | አማርኛ | - | - | 12 | 12 | - | የለም |
| 6 | 40 | ወ | ዲግሪ | አማርኛ | - | - | 9 | 9 | - | የለም |
| 7 | 41 | ወ | ድጊሪ | አማርኛ | - | - | 9 | 9 | - | የለም |
| 8 | 44 | ወ | ዲግሪ | አማርኛ | - | 7 | 8 | 15 | -- | የለም |
| 9 | 49 | ወ | ዲግሪ | አማርኛ | - | 9 | 14 | 23 | - | የለም |
| 10 | 46 | ሰ | ዲግሪ | የት.አስተዳደር | 13 | 5 | 6 | 24 | - | አዎ |

ከዚህ በላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ሁሉም ታላሚ መምህራን የዲግሪ ምሩቃን መሆናቸውንና በዋናነት የሠለጠኑበት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መሆኑን፣ዘጠኙ (90%) ታላሚ መምህራን የቅድመ ሥራ ላይ ሥልጠና የትምህርት መርጃ መሣሪያን በተመለከተ ራሱን የቻለ ኮርስ እንዳልወሰዱ ስገልጹ፣አንዱ የትምህርት አሰተዳደር የወሰደዉ (10%) ከሞላ ጎደል ወስጃለዉ ስል ገልጸዋል፡፡ስለዚህ በምዕራፍ ሁለት ተራ ቁጥር 2.5.3 ላይ መምህራን ሥልጠናን ባለማግኘታቸው ምክንያት በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚፈጥር ተገልጿል፡፡

ከዚህ አንፃር ታላሚ መምህራን ሥልጠና ያልወሰዱ መሆናቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃትን የሚወስን ተላውጦ ነው፡፡

### 4.3.2 የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀም በተመለከተ የታላሚ መምህራን የሥራ ላይ ሥልጠና፤

አንድ ባለ ሙያ በሚያገኘዉ ቅድመ ሥራ ስልጠና ብቻ በቂ ሆኖ የሚወጣ አይደለም፡፡ይልቁስ ተመርቀው ወደ ሥራው ዓለም ከተሠማራ በኋላ የሙያ ላይ ሥልጠና ወይም የተሐድሶ ሥልጠና በሥራ ላይ ሆነው ማግኘት ይኖርበታ፡፡ስልጠናዉም የሰልጣኙን ብቃትና ክህሎትን ያጠናክራል፡፡በመሆኑም ተጠኝዎቹ መምህራን የሥራ ላይ ሥልጠና መካፈላቸዉና አለመካፈላቸውን ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፤

**ሠንጠረዥ 4.16**

**የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ መምህራን ያገኙት የሥራ ላይ ሥልጠና፣**

| መልስ የሰጡ መምህራን ብዛት | ሥልጠና የወሰዱበት ዙር ብዛት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከአንድ ጊዜ በላይ የተካፈሉ | | አንድ ጊዜ ብቻ የተካፈሉ | | ምንም ያልተካፈሉ | |
| | በቁጥር | በመቶኛ(%) | በቁጥር | በመቶኛ(%) | በቁጥር | በመቶኛ(%) |
| 10 | 1 | 10% | 2 | 20% | 7 | 70% |

ከዚህ በላይ ካለው ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው ከአስሩ የጥናቱ ታላሚ መምህራን መካከል አንዱ (10%) መምህር የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ ወደ ሥራ ዓለም ከተሠማሩ በኋላ ከአንድ ጊዜ በላይ ስልጠና እንዳገኘ፤ሁለት መምህራን (20%) አንድ ጊዜ

የሥራ ላይ ሥልጠና  እንዳገኙና ሌሎቹ ቀሪ ሰባት መምህራን (70%)ምንም ዓይነት ሥልጠና ያልተካፈሉ መሆናቸዉ በቃለ መጠይቅ ጥያቄ ተራ ቁጥር 10 ላይ ተገልፀዋል፡፡ በተመሣሣይ በፅሁፍ መጠይቅ ተራ ቁጥር 18 የቃለ መጠይቁን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ለወጣው ጥያቄ የሰጡት ምላሽም ከዚህ ጋር አንድ ዓይነት መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ስለዚህ በምዕራፍ ሁለት ተራ ቁጥር 2.5.3 ላይ ለመምህራን የሥራ ላይ ሥልጠና ማግኘት ከወቅታዊ መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምና የማስተማር ዘዴ ጋር እንዲተዋወቅ ያግዛል፡፡ በቅድመ ሥራ ላይ በጥልቀት ያላዩትን (በንድፈ ሐሳብ ብቻ ገረፍ ገረፍ አድርገው የታለፉትን) የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀም እውቀትና ክህሎት ለመከለስ እድል ይሰጣቸዋል፡፡

ነገር ግን የሥራ ላይ ሥልጠና አለማግኘት አሉታዊ ተፅዕኖ አለው፡፡ ከዚህ አንፃር የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃትን የሚወስን ተላውጦ ነው፡፡

### 4.3.3 በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም የቋንቋ መምህራኑ ፍላጎትና ተነሳሽነት፤

የቋንቋ መምህራኑ የቅድመ ሥልጠናም ሆነ የሥራ ላይ ሥልጠና ማግኘት በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም በቋንቋ መምህራኑ ፍላጎትና አጠቃቀም ረገድ ምን? ለምንና እንዴት? እንደሚጠቀሙ ዕውቀትና ክህሎት ስለሚኖራቸው የሥራ ፍላጎትና የተነሳሽነት ስሜት ይፈጥርላቸዋል፤ከዚህ በተጨማሪ በትምህርት-መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ የሚያስተምሩት የቋንቋ ትምህርት በተማሪዎች ላይ የሚፈጥረውን የትምህርት አቀባበል ለውጥና ዕድገት ሲመለከቱ ሁልጊዜ የመጠቀም ፍላጎት ተነሳሽነት ያድርባቸዋል፡፡በአንፃሩ ግን የቅድመ ሥራ ላይ ሥልጠናም ሆነ ወደ ሥራ ዓለም ከተሰማሩ በኋላ ሥልጠና ያልወሰዱ መምህራን ስለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ለሚኖራቸው ፍላጎትና ተነሳሻነት ዝቅተኛ  ያደርጋል፡፡

ቀደም ሲል በሠንጠረዥ አስራ ሰባት እና በሠንጠረዥ አስራ ስምንት ላይ በተገለፀው መሠረት የጥናቱ ታላሚ የቋንቋ መምህራን  አስሩ  በመደበኛ ቅድመ መምህርነት ሥልጠና ወቅት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የሚመለከት ራሱን የቻለ ኮርስ እንዳልተማሩና ከአብዛኞቹ ታላሚ የቋንቋ መምህራን መካከል ደግሞ ሰባቱ (70%) ወደ ሥራው ዓለም ከተሠማሩ በኋላ ምንም ዓይነት የትምህርት መርጃ መሣሪያን የሚመለከት የሥራ ላይ ስልጠና እንዳልተካፈሉ፣ሁለቱ መምህራን (20%) ለአንድ ጊዜ ያህል የስራ ላይ ሥልጠና እንደወሰዱ ሌላው ቀሪው አንድ መምህር(10%) ከአንድ ጊዜ በላይ የሥራ ላይ ሥልጠና እንዳገኘ

በሠንጠረዥ አስራ ሰምንት ላይ ተገልጿል፡፡ ይህንን በተመለከተ Newby et al. (1996:263) በምዕራፍ ሁለት፣ መምህራን ወደ ሥራ ዓለም ከመሠማራታቸው በፊት በሥልጠና ወይም በሥራ ላይ እያሉ ሥልጠና በመስጠት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ክህሎት ማስጨበጥ አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ይሁን እንጂ አብዛኞቹ ታላሚ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያን የሚመለከት ቅድመም ሆነ የሥራ ላይ ሥልጠና ያልተሰጣቸው መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ይህም በቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ ላይ መምህራኑ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለመጠቀም ላላቸው ፍላጎትና ተነሳሽነት ዝቅተኛ ለመሆን ምክንያት (ተላውጦ) ሊሆን ይችላል፡፡

## 4.3 ተቋማዊ ተላውጦዎች

### 4.3.1 ቦታን በተመለከተ

የሁሉም የጥናቱ ታላም ትምህርት ቤቶች ክፍል መደበኛ መማርያ ክፍሎች ናቸዉ፡፡ይህ ደግሞ በተለያየ ሠለዳዎች፤የሚደመጡ፣የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ-መሣርያዎችን ለመጠቀም ወደ መማሪያ ክፍሎች ተሸክሞ ማመላለስ አስቸጋሪ ነዉ፡፡ይህንን አስመልክቶ በምዕራፍ ሁለት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀም በተመለከተ ከተገለጹት ጠቃሚ እሴቶች መካከል ለመያዝና ለመፈተሽ የሚሰጡት ዕድል፣ በመስህብነታቸው ምክንያት ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋሉ በመባል ተገልጾ ነበር፡፡ነገር ግን ቦታ ከለለው ለመያዚም ሆነ ከቦታ ቦታ ለማመላለስ፣ለማስዋብና ሳብ ለማድረግ አሰቸጋር ስለምሆን በትምህርት መርጃ መሣሪዎች አጠቃቀም ላይ አንድ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ ይህም መምህራን የሚፈጠረውን ሁኔታ በመፍራት በተገቢው መንገድ የትምህርት መርጃ መሣሪያን እንዳይጠቀሙ ጫና ሊያመጣ እንደሚችል ያመላክታል፡፡ ከዚህ አንፃር ቦታ አንድ ተላውጦ ነው፡፡

### 4.3.2 በጀትን በተመለከተ

በመሠረቱ መምህራን  የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የሚያገኙት በግዥና በስጦታ ነው፡፡በግዥ ከሆነ ደግሞ ባጀት ያስፈልጋል፡፡ይህንን በሚመለከት ታላሚ ለሆኑት መምህራን በተደረገላቸው ቃለ-መጠይቅ በጥያቄ ተራ ቁጥር አስራአንድ ላይ  ሁሉም መምህራን የሰጡት ምላሽ የሚጠቀሙበትን የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለማግኘት የበጀት ችግር እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡በስጦታ መልክ ደግሞ በግልም ሆነ በቡድን የጤየቀና የተጠየቁ አካል የለም፡፡ይህ ደግሞ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃት ሊወስኑ የሚችሉ በትምህርት ቤት በኩል የሚታዩ ተላውጦዎች ሊሆን ይችላል፡፡

## 4.2 የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የአማርኛ ቋንቋ መምኅራን የትምህርት መርጃ መሣርያ አጠቃቀም ለመፈተሽ ነበር፡፡ ይህንን ለመፈተሽ የክፍል ውስጥ ምልከታ፣የጽሁፍ መጠይቅና በቡድን ውይይት አመካኝነት መረጃዎች ተሰብስበው የተገኙ ውጤቶች ትንተናው በሚያነሳ መሠረት በሠንጠረዥ ውስጥ በቁጥርና በመቶኛ ስሌት (%) ተተንትነዋል፡፡ በዚህ መሠረት የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያ አጠቃቀም ምን ይመስላል? የሚል ሲሆን ጥያቄውን ለመመሌስም መረጃው በገላጭና ስታትስቲክስ ተተንትኗል፡፡ በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች በተደረገው የአስር አስር ጊዜ የክፍል ውስጥ ምልከታ በዘጠነኛ ክፍል ሁለት ጊዜ(20%)በአስረኛ ክፍል ሦስት ጊዜ (30%) መምህራኑ በትምህርት መርጃ መሣሪያ ታግዘዉ እንደሚያስተምሩ ታውቆዋል፡፡ በአንፃሩ በ9ኛ ክፍል ስምንት ጊዜ (80%)፣በ10ኛ ክፍል ደግሞ ሰባት ጊዜ (70%) ያለ ትምህርት መርጃ መሣሪያ በቃል ብቻ እንዳስተማሩ (በሠንጠረዥ 4.1)ላይ ባለው ውጤት ማወቅ ተችለዋል፡፡

የተተነተነው መረጃ እንደሚያሳየው ከተጠቀሙት ትምህርት መርጃ መሳርያዎች (51.54%)ቱ በቂ የጥራት ደረጃ ያለው የትምህርት መርጃ-መሳርያ የተጠቀሙ ሲሆን (42.85%)ቱ ደግሞ አነተኛ የጥራት ደረጃ ያለው የትምህርት መርጃ መሣርያ እንደተጠቀሙ የውጤቱ ትንተና ያመላክታል፡፡ ነገር ግን በጥናቱ ምዕራፍ ሁለት 2.2.1 ላይ እንደተገለጸዉ ለትምህርት መርጃ መሣርያዎች መምረጫ የሚውሉ መመዘኛዎች መሠረት ለተማሪዎች የሚታይ እና ሰፋ ባለ መጠን መዘጋጀት እንዳለበት ተጠቅሷል፡፡ ይሁን እንጅ የጥራት ደረጃው ሲታይ ኋላ ለተቀመጡ ተማሪዎች ስለማይታይ አነስተኛ የጥራት ደረጃ ያለው የትምህርት መርጃ መሣርያዎች መጠቀማቸውን ማረጋገጥ ተችለዋል፡፡

በተመሳሳይ ከተጠቀሙት መርጃ መሣርያዎች መካከል በዘጠነኛ ክፍል 3(100%) አነስተኛ መጠን ያለው የትምህርት መርጃ-መሣርያዎች ሲጠቀሙ አስረኛ ክፍል ደግሞ2(50%) በቂ፣2(50%)ቱ ደግሞ አነስተኛ መጠን ያለው የትምህርት መሣርጃ መሣርያ መጠቀማቸው ታውቋል፡፡

በአጠቃላይ መምህራን በክፍል ውስጥ ለማስተማሪያነት የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በጥራትም ሆነ በመጠን አነስተኛ ደረጃ ያለውን የትምህርት መርጃ-መሣርያ እንደሆነ ማወቅ ተችለዋል፡፡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠን አነስተኛ መሆንና ጎልቶ

አለመታየት ወደ ኋላ ለሚቀመጡ ተማሪዎች ለእይታ ስለሚያስቸግረዉ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ አማካይነት ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ሲያዛባ ፣ ያለመጠቀማቸው ደግሞ ትምህርቱን ተጨባጭ፣ሳብ እና ስኬታማ አያደርግም።

መምህራኑ የተጠቀሙትም የትምህርት መርጃ መሣርያዎች የተዘጋጀው በመምህራኑ አስተባባርነት በየ ዓመቱ ተማሪዎች እድሰሩ በማድረግ የተሠራ መሆኑ፣አስፈላጊና አጋዥ ብሆንም ጥራቱ እና መጠኑ እምብዛም አጥጋብ እዳልሆነ መረዳት ተችለዋል።

መምህራን በቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ ዕሙን ነው። መምህራን የቋንቋውን ትምህርት ብቃት ባላቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አስደግፈው ማቅረብ ለዓላማው ስኬት ወሳኝ ነው። ይህ ደግሞ የመምህሩን ችሎታ ይጠይቃል።በመሆኑም መምህራን ከተጠቀሙባቸው አራት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች (25%)ቱ እጅግ በጣም ጥሩ፣(12.5%)ቱ በጣም ጥሩ፣(12.5%)ቱ በአነስተኛ ብቃት መጠቀማቸው ማወቅ ተችለዋል። ይህ ደግሞ በምራፍ 2.5.3 እንደተገለጸው የመምህራኑ የትምህርት-መርጃ መሣርያ አጠቃቀም ብቃት ማነስ፣ የመምህሩ ችሎታ ማነስ ወይም ግድለሽነት፣የስልጠና ዕጥረትእና የመጠቀም ብቃት ማነስ መሆኑን ያመላክታል።

የተጠቀሙት መርጃ መሣሪያዎችም ሁለት ብቻ«እጅግ በጣም ጥሩ»በሆነ ሁኔታ የተገለገሉባቸው ቢሆንም አጠቃቀማቸው ሙሉ በሙሉ ብቃት አለው ለማለት አያስደፍርም።ይህ ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው የመምህራኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ብቃት ማነስ ሊሆን የሚችለው የመምህሩ ችሎታ ማነስ ወይም ግድየለሽነት፣የስልጠና እጥረት፣እና የትምህርት መርጃ መሣርያን በተገብዉ ሁነታ መምረጥ አለመቻል መሆኑ Aggrawal(1996:159-161)ላይ ተገልጸዋል። የመጠቀም ብቃት ማነስ ደግሞ ጤናማ የክፍል ውስጥ መስተጋብር እንደማይፈጥር፣ የመማር ፍላጎት እንደማይቀሰቅስ፣ በንቃት እንደማያሳትፍ ማወቅ ተችለዋል።

አግልግሎት ላይ የዋሉት የትምህርት መረጃ-መሣርያዎች አነስተኛ መስተጋብር ፈጥሮዋል። በመሠረቱ በስራቱ የተመረጡትና የተዘጋጁ የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ታላምውን የትምህርት ዓላማ በተጨባጭ እንድታይ፣የተሳካ እንድሆን፣የመማር ፍላጎት የምያነሳሳ፣የጽንስ ሓሳቦች ዕውነታ እንድረዱ የምያደርግ፣የፈጠራ ችሎታ የሚያሳድግ፣ልምድ የሚያጓላብት፣ወዘተ

ፋይዳዎች ብኖሩትም ተማሪዎች በነቃ አዕምሮአቸዉ ከመመልከት በስተቀር በቋንቋዉ የመጠቀም ችሎታ ስለሌላቸው ጥሩ መስተጋብር አልተፈጠረም፡፡

ጥቅም ላይ የዋለዉ መርጃ መሣሪያዎች በተማሪዎች መካከል የእርስ በርስ መሰተጋብር እንድፈጠር የሚያሳይ እና ተማሪዎቹ በቋንቋዉ እድጠቀሙ ሁነታዎች ብመቻቹም የእርስ-በእርስስ መስተጋብር እንዳልተፈጠረ መረዳት ተችለዋል፡፡ ይህ ደግሞ በምዕራፍ ሁለት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአግባቡ የመጠቀም ፋይዳ ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዱ ጤናማ የክፍል ውስጥ መስተጋብር እንዲፈጠር ማበረታታት እንደሆነ የሚያመላክት ብሆንም ከተብራራው ሀሳብ አንፃር ሲታይ ደግሞ ክፍተት እንዳለው ለማወቅ ተችሎዋል፡፡ በዋናነትም መሰተጋብ እዳይፈጠር ያደረገው ምክንያት ለቋንቋው ትምህርት ትኩረት ስላልሰጡት ይመሥላል፡፡

ተማሪዎች ታላሚውን ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ታግዞ የቀረበላቸውን የትምህርቱን ዋና ዓላማ ምን ያህል እንዳወቁት ለመገምገም ከመምህራኑ የቀረበላቸው ጥያቄዎች ተረድተው መልስ ለመስጠት በጣም ፈጣን በሆነ መልኩ ብሞክሩም በቋንቋው የመጠቀም ችሎታቸው በጣም አናሳ መሆኑ መረዳት ተችለዋል፡፡ሆኖም ግን በቋንቋው የመጠቀመው ችሎታ ብኖራቸው በጣም ፈጣን በሆነ ጊዜ መልስ መስጠት እንደሚችሉ ተረጋግጠዋል፡፡

በዕለቱም በመማር-ማስተማር ሂደት በአገልግሎት ላይ የዋለውን የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ ማራኪነት በሠንጠረዥ 4.1.7 ላይ የቀረበው ለአብዛኞቹ ተማሪዎች የደስታ ስሜት እንደፈጠረላቸው መረዳት ተችለዋል፡፡በአጠቃላይ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የደስታ ስሜት መኖራቸው በምዕራፍ ሁለት በተራ ቁጥር 2.2.2 ከተገለፀው ሀሳብ ጋር የተስማማ መሆኑን ያመላክታል፡፡

የክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደት የተሟላ ሆኖ ብቁርብ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ፣ በተማሪዎች አዕምሮ ላይ አዳዲስ ዕውቀቶችና ክሂሎች እንዲቀርጹ፣ተቀርፀውም በተገቢው ጊዜና ቦታ በተግባር ብገለገሉ፣የተለያዩ ተግባራትንና ልምዶችን በማቅረብ የተማሪዎችን ፍላጎት በማነሳሳት፣ ትኩረታቸውን ወጥሮ መያዝና ወደሚፈለገው ግብ እንዲያመሩ በክፍል ውስጥ ጥሩ ተሳትፎ እንዲያሳዩ መምህራን የሚገለገሉበት የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያና አጠቃቀም ወሳኝነት እንዳለው ታውቋል፡፡ በተመሳሳይ ሠንጠረዥ 4.1.8 የሚያሳየው የቋንቋ

ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ተጠቅሞ ማስተማር በቋንቋው የመጠቀም ችሎታቸው በጣም አናሳ ብሆንም ተማሪዎች በክፍል ውሰጥ የምያሳዩት የተሳትፎ እንቅስቃሰያቸዉ«ፈጣን»ሆኖ መገኘቱን ማወቅ ተችለዋል፡፡

ምልከታ በተደረገበት ወቅት የተጠቀሙባቸው የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በዕለቱ ሊሰጥ የታቀደውን ረቂቅ የትምህርት ይዘት ተጨባጭና ግልፅ ከማድረግ አኳያ ምን ያህል ተገቢነት እንዳላቸው በክፍል ውስጥ ምልከታ ተካሂደው ውጤቱ አብዛኛዎቹ መምህራን እጅግ ውስን በሆኑ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አልፎ አልፎ ቢጠቀሙም፣ የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ከማሳካት አኳያ የተደረገው የአጠቃቀም ብቃት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ ተገቢነት እንዳላቸው ለመረዳት ተችለዋል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም በጥቂት መምህራን ላይ የታየው የቅድመ ዝግጅት ብቃት ማነስን መሆኑንን መገንዘብ ተችለዋል፡፡

በእውነተኞ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም ቶሎ ሊረሱ የሚችሉትን ረቂቅ የሆኑ አስተሳሰቦችን፣የነገሮችን እንቅስቃሴ፣ጥልቀት፣ክብደት፣ጠረን፣ስሜት፣ጣዕምና፣ቀለም በተጨባጭ ከማስረዳት አኳያ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለውና ከተቻለ አዲስና ወጥ በሆነ እውናዊ የትምህርት ልምምድን ተጠቅሞ ማስተማር ሌሎች ወካይ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መጠቀም የተሻለ እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት በተራ ቁጥር 2.2 ላይ ተገልጾ ነበር፡፡ከዚህ አንፃርም የጥናቱ ማብራርያ እንደሚያመለክተው ከተጠኝ ትምህረት ቤቶች በምልከታው ጊዜ የታዩት እውነተኛ የሆነ የትምህርት-መርጃ መሣርያ በዘጠነኛ ክፍል አንዱ (33.33%)እውነተኛ ሲሆን፣በአስረኛ ክፍል ከተዘጋጁት አራቱ የትምህርት መርጃዎች መካከል አንዱ ብቻ(25%) እውነተኛ መሆኑ ማወቅ ተችለዋል፡፡ከዚህ መረዳት የሚቻለው መምህራን በቂ ስልጠናና የልምድ ልውውጥ ቢያደርጉት አስፈላዚውን የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ማዘጋጀት እንደሚችሉ አያጠራጥርም፡፡

ከታላሚ ትምህርት ቤቶች ለናሙና በአንዱ (በአርጆ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት እቅድ ውስጥ የተጠቆሙትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ብዛት በዓይነት ተለይቶ ሲቃኝ በዘጠነኛ ክፍል ላይ ከተጠቀሱት አስራ ሦስት የትምህርት መርጃ መሳርያዎች መካከል አንዱ (7.7%) የሚታይ፣ሁለት (15.38%) የሚደመጥ ሲሆን የተቀሩት(76.92%) የሚደመጡና የሚታዩ የትምህርት መርጃ መሣርያዎች እንደሆኑ፣ በአስረኛ ክፍል ላይ ከተጠቀሱት አስር የትምህርት መርጃ መሣርያዎች መካከል ሁለቱ (20%) የሚታይ የትምህርት መርጃ መሣርያ መሆኑ ፣ሁለቱ (20%) ቱ ደግሞ የሚደመጥ እና

የተቀሩት  ትምህርት መርጃ-መሣርያዎች ደግሞ ስድስቱ 60% የሚደመጥና የሚታይ መሆኑ ከሠንጠረዥ 4፣11 በተብራራው መረዳት ተችለዋል። በመሆኑም በትምህረት ዕቅዱ ላይ የተጠቀሱትና የተጠቀሙት የቋንቋ ትምህርት መርጃ-መሣርያዎች ታላሚውን የትምህርቱን ይዘት ተግባራዊ ለማድረግ በቂ እንዳልሆነ መረጋገጥ ተችለዋል።

በአጠቃላይ በተጠኘ ትምህርት ቤቶች የተጠቀሙትና በ2013 ዓ.ም በመንፈቀ ዓመቱ ዕቅድ ላይ የተጠቀሱት የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ማለትም የሚደመጥ፣የሚደመጥና የሚታይ በበቂ ሁነታ እንዳልተጠቀሙ ያመለክታል።ይህ ደግሞ በምዕራፍ ሁለት 2.1.2 ላይ እንደተገለጸዉ የአንድን ድርጊት ወይም የአንድን ነገር ተከተላዊ ዕደት በተማሪዎች አዕምሮ ውስጥ ምናባዊ ምስል በመፍጠር ሓሳቡ በአዕምሮ እየተደጋገመ እንድመጣ አያደርግም፤የተማሪዎች የማሰብ ችሎታ አያፋጥንም፤ከአከባብያቸው ጋር መስተጋብር አያደርጉም፤አከባብያቸውን አይወዱም፤ አያደንቁም፤የመማር ፍላጎትን አይቀሰቅስም፤መምህራን የሚያቀርቡላቸውን የትምህርት ይዘቶች ተአማን (እዉነተኛ) አያደርግም፤ተገብ ትርጉም እንድኖራቸው አያስችልም (Malawi institute of Education20003)።

በምልከታውም ወቅት  መምህራን በኅትመት ውጤቶች በመጠቀም ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ለማወቅ ተችለዋል። እንደ ዋና ዋና ችግሮች የተጠቀሱትም  መጽሔቶች፤የድምፅ ቀረጻ መሣርያዎች እና የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ከአከባብያቸው  ማግኘት እንደማይችሉ ታውቆዋል። ስለሆነም መምህራን ምንም ዓይነት የኅትመት ውጤቶች ያልተጠቀሙና በዕቅዳቸው ውስጥም ያልተካተተ መሆኑን  በማብራርያው ላይ ተገልፀዋል። እንድሁም  የቋንቋ መምህራኑ በሠሌዳዎች የመጠቀም ልምዳቸው እጅግ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል።

 መረጃው ተተንትኖ የተገኘው ውጤት እንዳሳየውም  በትምህርት መርጃ መሣርያዎችን ተጠቅመው ማስተማር ከፍተኛ ጠቀመታ እንዳለው ሁሉም ተጠኝዎች ይስማሙታል። የተስማሙበት ምክንያት ስገልጹትም  የአንድን ድርጊት ወይም የአንድን ነገር ተከተላዊ ሂደት በተማሪዎች አዕምሮ ውስጥ ምናባዊ ምስል በመፍጠር ሓሳቡ በአእምሮ እየተደጋገመ እንድመጣ ያደርጋሉ።ይህም ተተኳር የትምህርት ይዘቱን ተጨባጭና አይረሴ ያደርጋል፤ረቂቅ የሆኑ የትምህርት ሐሳቦችን በተጨባጭ በማቅረብ ተማሪዎች ያለ ምንም ችግር የትምህርት ይዘቶችን እንድረረዱና የተማሪዎችን የማስታወስ ችሎታ በማፋጠን ተማሪዎች ከአከባብያቸው ጋር መስተጋብራዊ ግኑኝነት እንድያደርጉና አከባብያቸውን እንድወዱ እንድሁም፣ እንድያደንቁ

በማገዝ ተማሪዎች ክሂሎትን ለምሳሌ፣የማዳመጥ፣የምልክት ወይም በእጅ የመጠቀም፣የመገጣጠም፣ችግር የመፍታት፣አብሮ የመስተራት ልምዶችን እድያዳብሩና የመማሪ ጉጉት በመቀስቀስ ለመማር የሚኖራቸዉን መነሳሳት በመጨመር፣በተማሪዎችና በመምህራን ዘንድ ፈጠራን ለመቀስቀስ ፣ መምህራን የሚያቀርቡአቸው የትምህሪት ይዘቶች ለተማሪዎች ተአማኒ (እዉነተኛ)፣ተገብ እና ትርጉም ልኖረው እንደሚችል መረዳት ተችሏል ። ጠቃምነቱን ይረዱ እንጅ የልምድ ልውውጥ እንደ ለላቸው፣በትምህርት በታቸው የተመቻቸ ሁነታዎች እንደሌለ፣በየትምህርት በታቸው የመምህሩ መምህርያ እና መርሓ ትምህርት እንደሌለ፣የስራ ላይ ስልጠና እንደሌላቸው ተጠኝዎቹ በቡድናቸው ውይይት ላይ አበክረው እንዳነሱት ከጥናቱ ውጤት መረዳት ተችለዋል። በተጨማርም በየትምህርት በቱ የተመቻቸ የትምህርት መርጃ መሣርያዎች አለመኖሩ እና ባጀት አለመመደቡ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም ብቃት ሊወስኑ የሚችሉ በትምህርት ቤት በኩል የሚታዩ ተላውጠዎች ሊሆኑ እንደምችሉ ከጥናቱ ትንተና ውጤት ማወቅ ተችለዋል።

በአጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን በተገብ መጠቀማቸው እና አለመጠቀማቸውን፣የአጠቃቀማቸውን ሁነታ እና ደረጃ፣እንድሁም ለመጠቀም እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ተግዳሮቶች ተለይተው ተብራርተዋል። በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀም አሰመልክተው የሚመለከታቸው አካላት ትኩረት እንድሰጡባቸው ቢደረግ አዎንታዊ ውጤት ያለው በመሆኑ ተገቢ ትኩረት ተሰጥቶት ተግባራዊ ቢደረግ የተሻሌ ውጤት ሊመጣ እንደሚችል ከተገኘው መረጃዎች ትንተና ውጤት ለመገንዘብ ተችሎል።

## ምዕራፍ አምስት

## 5.ማጠቃለያና  የመፍትሔ ሀሳቦች

በዚህ  ምዕራፍ የተነሱት  ዋና ዋና ነጥቦች አጠር ተደርገው ከተዳሰሱ በኋላ በተገኙት ማብራሪያና ውጤት ላይ በመመስረት የመፌትሄ ሀሳቦች ተሰጥቷል።ምዕራፉ የመፌትሄ ሀሳቦቹንም ሌመስጠት ቅዲሚያ በምዕራፍ አንድ ላይ የተነሱትን  የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች በማመሊከት በእያንዳንዳቸው ስር የተገኙ ክፍተቶችና ክፍተቶቹን ሌመሙሊት ሉደረጉ የሚገባቸውን  ተግባራት በመጠቆም  ቋጭቷል።

### 5.1 ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በምስራቅ ወለጋ ዞን በአርጆ ወረዳ ሦስት ሁለተኛ ከፍተኛ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቁንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሳርያዎች አጠቃቀም ምን እንደምመስል መፈተሽ ነዉ።የተካተቱ ዝርዝር ዓላማዎችም፣

- ✓ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀም ምን እንደሚመስል ለመዳሰስ፣
- ✓ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን  በትምህረት መርጃ መሣርያዎች ሲጠቀሙ የሚያጋጥሟቸዉ ችግሮች ካሉ  ለመለየት፣
- ✓ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን  ስለ ትምህርት   መርጃ መሣርያዎች አጠቃቀም በተመለከተ ያላቸውን   ግንዛበ መዳሰስ፣
- ✓ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣርያን ለመጠቀም ያላቸዉን ፍላጎት ለማወቅ፣

.በመሆኑም መምህራኑ ተገቢ የሆነ የትምህርት መርጃ መሣሪያ መጠቀም የሚያስችላቸውን የቅድመ ሥራም ሆነ የሥራ ላይ ሥልጠና ማግኘት የሚገባቸው ቢሆንም በቂ የሆነ ሥልጠና ባለማግኘታቸው በአጠቃቀም ረገድ ያላቸው ተሳትፎ አናሳ ሆኖ ተገኝቷል።

.የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለመጠቀም ማቀድ ብቻውን በቂ አይደለም። ዋናው ነገር የታቀዱትንና  ከየትም የተገኙትን መርጦ በመማር-ማስተማር ሂደት በክፍል  ውስጥ በአግባቡ መጠቀም ወሳኝ ነው።

ከዚህ አኳያ በተካሄዱት የክፍል ውስጥ ምልከታዎች ማረጋገጥ እንደተቻለው 12% ያህሉ በመርጃ መሣርያ የሚያስተምሩ ስሆን፣የተቀሩት 88%ቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያስተምሩት ያለ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በቃል ብቻ ነው፡፡

.መምህራን የሚጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሳቢ እንደሆኑ፣ መጠናቸው ጉልህ ሆኖ መገኘት፣መራኪና ተስማሚ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ነገር ግን የተጠቀሙትን የትምህርት መርጃ መሣርያ ከዚህ አኳያ ስታይ ሳብ እንዳልሆነ፣ጉልህ፣መራኪና ተሰማም እንዳልሆነ ማረጋገጥ ተችለዋል፡፡

.መምህራኑ የተጠቀሙት የትምህረት መርጃ መሣርያዎች እይታዊ ነዉ፡፡ነገር ግን የትምህርት መርጃ መሣርያዎች በአይነት እይታዊ፣የሚደመጡ፣የሚደመጡና የሚታዩ ተብለዉ ብከፈሉም ተጠኝ ትምህርት ቤቶች የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ-መሣርያዎች እይታዊ ብቻ ነው፡፡ከተጠቀሙት ቦነላም ተገብ የሆነ ማስቀመጫ ቦታ ስለሌላቸው ቶሎ ብለዉ እንደምበላሹ ጥናቱ አረጋግጠዋል፡፡የትምህርት መርጃ-መሣርያዎቹም የተገኙት በመምህራን አስተባባርነት ከወረቀትና ከአቡደጅ ጨርቅ በተማሪዎች የተሠሩና ቶሎ ብለው የሚበላሹ መሆናቸው በጥናቱ ምልከታ ወቅት ተረጋግጠዋል፡፡ ይህ ደግሞ ተጠኝዎቹ በቂ ዕዉቀት፣ፍላጎት እና ልምድ እንደለላቸው ለማወቅ ተችለዋል፡፡

.የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ታግዘው ለማስተማር በቅድሚያ የቋንቋ ማስተማሪያ መሣርያዎች (መርሐ ትምህርት፣ የመምህር መምሪያና የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ)ን ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ይሁንና በጥናቱ በተካተቱ ትምህርት ቤቶች ግን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መሣሪያዎች ከተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውጭ ሌሎች እንደሌሉ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ የተነሣ የመንፈቀ ዓመቱንም ሆነ የዕለቱን ትምህርት ለማቀድና በአንፃሩም በተገቢ የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለመጠቀም አስቸጋሪ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የመንፈቀ ዓመት ዕቅዳቸውም ከመርሓ ትምህርቱ ጋር የየትምህርት ቤቶቹ እቅዶች የቅርፅና የይዘት ልዩነት ይታያል፡፡

## 5.2 የመፍትሔ ሀሳቦች

ከላይ የተነሱትን ማጠቃለያ ነጥቦች መሠረት በማድረግ  የሚከተሉት የመብትሔ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል፣

- ለመምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በሚመለከት  የሙያ ላይ ሥልጠና  ቢሰጣቸው፣
- መምህራን፣ ቋንቋ ውስብስብ መሣሪያ መሆኑን ተረድተው ይህንን ውስብስብ መሣሪያ ግልፅ፣ ቀላልና ተጨባጭ በሆነ መንገድ ተማሪዎች እንዲማሩት ጥረት ቢያደርጉና መጠኑ የተሟላ፣ተገቢነት ያለዉ፣ደረጃውን በጠበቀ የቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ በመጠቀም ቢያስተምሯቸው፤
- መምህራን ያገኙትንና ያሰሩትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹን በተገቢ መንገድ ቢገለገሉበት እና የተለያዩት የትምህርት መርጃ መሣርያዎች (በሚደመጥ፣በሚደመጥና በሚታይ) የትምህርት መርጃ መሣሪያ ዓይነት በመገልገል ተማሪዎቻቸውን የተለያዩ የቋንቋ ክህሎት በሚያጎለብት መልኩ ቢያስተምሯቸው፣
- መምህራን የተጠቀሙትን የትምህርት-መርጃ መሣርያዎችን በተገብ ቦታ አስቀምጠዉ ቢገለገሉበት፣
- የሚመለከታቸው አካላት  በየትምህርት ቤቱ በቂ የቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያ መሣሪያዎች (መርሐ-ትምህርት፣ የመምህሩ መምሪያና የተማሪ መጽሐፍ) ለትምህርት ቤቶቹ በተገቢ መንገድ እንዲደርስ ቢያደርጉ፣
- መምህራን የሚገለገሉባቸውን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመጠቀም ተማሪዎች የእርስ በርስ መስተጋብራቸውና የክፍል ውስጥ ተሳትፏቸው እንዲጨምር መምህራን በብቃት ተገቢ የሆነ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም ዕውቀት እንዲኖራቸው የተለያዩ ጥረቶችን ቢያደርጉ፣ትምህርት ቤቱም ሁኔታዎችን ቢያመቻች፣
- መምህራን  የልምድ ልውውጥ ቢያደርጉ፣

- የመማርያ ክፍሎች በተገቢ ሁነታ ቢዘጋጁ፣እንድሁም የትምህርት መርጃ መሣርያዎች ማስቀመጫ ክፍል ቢዘጋጂለት፣በሚመለከታቸዉ ትምህርት ባለሙያዎች ትኩረት ቢደረግበት፣
- ስለ መርጃ መሣርያ አሰራርና አጠቃቀም አሰመልክተው በባሌሙያዎች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስልጠና ብሰጥ፣
- የሚመለከታቸው አካላት ባጀት ብበጅቱለት፣

**ዋቢ መፃሕፍት**

በድሉ ዋቅጅራ።(1996)። በሥነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር።አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት።

ባየ ይማም።(2000)።የአማርኛ ሰዋስው።አዲስ አበባ፣ እሌኒ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር።

ተስፋዬ አበራና ማረው አለሙ።(1930)።አማርኛ ቋንቋን በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የማስተማር ዘዴ።ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ፋኩልቲ፣ የአማርኛ ትምህርት ክፍል ለልዩ ዲግሪ ፕሮግራም የርቀት ትምህርት የተዘጋጀ። (ያልታተመ

ጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ። (1997) የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መፅሐፍ ዘጠነኛ ክፍል።አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ አማርኛን በማስተማር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ። (ያልታተመ)

ጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ።(1997)የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መፅሐፍ ሰባተኛ ክፍል ። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

ጎንደር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ። (1997)። የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መፅሐፍ አስረኛ ክፍል ። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

ያለው እንዳወቀ (2001 የምርምር መሰረታዊመርሆዎችና አተገባበር፣አድስ አበባ፣ንግዴማተሚያ ቤት።

ያለው እንዳወቀ። (2006)። የምርምር መሠረታዊ መርሖዎችና አተገባበር። አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚዎች።

Aggarwal, J. (1995) Essentials of Educational Technology: Teaching Learning Innovations in Education.New-Delhi: Vikas Publishing House.

Aggarwal, J.(1995) Essentials of Educational Technology: Teaching Learning Innovations in Education New-Delhi: Vikas Publishing House.

Aggarwal,J.1996Principles, Methods and Techniques of Teaching. New-Delhi: Vikas Publishing House.

Allen, V.(1983) Techniques in Teaching Vocabulary. Oxford: Oxford University Press.

Amare A.(1998)Teacher's Cunningworth, A. 1989 Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials.Oxford: Oxford

Perceptions of Educational Problems in Ethiopia. In Quality Education in Ethiopia:

Best, J. & Kahn, J. (2003) Research in Education. (9th ed.) New Delhi: Prentice Hall. Bowen, B. M. (1982) Look Here!Visual Aids in Language Teaching.

Bestate Terefe .(2000) Application of Instructional Materials in the Primary School.

Celce-Murcia, M. (ed.) (1991) Teaching English as a Second or Foreign Language. Los Angeles Heinle and Heinle Publishers. Clark, L. and Irving, S.

College of Teacher Education, July,12-18 1998. Ashby, E. and Besse,

M. (1972) The Fourth Revolution-Instructional Technology in Higher Education.

Cunningworth, A.(1989) Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials. Oxford

Hong Kong: Macmillan Publishers Ltd. Burns, K. et al. (1999) Teaching Reading:

In Today's Elementary Schools. (7th ed.) New York: Houghton Mittlin Company.Hutchinson, T. and Waters, A. 1987 English For Specific Purposes: ALearning Centered Approach.

New York: McGraw-Hill Co. Atkins, J. et al.(1996) Skills Development methodology Part

Richards and D. Nunan (Eds), Language Teacher Education.Cambridge: Cambridge U niversity Press PP. 66-72. Dubin, F. and Olshtain, E.(1986) Course Design Developing Programs and Materials for.Language Learning

University Press.Day, R.(1990) Teacher Observationin Language Education.In J.C.

Unpublished Master's Thesis, Addis Ababa University, Faculty of Education, Addis Ababa. niversity Press. PP. 66-72. Dubin, F. and Olshtain, E. 1986 Course Design Developing Programs and Materials for Language Learning.

Practices Handbook. London: Heinemann. Grains, R. and Redman, S. 1986 Working with Words:

A Guide to Teaching Vocabulary. Cambridge: Cambridge University Press.

Grant N. (1987) Making the Most of Your Text Book. London:

Longman Group Ltd. Harmer, J. (2001) The Practice of English Language Teaching.

London: Pearson Educational Limited.Harrison, R. H. and Gowin, L. E. (1995) The Elementary Teacher In Action. Sanfransisco:

Wadsworth Publishing Company Inc. Heinich, R. et al. (1996) Instructional Media and Technologies for Learning.

## አባሪ

### አባሪ «ሀ » የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅፅ፣

የሶሻል ሣይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎችናሥነ ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር በ2013 ዓ.ም በአንደኛ ወሰነ ትምህርት በጅማ

አርጆ ወረዳ ሦሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት

መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅፅ፡፡

**ክፍል አንድ፡- አጠቃላይ መግለጫዎች**

1.ሀ. የትምህርት ቤቱ ስም-------------------------------------------

ለ.የክፍልደረጃ--------------------------------------------------------

ሐ.ክፍለ ጊዜ-----------------------------------------------------------------

መ. ምልከታው የተካሄደበት ቀን------------ ወር------------- ዓ.ም.------------------

**ክፍል ሁለት፡- ዝርዝር መረጃዎች**

2. የስምስተር ወይም የመንፈቀ ዓመቱ የትምህርት ዕቅድ ሀ. ተዘጋጅቷል ለ. አልተዘጋጀም

3. የዕለቱ የትምህርት ዕቅድ ሀ. ተዘጋጅቷል ለ. አልተዘጋጀም

4. የስምስትተሩና የዕለቱ ትምህርት ዕቅድ ሀ. በትክክል እየተካሔደ ነዉ ለ.በትክክል እየተካሔደ አይደለም

5. በመንፈቀ ዓመቱ ዕቅድ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሀ. ተጠቅሰዋል

ለ. አልተጠቀሱም

6. በዕለቱ የትምህርት ዕቅድ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

ሀ. ተጠቅሰዋል ለ.አልተጠቀሱም

7. በዓመታዊ እቅድ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተጠቅሰው ከሆነ ከዕለቱ የትምህርት ዕቅድ መርጃ መሣሪያዎች ጋር ይመሳሰላሉ ሀ. ይመሳሰላሉ ለ. አይመሳሰሉም

8. መምህሩ በዕለቱ የተጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

ሀ-------------------------------------------. ለ.----------------------------------------

ሐ--------------------------------------------------መ.--------------------------------------

9. የዕለቱ ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎች ሀ.-------------------------------

ለ.-------------------------------

ሐ.------------------------------

10. መምህሩ የዕለቱን ትምህርት ለመተግበር በአጋዥነት የተጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ ምንድን ነው? ሀ. የመምህሩ መምሪያ ለ. መርሐ ትምህርት ሐ. መምህሩ ከነበራቸው ልምድ በመነሳት ያለምንም አጋዥ (ጠቋሚ) መረጃ ነው የተጠቀሙት

11. መምህሩ የተጠቀሙባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የዕለቱን ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎች ከማሳካት አኳያ ያላቸው ተገቢነት? ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ለ. በጣም ጥሩ ነው .ሐ.ጥሩ ነው መ. አነስተኛ ነው

12. በዕለቱ መምህር/ርትዋ/ የተጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ መጠን?

ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው ሐ. ጥሩ ነው ለ. በጣም ጥሩ ነው መ. አነስተኛ ነው

13. በዕለቱ መምህሩ/ርትዋ/ የተጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ ጥራት?

ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው ሐ. ጥሩ ነው ለ. በጣም ጥሩ ነው መ. አነስተኛ ነው

14. በዕለቱ መምህሩ የተጠቀመዉ የትመህርት መርጃ መሣሪያዎች የተገኙት እንዴት ነው? ሀ.ተገዝተው ነው ለ. ከአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች የተዘጋጁ ናቸው ሐ. በስጦታ መልክ የተገኙ ናቸዉ መ. ከትምህርት ቤቱ የተገኙ ናቸው

14.1ተገዝተው ለአገልግሎት የዋሉ ከሆነ ማን ገዛቸው?

14.2 ከአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች የተዘጋጁ ከሆነ ማን አዘጋጃቸው?

14.3 በስጦታ መልክ የተገኙ ከሆነ ከማን?

15. በዕለቱ መምህር/ርትዋ/ የተጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ መጠን?

ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው ሐ. ጥሩ ነው ለ. በጣም ጥሩ ነው መ. አነስተኛ ነው

16. በዕለቱ መምህሩ/ርትዋ/ የተጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ ጥራት?

ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው ሐ. ጥሩ ነው ለ. በጣም ጥሩ ነው መ. አነስተኛ ነው

17. በዕለቱ መምህሩ/ርትዋ/ የተጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ ለዕለቱ ትምህርት ተስማሚነቱ ምን ያህል ነው? ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው ሐ. ጥሩ ነው ለ. በጣም ጥሩ ነው መ. አነስተኛ ነው

18. በዕለቱ መምህሩ/ርትዋ/ የተጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ ዓይነቱ ከየትኛው ዓይነት ይመደባል? ሀ. ዕይታዊ ለ. ድምፃዊ ሐ. ድምፃዊ እና ዕይታዊ

19. የመምህሩ/ርትዋ/ በትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ የመጠቀም ብቃታቸው? ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው ሐ. ጥሩ ነው ለ. በጣም ጥሩ ነው መ. በቂ ነው ሠ. አነስተኛ ነው

20. የዕለቱ የትምህርት መርጃ መሣሪያ የመማር ማስተማር ሂደቱን ተማሪ ተኮር ለማድረግ ያለው እገዛ? ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው ሐ. ጥሩ ነው ለ. በጣም ጥሩ ነው መ. አነስተኛ ነው

21. በዕለቱ የቀረበው የትምህርት መርጃ መሣሪያ ማራኪነት? ሀ. ሁሉም ተማሪዎች የደስታ ስሜት ይታይባቸዋል ለ. አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የደስታ መንፈስ ይታይባቸዋል ሐ. ግማሽ ያህሉ የደስታ መንፈስ ይታይባቸዋል ሠ. ሁሉም ተማሪዎች የደስታ መንፈስ አይታይባቸውም

22. ተማሪዎች በዕለቱ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በመታገዝ የተማሩትን ትምህርት በክፍለ ጊዜው መጨረሻ መምህሩ ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች የሚሰጡት ምላሽ? ሀ. እጅግ በጣም ፈጣን ነው ለ. በጣም ፈጣን ነው መ. ዝቅተኛ ነው ሠ. በጣም ዝቅተኛ ነው

23. በዕለቱ አገልግሎት ላይ የዋለው የትምህርት መርጃ መሣሪያ ምንን ለማስተማር ነው?

ሀ. የንባብ ክሂልን ሐ. የመፃፍ ክሂልን ሠ. ቃላትና ሰዋስውን ለ. የማዳመጥ ክሂል

መ. የመናገር ክሂልን ረ. ክሂሎችን በቅንጅት

24. ተማሪዎች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ በመጠቀም የሚያሳዩት የክፍል ውስጥ ተሳትፎ (participation) ምን ይመስላል? ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው ሐ. ጥሩ ነው

ለ. በጣም ጥሩ ነው መ. አነስተኛ ነው

25.ተማሪዎች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎቹ በመጠቀም የሚያሳዩት የዕርስ በርስ መስተጋብር (Interaction) ምን ያህል ነው?

ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ነው ሐ. ጥሩ ነው ለ. በጣም ጥሩ ነው መ. አነስተኛ ነው

**አባሪ «ለ የፅሁፍ መጠይቅ፡**

• በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

» በጅማ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎችና ሥነ ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር በ2013 ዓ.. በአንደኛ ወሰነ ትምህርት በጅማ አርጆ ወረዳ በሦሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ  የፅሁፍ መጠይቅ፡፡

ውድ መምህር/ት የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በሦሥት ሁለኛ ደረጃ እና  የሰባተኛ እና የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም መፈተሽና የታዩትን ችግሮች መርምሮ የመፍትሄ ሀሳብ ለመጠቆም ሲባል ለተዘጋጀው ጥናት መረጃ መሠብሰብ ነው፡፡

ጥናቱ ከተፈለገው ግብ እንዲደርስ ተገቢ መረጃዎችን መሰብሰብና ማጠናከርን ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም መልስዎትን በማያሻማ መልኩ በተሰጠው ቦታ ላይ እንዲያስፍሩልኝ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ስለ ትብብሮ አመሰግናለዉ፡፡

ማሳሰቢያ

• ጥናቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ የርስዎ ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ ትክክለኛ መረጃ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

• በመጠይቁ ላይ የሰፈሩትን ጥያቄዎች ከሌላ ሰው በመነጋገር መሙላት በጥናቱ ውጤት ላይ ተፅዕኖ ስለሚያሳድር ብቻዎትን ይሙሉት፡፡

• ከተነሱት ጥያቄዎች ሌላ ተጨማሪ ሀሳብ ካለዎት በመጠይቁ መጨረሻ ላይ ማስፈር ይችላሉ፡፡

• የሚያሰፍሯቸው መረጃዎች በሙሉ መጠይቁ ከተዘጋጀበት የጥናት ዓላማ ውጭ ለምንም ነገር አይውሉም፡፡  ውድ ጊዜዎን ሰውተው ተገቢውን መረጃ ሊሰጡ ፈቃደኛ በመሆንዎ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡  ህዳር 2013 ዓ.ም

**ክፍል አንድ፡- የግል ሁኔታ መግለጫ፣**

1. የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት--------------------------------

2. ፆታ ሀ. ሴት ለ. ወንድ

3. የአገልግሎት ዘመን ሀ. ከ1-5 ለ. ከ6-10 ሐ. 11-20 መ. ከ21 ዓመት በላይ

4. የትምህርት ደረጃ ሀ. ዲፕሎማ ለ. ዲግሪ ሐ.ሁለተኛ ዲግሪ

5. በኮሌጅ ደረጃ ሰልጥነው ከሆነ የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት /ዐቢይ-------------------------

ንዑስ------------------------------

6. የተመረቁበት ዘመን. ------------------------------------------

7. የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ ሀ.9ኛ ክፍል ለ. 10ኛ ክፍል ሐ. 9ኛ እና 10ኛ መ. --

8. በሳምንት ውስጥ ምን ያህል ክፍለ ጊዜያት ያስተምራሉ?ሀ.ከ10-14 ለ.ከ11-15 ሐ.ከ16- 20 መ.ከ20-24 ሠ. ከ25 በላይ

**ክፍል ሁለት፡- ዝርዝር መረጃዎች**

9. የትምህርት መርጃ መሣሪያን የሚመለከት ትምህርት ራሱን የቻለ አንድ ኮርስ ሆኖ ተምረውታል? ሀ. ተምሬያለሁ ለ. አልተማርኩም ሐ. ትምህርቱም ራሱ መኖሩን አላውቅም

10. በቅድመ ሥራ ላይ ሥልጠና ኮርሱን ወሰደው ከሆነ ስለትምህርት መርጃ መሣርያ አጠቃቀም በቂ የሆነ ተግባሪዊ ልምምድና ትምህርት ያገኙ ይመስልዎታል? ሀ. ይመሰለኛል ለ.አይመስለኝም ሐ. አስተያየት ለመስጠት ይከብደኛል

11. ለጥያቄ ተራ ቁጥር «10» መልስዎ ይመስለኛል የሚል ከሆነ ኮርሱ የትምህርት መርጃ መሣርያዎችን አጠቃቀም በሚመለከት ላለብዎት ኃላፊነት በብቃት አዘጋጅቶኛል ብለው ያስባሉ? ሀ.በከፍተኛ ደረጃ አዘጋጅቶኛል ለ.ምንም አላዘጋጀኝም ሐ.በመጠኑ አዘጋጅቶኛል መ.አላዉቅም

12. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የሚመለከት ትምህርት በኮርስ ደረጃ ተምረው ከሆነ ትምህርቱ ለማስተማር ሥራዎ የሚሰጠውን ጥቅም በሚገባ ያወቁት መቼ ነው?

ሀ. ትምህርቱን በምከታተልበት ጊዜ ለ. አላስታውስም ሐ. ትምህርቱን ጨርሼ ወደ ሥራ ዓለም ከገባሁ በኋላ መ. ከተወሰነ ዓመት በኋላ

13. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በተመለከተ በሥልጠና ወቅት ኮርሱ ከተሰጠዎ ትምህርቱን በዕርጋታ ለመከታተል በወቅቱ በቂ ጊዜ አግኝተዋል? ሀ. አግኝቻለሁ

ለ. አላገኘሁም ሐ. ዛሬ ላይ አላስታወሰውም

14.መሣሪያዎችን አጠቃቀም የሚመለከት ፅሁፍ በተቀነባበረ መልኩ(Handout)በአሰልጣኝዎ ተሰጥቶዎታል? ሀ. አዎ ለ. የለም ሐ. ሌላ መልስ ካለ ይግለፁ

15. ለጥያቄ አስራ አራት መልስዎ «አዎ» የሚል ከሆነ ፅሁፉ በሥራዎ ላይ ምን ያህል ጠቀሞዎታል? ሀ. እጅግ በጣም ለ. በጣም ሐ. በመጠኑ መ. ምንም አልጠቀመኝም

16. ለጥያቄ አስራ አራትመልስዎ «የለም» የሚል ከሆነ ስለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ያለዎትን ዕውቀት ከየት አገኙት? ሀ. ከስራ ላይ ሥልጠና ለ. ከተለያዩ ጓደኞቼ ሐ. ራሴ በማደርገው ጥረት መ. በልዩ ልዩ አጋጣሚና ከግል ተሞክሮ

17. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የሚመለከት የሰራ ላይ ስልጠና ተካፍለው ያውቃሉ? ሀ. ለአንድ ጊዜ ያህል ተካፍያለሁ ለ.ከአንድ ጊዜ በላይ ተከፍያለሁ ሐ.በጭራሽ አልተካፈልኩም

18. ለጥያቄ ተራ ቁጥር አስራ ሰባት መልስ «ተካፍዬ አውቃለሁ»

የሚል ከሆነ ሥልጠናው የተዘጋጀው? ሀ. በትምህርት ቤት ደረጃ ለ. በወረዳ ጽህፈት ቤት ደረጃ ሐ. በዞን ጽህፈት ቤት ደረጃ

19. በአሁኑ ሰዓት የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀም በሚመለከት በቂ ዕውቀትና ችሎታ ያለዎት ይመስልዎታል? ሀ. ከበቂ በላይ አለኝ ለ. በቂ አለኝ ሐ. በቂና ችሎታ የለኝም መ. ምንም ዕውቀት የለኝም

20. በዕርስዎ አመለካከት የመማር ማስተማሩን ሂደት ስኬታማ ለማድረግ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚጫወቱት ሚና ምን ያህል ነው? ሀ. በጣም ከፍተኛ ለ.ከፍተኛ ሐ.ዝቅተኛ መ. ምንም ሚና የለውም

21. ትምህርት ቤትዎ ከፋብሪካ የሚገኙ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለመጠቀም የበጀት ችግር አለበዎት? ሀ. በተወሰነ ደረጃ ችግር አለ ለ.መኖር አለመኖሩን አላውቅምሐ. በጣም ችግር አለ መ. ምንም ችግር የለም

22. ተማሪዎች በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ታግዘው ሲማሩ የአቀባበልና የማስታወስ ችሎታቸው ከፍ ይላል ብለው ያምናሉ? ሀ. በጣም አምናለሁ ለ. በፍፁም አላምንም

ሐ. በመጠኑ አምናለሁ መ. ለመወሰን ያስቸግራል

23. ከትምህርት ቤትዎ ውጭ ካሉ ምንጮች ልዩ ልዩ ለትምህርት መርጃ መሣሪያ የሚያግዙ መሣሪያዎችን ለመግዛት የሚያስችል በጀት በስጦታ መልክ ለማግኘት ምን ያህል ጥረት እያደረጉ ነው? ሀ. በጣም በርካታ ጥረት ለ. አነስተኛ ጥረት ሐ. መካከለኛ ጥረት መ. ምንም ጥረት አላደረግሁም

24. በመምህራን መገምገሚያ ላይ የትምህርት መርጃ መሣሪያን መጠቀም የሚመለከት ነጥብ መካተቱ ተገቢ ነው ይላሉ? ሀ. በጣም ተገቢ ነው ለ. በተወሰነ ደረጃ ተገቢነት ይኖረዋል

ሐ.ተገቢነት የለውም መ. ለመወሰን እቸገራለሁ

25. ትምህርት ቤትዎ በቴክኖሌጅ ውጤቶች ለመጠቀም ያለው አመችነት ምን ያህል ነው? ሀ. ከፍተኛ ነው ለ. መጠነኛ ነው ሐ. ምንም ምቹነት የለውም

26. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በሚመለከት ያጋጠመዎት ችግር አለን?

27. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በሚመለከት ከመምህራን ምን ይጠበቃል?

28. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀምን በሚመለከት ለወደፊቱ አስፈላጊ ነው የሚሉትን ሀሳብ ያስፍሩ?

## አባር ሐ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

**በጅማ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎችና ሥነ ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር በ2013 ዓ.ም.በአንደኛ ወሰነ ትምህርት በጅማ አርጆ ወረዳሦሥት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችት በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ፤**

**ቃለ መጠይቅ፡፡**

ውድ መምህር/ት የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ ሦሥት ሁለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም መፈተሽና የታዩትን ችግሮች መርምሮ የመፍትሄ ሀሳብ ለመጠቆም ሲባል የተዘጋጀ ጥናታዊ መረጃ መሠብሰብ ነው፡፡

ጥናቱ ከተፈለገው ግብ እንዲደርስ ተገቢ መረጃዎችን መሰብሰብና ማጠናከርን ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም መልስዎትን በማያሻማ መልኩ እንዲመልሱልኝ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

ማሳሰቢያ

• ጥናቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ የርስዎ ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ ትክክለኛ መረጃ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ውድ ጊዜዎን ሰውተው ተገቢውን መረጃ ሊሰጡ ፈቃደኛ በመሆንዎ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ህዳር 2013 ዓ.ም

**ክፍል አንድ፤ቃለ መጠየቅ**

1. የሰለጠኑበት ተቋም የት ነው ሀ. ኮሌጅ ለ. ዩኒቨርሲቲ ሐ. ሌላ ካለ ይግለፁ

2. የአገልግሎተ ዘመንዎ ስንት ነው

3. በክፍል ውስጥ የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ብዛት በአማካይ ምን ያህል ናቸው?

4. በሰለጠኑበት ተቋም (ኮሌጅ) ትምህርት መርጃ መሣሪያን የሚመለከት ኮርስ ራሱን ችሎ ወሰደዋል? ሀ. አዎ ለ. የለም

5. ለተራ ቁጥር አራት ጥያቄ መልስዎ አዎ ከሆነ ወደ ሥራ ከተሰማሩ በኂላ ያደረገለዎት እገዛ? ሀ. እጅግ በጣም ጥሩ ለ. በጣም ጥሩ ነው ሐ. ጥሩ ነው መ. መጠነኛ ነው ሠ. ምንም አላገዘኝም

6. በትምህርት መርጃ መሣሪያ ተጠቅሞ ማስተማር ጠቀሜታ አለው ብለው ያስባሉ?

7. የቋንቋውን ትምህርት በቋንቋ ትምህርት መርጃ መሣሪያ አስደግፎ ማቅረብ ለተማሪውና ለመምህሩ ይጠቅማል? ለምን?

8. የትምህርት መሣሪያዎች (የመምህሩ መምሪያ፣ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍና መርሐ ትምህርቱ) በትምህርት መርጃ መሣሪያ ለመጠቀም እገዛ አላቸው? ለምን?

9. እርስዎ የበለጠ ያግዘኛል ብለው የሚጠቀሙበት የትምህርት መሣሪያ (መርሐ ትምህርት፣ የመምህሩ መምሪያ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ) የትኛው ነው በሚገባ ያግዘኛል የሚሉት?

10. የሚጠቀሙባቸውን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የሚያገኙት ከየት ነው? እንዴት ያገኛቸዋል?

11. በማስተማር ሙያ ላይ እያሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያን በተመለከተ የሙያ ላይ ስልጠና አግኝተዋል? በማን አዘጋጅነት?

12. ስለትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም በመምህራን መገምገሚያ ስለመስፈሩ ያለዎት አስተያየት ምንድን ነው?

13. በመማር-ማስተማር ሂደት በትምህርት መርጃ መሣሪያ ከተገለገሉ በኂላ የዕለቱ ትምህርት ለተማሪዎች ግልፅ መሆኑን እንዴት ያውቃሉ?

14. በትምህርት ቤትዎ የትምህርት መርጃ መሣሪያን ለመጠቀም የሚያገዙ የተመቻቹ የቴክኖሎጂ ውጤቶች አሉ?

15. የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ በትምህርት ቤትዎ ሃሳብ የሚለዋወጧቸው መምህራን አሉ? በሙያዎት ላይስ ምን ያህል እገዛ አድርጓል?

16. ለእለቱ የትምህርት ይዘት አስፈላጊ ነው ብለው የተጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ ተማሪዎችዎን ግራ ያጋባበት ጊዜ ይኖራል? የለም ካሉ ያላጋጠመዎት ለምን ይመስለዎታል?

17. የአማርኛ ቋንቋን የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ ያጋጠመዎት ችግር አለ? ካለ ምንድርነዉ?

18. አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙበት የትምህርት መርጃ መሣሪያ አይነት ምን አይነት ነው? ለምን?

19. አብዛኛውን ጊዜ የትምህርት መርጃ መሣሪያ የሚጠቀሙት የትኛውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ለማስፈፀም ነው? ለምን?

20. ለወደፊቱ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ መሆንና መደረግ ስለአለበት ሁኔታ ያለዎት አስተያየት ምንድን ነው?